# የገቢዎች ሚኒስቴር








## የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት






ሀምሌ, 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ማውጫ


ክፍል አንድ ........ 1
1 መግቢያ ........ 1
ክፍል ሁለት ........ 2
2 የተቋማዊ የማስፈጸም አቅም ስራዎች አፈጻጸም ........ 2
2.1 የዕቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ስራዎች አፈጻጸም ........ 2
2.2 የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር አሰራርና ውጤታማነት ማሻሻል አፈጻጸም ........ 4
2.3 የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል አፈጻጸም ........ 2
2.4 የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አሰራርንና ውጤታማነት ስራዎች አፈጻጸም ........ 7
2.5 ለተጠሪ ተቋማት እና ለክልሎች የሚደረግ ድጋፍና ክትትል ማሻሻል አፈጻጸም ........ 23
2.6 የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ክትትል ሥራዎች አፈጻጸም ........ 27
2.9. የበጎ አድራጎት እና የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎች አፈጻጸም ........ 32
ክፍል ሦስት ........ 35
3 በቁልፍ የውጤት አመልካቾች (KPIS) ላይ የተመሰረተ የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ........ 35
3.1 ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ተደራሽ የታክስና ጉምሩክ አስተዳደር ሥራዎች አፈጻጸም ........ 35
3.1.1 የገቢ አሰባሰብ የህግ ማዕቀፎችና አሰራሮችን የማሻሻል ሥራዎች አፈጻጸም ........ 35
3.1.2 የታክስ መረጃ አስተዳደር ውጤታማነት ማረጋገጥ ስራዎች አፈጻጸም ........ 38
3.1.3 የኤሌክትሮኒክ ታክስ (E-Tax) አጠቃቀምን ማሻሻል ስራዎች አፈጻጸም ........ 42
3.1.4 የቀረጥና ታክስ አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን ማረጋገጥ ስራዎች አፈጻጸም ........ 44
3.1.5 የጉምሩክ ስነስርዓት ማሻሻል ስራዎች አፈጻጸም ........ 51
3.2.1 የታክስ ማስታወቅና ክፍያ አቀራረብ ማጠናከር ስራዎች አፈጻጸም ........ 55
3.2.3 የታክስ ማጭበርበርና ኮንትሮባንድ መከላከል ስራዎች አፈጻጸም ........ 74
ሰንጠረዥ 49፡- በንግድ ማጨበርበር እና በኮንትሮባንድ መከላከል አፈፃፀም የተገኘ ውጤት ........ 77
3.2 ዘላቂ የመንግስት ገቢ ዕድገት የማረጋገጥ ስራዎች አፈጻጸም ........ 77
3.2.1 ከሀገር ውስጥ ታክስ የሚሰበሰብ ገቢን ማሳደግ ስራዎች አፈጻጸም ........ 77
3.2.2 የታክስ ዕዳ አሰባሰብ አቅም ማጎልበት ሥራዎች አፈጻጸም ........ 84
3.2.3 የ2016 በጀት ዓመት የግቦች አፈጻጸም ........ 85
3.2.4 ሰንጠረዥ 55 የግቦች፣ የዋና ዋና ተግባራት እና የቁልፍ የአፈጻጸም አመላካቾች አፈጻጸሞች ........ 85
3.2.5 ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሃብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አፈጻጸም ........ 85
3.2.6 ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ተደራሽ የታክስና ጉምሩክ አስተዳደር ስርዓትን ማጎልበት አፈጻጸም ........ 87
3.2.7 የታክስና ጉምሩክ ህግ ተገዥነት ማረጋገጥ አፈጻጸም ........ 89
3.2.8 የዘላቂ የመንግስት ገቢ ዕድገት ማረጋገጥ አፈጻጸም ........ 91
ክፍል አራት ........ 93
4. በአፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶች እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ........ 93
4.1 በአፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶች ........ 93
4.2 የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ........ 93
ክፍል አምስት ........ 95
5 ማጠቃለያ ........ 95

# ሰንጠረዦች

ሰንጠረዥ 1 የተሰጡ ስልጠናዎች በስልጠና ዓይነትና በኃላፊነት ደረጃ....1
ሰንጠረዥ 2 የሀገር ውስጥ ታክስ የበጀት ዓመቱ አጠቃቀም በወጪ ሂሣብ መደቦች....2
ሰንጠረዥ 3 የጉምሩክ ኮሚሽን የ12 ወራት የበጀት አጠቃቀም በወጪ ሂሣብ መደቦች....3
ሰንጠረዥ 4 የሃገር ውስጥ ታክስና የጉምሩክ ኮሚሽን የ12 ወራት የበጀት አጠቃቀም....4
ሰንጠረዥ 5 የኂላ ዘመናት የፌዴራል ኦዲት ግኝት ማስተካከያ አፈጻጸም....4
ሰንጠረዥ 6 በ2016 በጀት ዓመት ስልጠና የወሰዱ ክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች....23
ሰንጠረዥ 7 እስከ አሁን ወደ ስርዓቱ የገቡና እያስታወቁ ያሉ....43
ሰንጠረዥ 8 የኤሌክትሮኒክ ክፍያ (E-PAYMENT) የእስከ አሁን አፈጻጸም....43
ሰንጠረዥ 9 የቴሌብር ኤሌክትሮኒክ ክፍያ (E-PAYMENT) የእስከ አሁን አፈጻጸም....44
ሰንጠረዥ 10 የቴሌብር ኤሌክትሮኒክ ክፍያ (E-PAYMENT) የበጀት ዓመቱ አፈጻጸም....44
ሰንጠረዥ 11 የግብር ከፋዮች ምዝገባ አፈጻጸም....45
ሰንጠረዥ 12 የአገልግሎት ኦዲት አፈጻጸም በማህደር....46
ሰንጠረዥ 13 የአገልግሎት ኦዲት አፈጻጸም በገንዘብ (በፍሬ ግብር)....46
ሰንጠረዥ 14 የታክስ ተመላሽ ስራዎች አፈጻጸም....47
ሰንጠረዥ 15 የተመላሽ አፈጻጸም በገንዘብ....47
ሰንጠረዥ 16 የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አፈታት አፈጻጸም....47
ሰንጠረዥ 17 የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አፈታት ሁኔታ በቅ/ጽ/ቤቶች....48
ሰንጠረዥ 18 የሀገር ውስጥ ታክስ ማብራሪያና ምክር አገልግሎት ስራዎች አፈጻጸም....49
ሰንጠረዥ 19 የጉምሩክ ማብራሪያና ምክር አገልግሎት ስራዎች አፈጻጸም....49
ሰንጠረዥ 20 የአጠቃላይ ቅሬታ አፈታት አፈጻጸም....50
ሰንጠረዥ 21 የቀረጥ ነፃ መስተንግዶ አገልግሎት አፈጻጸም መረጃ....52
ሰንጠረዥ 22 የውጭ ንግድ ዕቃ አፈጻጸም መረጃ በዶላር....53
ሰንጠረዥ 23 የንግድ ትርፍ ግብር ማስታወቅ አፈጻጸም....55
ሰንጠረዥ 24 የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቅ አፈጻጸም....56
ሰንጠረዥ 25 የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቅ አፈጻጸም....57
**ሰንጠረዥ 26 የስሌት ስራዎች አፈጻጸም እና በልዩነት የተገኘ የገንዘብ መጠን....58**
ሰንጠረዥ 27 ዘግይተው በቀረቡ የታክስ ማስታወቂያዎች ላይ የተሰራ ስሌት እና የተወሰነ ገቢ....58
ሰንጠረዥ 28 በማሳወቂያ ጊዜ ኢ-ፋይል አድርገው ክፍያ ያልከፈሉት ላይ የተሰራ ስሌት....59
ሰንጠረዥ 29 ሌሎች በዴስክ የተሰራ የታክስ ስሌት....59
ሰንጠረዥ 30 የግብር ዕፎይታ ዝርዝር መረጃ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሲታይ....60
ሰንጠረዥ 31 የገቢ ግብር ነፃ መብት አሰጣጥ መረጃ....61
ሰንጠረዥ 32:- የገቢ ግብር ነፃ መብት የተሰጣቸው ግብር ከፋዮች በሥራ መስክ....61
ሰንጠረዥ 33 አጠቃላይ የታክስ እፎይታ ተጠቃሚዎች....63
ሰንጠረዥ 34 ያላስታወቁ ግብር ከፋዮች ክትትል አፈጻጸም....63
ሰንጠረዥ 35 የኦዲት አፈጻጸም በማህደር....71
ሰንጠረዥ 36 የኦዲት አፈጻጸም በገንዘብ (በፍሬግብር)....71
ሰንጠረዥ 37 የኦዲት ውጤት በኦዲት ዓይነት፣ የቀነሰ ኪሳራ እና የቀነሰ ተመላሽ....71
ሰንጠረዥ 38 በግብይት ወቅት ደረሰኝ የማይቆርጡ ድርጅቶች ላይ የተወሰደ እርምጃ በቅ/ጽ/ቤት....72
ሰንጠረዥ 39 የኢንተለጀንስ ጥናት ተደርጎባቸው ኦዲት እንዲደረጉ ለኢንቨስትጌሽን ኦዲት የተላለፉ ድርጅቶች....73
ሰንጠረዥ 40. የኢንቨስትጌሽን ኦዲት ሥራዎች አፈጻጸም....73
ሰንጠረዥ 41. የገቢ እና ወጪ ኮንትሮባንድ አፈጻጸም መረጃ....75
ሰንጠረዥ 42. የገቢ ኮንትሮባንድ ፍሰት በዕቃዎች ዓይነት....75
ሰንጠረዥ 43 የበጀት ዓመቱ አጠቃላይ የገቢ አሰባሰብ አፈጻጸም....78
ሰንጠረዥ 44 የሀገር ውስጥ ታክስ የገቢ አፈጻጸም በቅ/ጽ/ቤቶች....78
ሰንጠረዥ 45 የሀገር ውስጥ ታክስ ገቢ አፈጻጸም በታክስ ዓይነት....78
ሰንጠረዥ 46 የውጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ ገቢ አፈጻጸም በቅ/ጽ/ቤቶች....79
ሰንጠረዥ 47 የውጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ ገቢ አፈጻጸም በታክስ ዓይነት....80
ሰንጠረዥ 48 ለክልሎች የተላለፈ የጋራ ገቢ....80

ሰንጠረዥ 49 የጋራ ገቢ ትልልፍ በንጽጽር....81
ሰንጠረዥ 50 የውክልና/ዊዝሆልዲንግ/ ታክሶች ገቢ ትልልፍ....81
ሰንጠረዥ 51 የዊዝሆልዲንግ ታክሶች ንጽጽር....82
ሰንጠረዥ 52 አጠቃላይ የጋራ ገቢና የዊዝሆልዲንግ ታክሶች ጥቅል ትልልፍ....82
ሰንጠረዥ 53 የጋራ ገቢ እና የዊዝሆልዲን ታክሶች ጥቅል ትልልፍ ንጽጽር....83
ሰንጠረዥ 54 የታክስ ዕዳ አሰባሰብ አፈጻጸም....84
ሰንጠረዥ 55 የግቦች፣ የዋና ዋና ተግባራት እና የቁልፍ የአፈጻጸም አመላካቾች አፈጻጸሞች....85

# ክፍል አንድ

## 1 መግቢያ

የገቢው ዘርፍ የገቢ አሰባሰብ አፈጻጸምን ለማሻሻል ህገወጥ ንግድን በመቆጣጠር በህግ የተሰጡትን ስልጣንና ኃላፊነቶች በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችሉ ከአስር፣ ከአምስት ዓመቱ እና ከመካከለኛ ዘመን (2016- 2018) የልማትና ኢንቨስትመንት ዕቅዶች የተመነዘረ የ2016 ዓመታዊ ዕቅድ በማቀድ ወደ ስራ ገብቷል፡፡ በዚሁ መሰረት ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራርን ማሻሻል፣ ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ተደራሽ የቀረጥና ታክስ አስተዳደር ሥርዓትን ማጎልበት፣ የታክስና ጉምሩክ ሕግ ተገዥነት ማረጋገጥ እና ዘላቂ የመንግስት ገቢ ዕድገት ማረጋገጥ የሚባሉ አራት ስትራቴጂክ ግቦችንና በስራቸው ዋና ዋና ተግባራትን በማስቀመጥ ለ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ ስኬት ጉልህ ድርሻ የሚኖራቸው ቀረጥና ታክስ በፈቃደኝነት መክፈል ባህል ማሳደግ፣ ዲጂታል የቀረጥና ታክስ አስተዳደር ስርዓትን መገንባት፣ የታክስና ጉምሩክ አስተዳደር ፍትሀዊነትን ማረጋገጥ፣ የውስጥ እና የውጭ ስትራቴጂክ አጋርነትን ማጠናከር እና የዳበረ የሥራ ባህል መፍጠር የሚሉትን ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎችን ተከትሎ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡

በ2016 በጀት ዓመት ከሀገር ውስጥ ቀጥታ ታክስ፣ ቀጥታ ካልሆኑ እንዲሁም ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች ብር 319.33 ቢሊዮን ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 321.85 ቢሊዮን በመሰብሰብ የዕቅዱን 100.79 በመቶ ሲሳካ ከውጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች ደግሞ ብር 210.00 ቢሊዮን ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 190.98 ቢሊዮን በመሰብሰብ የዕቅዱን 90.94 በመቶ ማሳካት ተችሏል፡፡ ስለሆነም በገቢው ዘርፍ በበጀት ዓመቱ ብር 529.33 ቢሊዮን ጥቅል ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 512.33 ቢሊዮን በመሰብሰብ የዕቅዱን 96.88 በመቶ ማሳካት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በ70.81 ቢሊዮን ብር ወይም በ16.02 በመቶ ዕድገት አሳይቷል፡፡

በመጨረሻም የገቢው ዘርፍ ሪፖርት የሥራ ዘርፎችን፣ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን፣ የታክስ ማዕከላትን እና የመቅረጫ ጣቢያዎችን ሪፖርት በመረጃ ምንጭነት በመጠቀም የተዘጋጀ ሲሆን መረጃዎቹም ተተንትነዉ ግልጽ በሆነ መልኩ የቀረቡና የሪፖርቱም አደረጃጀት በተመለከተ በክፍል አንድ መግቢያ፣ በክፍል ሁለት የተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት ሥራዎች፣ በክፍል ሶስት በቁልፍ የውጤት አመልካቾች (KPIs) ላይ የተመሰረተ የዕቅድ አፈጻጸም ትንተና እና በክፍል አራት በአፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶችና የተወሰዱ የመፍትሄ ዕርምጃዎችን ሲያካትት በመጨረሻው ክፍል ደግሞ የሪፖርቱን ማጠቃለያ እንዲይዝ ተደርጎ ተደራጅቷል፡፡

# ክፍል ሁለት

## 2 የተቋማዊ የማስፈጸም አቅም ስራዎች አፈጻጸም

### 2.1 የዕቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ስራዎች አፈጻጸም

**የዕቅድ ዝግጅት ሥራዎች አፈጻጸም** የገቢው ዘርፍ የአስር ዓመት፣ የአምስት ዓመት እና የመካከለኛ ዘመን (2016- 2018) የልማት እና ኢንቨስትመንት የልማት ዕቅዶች መነሻ በማድረግ የአንድ ዕቅድ አንድ ሪፖርት መርህን በመከተል ለ2016 በጀት ዓመት የተጣለውን እና ወደ መንግስት ካዝና ብር 446.38 ቢሊዮን ፈሰስ ለማድረግ የሚሰራ ሲሆን ከሚሰበስበው ጥቅል ገቢ ላይ ለክልሎች የሚተላለፈውን የጋራ ገቢ እና ሌሎች ተቀናናሽ ሂሳቦችን ታሳቢ በማድረግ ጥቅል የገቢ ዕቅድ ብር 529.33 ቢሊዮን ታቅዷል። የገቢ ዕቅዱን በገቢ አርስቶች ተተንትኖ እና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተከፋፍሎ ወደ ስራ ተገብቷል። በዕቅድ ዝግጅቱም ከዋናው መ/ቤት እስከ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ ያሉትን አመራሮችን እና ባለሙያዎችን በማወያየት በዕቅድ ዝግጅቱ ዙሪያ የጋራ መግባባት በመፍጠር እና ዕቅዱን እስከ ፈጻሚ ድረስ በማውረድ ወደ ሥራ ተገብቷል።

በዚሁ መሠረት የ2015 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ፣ በመካከለኛ ዘመን (2016- 2018) የልማት እና ኢንቨስትመንት ዕቅድ እንዲሁም በ2016 ዓመታዊ ዕቅድ ዙሪያ ከዋናው መስሪያ ቤት እስከ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ድረስ ያሉት 209 ወንድ እና 30 ሴት በድምሩ 239 መካከለኛና ከፍተኛ አመራሮች በተገኙበት በሃዋሳ ከተማ በተካሄደ የውይይት መድረክ ላይ በ2016 በጀት ዓመት ሊሰሩ በታሰቡ ሥራዎች ዙሪያ ግንዛቤ ኖሯቸው ዕቅዱን በባለቤትነት ወስደው እንዲተገብሩት የማድረግ ሥራ ተሰርቶ ሲተገበር ቆይቷል። በዚሁ መሰረት በዕቅዱ ዙሪያ መግባባት እነዲፈጠር የተደረገ ሲሆን በሌላ በኩል የገቢው ዘርፍ የሥራ ዘርፎችና ዳይሬክቶሬቶች እንዲሁም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ያለፈውን በጀት ዓመት የአፈጻጸም ግብረ-መልስ በማቅረብ መስተካከል በሚገባቸው ጉዳዮች ዙሪያ የጋራ ውይይት ተደርጓል።

በ2016 በጀት ዓመት የሩብ ፣ የስድስት እና የዘጠኝ ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ከዋናው መስሪያ ቤት እስከ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ድረስ ያሉ ከፍተኛና መካከለኛ አመራሮች በተገኙበት በድሬድዋ ፣ በሃዋሳ ከተማ እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ ግምገማ ተደርጎ ቀጣይ በሚሰሩ ሥራዎች ዙሪያ መግባባት ላይ ተደርሷል። በተጨማሪም የተቋሙ ከፍተኛ አመራሮች፣መካከለኛ አመራሮች እና ሰራተኞች በተገኙበት የአራት ወራት ፣ የሰባት ወራት እና የአስራ አንድ ወራት የተቋሙ ዕቅድ አፈጻጸም ከሀገሪቱ ማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታዎች ጋር በማጣጣም ግንዛቤ እንዲፈጠር ተደርጓል።

የ2016 በጀት ዓመት የሩብ፣ የስድስት እና የዘጠኝ ወራት የገቢና የፊዚካል ሥራዎች ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶችን በማዘጋጀት ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት፣ ለፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ለፕላንና ልማት ሚኒስቴር እንዲሁም ገቢ ነክ ሪፖርቶችን ለገንዘብ ሚኒስቴር ያለምንም ማጓደል የሪፖርት ጥራቱ ተጠብቆ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት የመላክ ሥራ ተሰርቷል። በነዚሁ አካላትም በጽሁፍም ሆነ በቃል በተቋሙ ዕቅድና ሪፖርት አቀራረብ ዙሪያ የተሰጡትን ገንቢ ግብረ-መልሶች በግብዓትነት በመውሰድ የተቋሙ ዕቅድና ሪፖርት አቀራረብ ደረጃው እንዲሻሻል ጥረት

ሲደረግ ቆይቷል፡፡ የተሰጠው ግብረ-መልስም የድርጊት መረሀ-ግብር ተዘጋጅቶለት ለፈጻሚ አካል እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

በ2016 በጀት ዓመት በአጠቃላይ ያለፉ የሪፎርም ዓመታትን ጨምሮ ጥራት ያለው የተደራጀ ሪፖርትና የገለጻ ሰነድ በማዘጋጀት የተቆጣጣሪ አካል ለሆነው ለፕላን፣ በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት በሙሉ በሃዋሳ ከተማ በገቢው ዘርፍ በተሰሩ የሪፎርም ሥራዎች እና የ2016 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ግንዛቤ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

የገቢው ዘርፍ የአስር ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ተዘጋጅቶ በተከበረው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በክብርት ሚኒስትሯ አቅራቢነት እንዲገመገም ተደርጓል፡፡ ከምክር ቤቱ የተሰጡ አስተያየቶችንም ሳይንጠባጠቡ ሙሉ በሙሉ በግብዓትነት እንዲወሰዱ ተደርጓል፡፡

የገቢው ዘርፍ በየሩብ ዓመቱ በዕቅድና ሪፖርት አቀራረብ ዙሪያ ሙያዊ ግብረ-መልስ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ዳይሬክቶሬቶች እየተሰጠ በቀጣይ የሚቀርቡ ዕቅዶችና ሪፖርቶች በተሰጠው ግብረ-መልስ መሰረት እንዲሆን አስችሏል፡፡

የገቢው ዘርፍ የአለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት በሚደገፈው በሀገራዊ Nationl Medium Term Revenue Strategy (NMTRS) ዝግጅትና አለም ባንክ ባዘጋጀው የድጋፍ ኢኒሼቲቭስ (Initatiives) ልየታ ላይ ተሳትፎ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ከዘጠኝ መስሪያቤቶች ማለትም ከጠቅላይ ሚንስትር ጽ/ቤት፣ ከፕላንና ልማት ሚኒስቴር፣ ከጸረ-ሙስና ኮሚሽን፣ ከብሄራዊ ድህንነት፣ ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን እና ከመሳሰሉት ለተውጣጡ የመንግስት የሱፐርቪዥን አባላት በገቢው ዘርፍ የሪፎርም ሥራዎችና ስኬቶች እንዲሁም የታክስ አስተዳደር ስርዓቱን ለማሻሻል ወይም ለማዘመን በተከናወኑ ሥራዎች እና በተቋሙ ዕቅድ አፈጻጸም ዙሪያ የተደራጀ ሰነድ ተዘጋጅቶ ገለጻ ተደርጓል፡፡

**የሰው ኃይል ዝግጅት ስራዎች አፈጻጸም** ተቋሙ ያስቀመጠውን ተልዕኮ ለማሳካት የሰብዓዊና ቁሳዊ ሀብቶች ወሳኝ ሚና ያላቸው መሆኑን በመገንዘብ በ2016 በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ በመዋቅር ከተፈቀደው 23,052 የሥራ መደቦች ውስጥ ወንድ 7,456 እና ሴት 6,405 በድምሩ 13,861 የሰው ኃይል ወይም የመዋቅሩን 60.13 በመቶ በመሸፈን ሥራ ጀምሯል፡፡ የአመራር እና የፈጻሚውን አቅም ለመገንባት የሚያግዙ ሥልጠናዎች ለ3,014 (ወንድ 1,873 እና ሴት 1,141) ሰራተኞች በ2015 በጀት ዓመት የተሰጡ ሲሆን እነኝህ ስልጠናዎች ለ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ ስኬት ከፍተኛ አስተዋጽዎ እንዳላቸው ታሳቢ ተደርጓል፡፡

**የግብዓት ዝግጅት ሥራዎች አፈጻጸም** በሀገር ውስጥ ታክስ እና በጉምሩክ ኮሚሽን በ2016 በጀት ዓመት ለሥራ ማስኬጃ እና ደመወዝ ብር 6,011,760,557.00 እና ለካፒታል ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ብር 1,700,000,000.00 በአጠቃላይ ብር 7,711,760,557.00 በጀት በማስፈቀድ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡

## 2.2 የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር አሰራርና ውጤታማነት ማሻሻል አፈጻጸም

### ➲ የሰው ሃብት አስተዳደር ስራዎች አፈጻጸም

ግልጽነት የሰፈነበት የሰው ኃይል ስምሪትን መሰረት በማድረግ የገቢው ዘርፍ ያስቀመጠውን የሰው ኃይል መሳብ፣ ማቆየትና የመፈጸም ብቃትን ማሳደግ ግብ ለማሳካት በ2016 በጀት ዓመት በተለያዩ የሥራ መደቦች ላይ ብቃት ያላቸው ሰራተኞች በማወዳደር በቅጥር ለመሙላት ታቅዶ 955 (ወንድ 430 እና ሴት 522) ቅጥር በመፈጸም የሰው ሀይል ቁጥሩን 14,220 (ወንድ 7,530 እና ሴት 6,690) ወይም በሽፋን ደረጃ በመዋቅር ከተፈቀደው 27,336 የሥራ መደብ አንጻር ሲታይ 52.02 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ትምህርታቸውን በማስተርስ ጨርሰው ለመጡ የ2015 በጀት ዓመት 31 ተመራቂ ሠራተኞች (ወንድ 12 እና ሴት19) ያላቸውን የትምህርት ዝግጅትና አገልግሎት መሠረት በማድረግ በዋና መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች ምደባ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በተጨማሪም በውጭ ሀገር በመማር ላይ ያሉ 7 ሰራተኞች እና 2 አመራሮች ትምህርት ላይ መሆናቸውን ለውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በመላክ የማረጋገጥ ሥራ ተሰርቷል፡፡ በተጨማሪም የውጭ አገር የትምህርት እድል ያገኙ 5 ሰራተኞች ትምህርታቸውን እንዲማሩ የማመቻቸት ስራ ተሰርቷል፡፡

ለ902 (ወንድ 562 እና ሴት 340) ሠራተኞች ዝውውር ሲከናወን በሌላ በኩል የስራ ተነሳሽነትን ለመጨመር በተለያየ ደረጃ ብቃት ያላቸውን 1444 (ወንድ 685 እና ሴት 759) ሰራተኞች በማወዳደር የደረጃ ዕድገት ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም የካበተ ልምድ ያላቸውን ባለሙያዎች ለማቆየት እንዲቻል አጥጋቢና ከዚያ በላይ የስራ አፈጻጸም ውጤት ላስመዘገቡ ሰራተኞች የ4 እርከን የደመወዝ ጭማሪ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

በገቢው ዘርፍ ከሰራተኞች ከደረጃ ዕድገት፣ ከዝውውር፣ ከአፈጻጸም ምዘና እና ተያያዥ ጉዳዮች ጋር ተያይዞ ለቀረቡ አቤቱታዎች ፈጣን ምላሽ ከመስጠት አንጻር በበጀት ዓመቱ 534 የሰራተኞች ቅሬታ ቀርቦ ለ501ዱ ምላሽ የተሰጠ ሲሆን ቀሪው 33 በመታየት ሂደት ላይ ይገኛል፡፡ የውሳኔ አሰጣጡን በተመለከተ 14 ለቅሬታ አቅራቢው የተወሰነ፣ 396 ለተቋሙ ሲወሰን፣ 66 የተሻሩ እና 25 ውሳኔዎች ደግሞ የተሻሻሉ ሆነዉ የተወሰኑ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ከተቋሙ 593 ሰራተኞች የለቀቁ ሲሆን የለቀቁበት ምክንያት ሲታይም በጡረታ 41፣ በገዛ ፈቃድ 443፣ በሀሰተኛ የት/ት ማስረጃና በዲስፕሊን 78 ፣ በሞት 28 እና በብቃት ማነስ 3 ሰራተኞች ናቸው፡፡

## ➲ የሥልጠና ስራዎች አፈጻጸም

የተቋሙን የመፈጸም አቅም ለማጎልበት በ2016 በጀት ዓመት በ68 የስልጠና ርዕሶች ለ4,328 የአገር ውስጥ ታክስ አስተዳደር፣ የጉምሩክ አስተዳደር እና የክልል የታክስ አስተዳደር አመራሮችና ባለሙያዎች ሥልጠና ተሰጥቷል።

**ሰንጠረዥ 1 የተሰጡ ስልጠናዎች በስልጠና ዓይነትና በኃላፊነት ደረጃ**

| ተ.ቁ. | የስራ ዘርፎች | ዕቅድ | ክንውን | | | | | | | | | አፈጻጸም (%) | የተሠጡ ስልጠና ርዕሶች ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አመራር | | | ባለሙያ | | | ድምር | | | | |
| | | | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | |
| 1 | የአገር ውስጥ ታክስ አስተዳደር | | | | | | | | | | | | |
| 1.1 | ታክስ አስተዳደር | 1097 | 160 | 106 | **266** | 412 | 331 | **743** | 572 | 437 | **1009** | **92** | **22** |
| 1.2 | ድጋፍ ሰጪና መረጃ ቴክኖሎጂ | 573 | 88 | 37 | **125** | 216 | 181 | **397** | 304 | 218 | **522** | **91** | **17** |
| | ድምር 1 | **1670** | 248 | 143 | **391** | 628 | 512 | **1140** | 876 | 655 | **1531** | **92** | **39** |
| 2 | የጉምሩክ አስተዳደር | | | | | | | | | | | | |
| 2.1 | ጉምሩክ አስተዳደር | 1717 | 179 | 37 | **216** | 1011 | 415 | **1426** | 1190 | 452 | **1642** | **96** | **19** |
| 2.2 | ድጋፍ ሰጪና መረጃ ቴክኖሎጂ | 709 | 168 | 84 | **252** | 178 | 256 | **434** | 346 | 340 | **686** | **97** | **18** |
| | ድምር 2 | **2426** | **347** | **121** | **468** | **1189** | **671** | **1860** | **1536** | **792** | **2328** | **96** | **37** |
| 3 | ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች | | | | | | | | | | | | |
| 3.1 | ታክስ አስተዳደር | 640 | 102 | 48 | **150** | 222 | 97 | **319** | 324 | 145 | **469** | **73** | **10** |
| 3.2 | ድጋፍ ሰጪና መረጃ ቴክኖሎጂ | 0 | | | **0** | | | **0** | 0 | 0 | **0** | **0** | |
| | ድምር 3 | **640** | **102** | **48** | **150** | **222** | **97** | **319** | **324** | **145** | **469** | **73** | **10** |
| 4 | አጠቃላይ ድምር (1+2+3) | | | | | | | | | | | | |
| 4.1 | ታክስ አስተዳደር | 1737 | 262 | 154 | **416** | 634 | 428 | **1062** | 896 | 582 | **1478** | **85** | **27** |
| 4.2 | ጉምሩክ አስተዳደር | 1717 | 179 | 37 | **216** | 1011 | 415 | **1426** | 1190 | 452 | **1642** | **96** | **19** |
| 4.3 | ድጋፍ ሰጪና መረጃ ቴክኖሎጂ | 1282 | 256 | 121 | **377** | 394 | 437 | **831** | 650 | 558 | **1208** | **94** | **22** |
| | ድምር | **4736** | **697** | **312** | **1009** | **2039** | **1280** | **3319** | **2736** | **1592** | **4328** | **91** | **68** |

በገቢዎች ሚኒስቴር በሀገር ውስጥ ታክስ በ20 የስልጠና ርዕሶች ለ1,009 አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል። ከእነዚህ ሰልጣኞች ውስጥ 198(19 በመቶ) ከዋናው መ/ቤት ሲሆኑ ቀሪዎቹ 813(81 በመቶ) ከቅ/ጽ/ቤቶች የተሳተፉ ናቸው። በድጋፍ ሰጪ ስራዎችና በመረጃ ቴክኖሎጂ በ17 የስልጠና ርዕሶች ለ522 አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል። ከነዚህ ሰልጣኞች 228 (44 በመቶ) የሚሆኑት ከዋናው መ/ቤት ሲሆኑ ቀሪዎቹ 294 (56 በመቶ) ሰልጣኞች ከቅ/ጽ/ቤቶች የተሳተፉ ናቸው። በድምሩ በ39 የስልጠና ርዕሶች ለ1531 የሚ/ር መ/ቤቱ አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል።

በጉምሩክ አስተዳደር በ19 የስልጠና ርዕሶች ለ1642 አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል። ከዚህ ውስጥም 58 (4 በመቶ) የሚሆኑት ከዋናው መ/ቤት ሲሆኑ፣ ቀሪዎቹ 1584 (96 በመቶ) ከቅ/ጽ/ቤቶች የተሳተፉ ናቸው። በድጋፍ ሰጪ ስራዎችና በመረጃ ቴክኖሎጂ በ18 የስልጠና ርዕሶች ለ686 አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል። ከነዚህ ሰልጣኞች 94 (14 በመቶ) የሚሆኑት ከዋናው መ/ቤት ሲሆኑ ቀሪዎቹ 592 (86 በመቶ) ከቅ/ጽ/ቤቶች የተሳተፉ ናቸው። በድምሩ በ37 የስልጠና ርዕሶች ለ2,328 አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል። ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በ10 የስልጠና ርዕሶች ለ469 አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል።

የተሰጡ የስልጠና ዓይነቶች በታክስ ኦዲት ማንዋል፣ በህግ ተገዥነትና ስጋት አጣጣል፣ ያላሳወቁ ግብር ከፋዮች መለያ፣ በታክስ ህጎች፣ በደንበኞች አያያዝና ድጋፍ፣ በታክስ ከፋይ ምዝገባና ስረዛ ሞጁል፣ በክርክር ክህሎት፣ በፋይናንስ ሞጁል፣ በኢ-ታክስ ሞጁል፣ በሲግታስ ስልጠና፣ በኤክሳይዝ ታክስ፣ በግዥ ሞጁል፣ በቋሚና አላቂ እቃዎች ሞጁሎች፣ በፔሮል ሞጁል፣ በአመራር ሰጪነት ክህሎት፣ በሰው ሃብት አስተዳደር አዋጅ፣ በጉምሩክ ኦፕሬሽን፣ በመጋዘን አስተዳደር፣ በወጪ ንግድ ማበረታቻ ሥርዓት፣ በንግድ ማጭበርበርና በኮንትሮባንድ መከላከል ዙሪያ፣ በስሪት አገር አወሳሰን፣ በትራንዚት አስተዳደር፣ በቆዳና የቆዳ ውጤቶች መለያ ባህሪያቶችና ደረጃዎች፣ በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት፣ በኤሌክትሮኒክ የመንግስት ግዥ ሥርዓት፣ በብሔራዊ መታወቂያ ስርዓት፣ በጋራ ገቢ ትልልፍ፣ በታክስ ተመላሽ፣ በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ቁጥጥርና መረጃ አያያዝ፣ በሶስተኛ ወገን መረጃ አሰባሰብና አጠቃቀም(ታስ)፣ በተሽከርካሪ ስምሪት ስልጠና፣ በመንግስት ሂሳብ አያያዝ፣ በስልጠና አስተዳደር፣ በቢሮ አያያዝና አስተዳደር፣ በበጀት አስተዳደር፣ በመንግስት ግዢ አስተዳደር፣ በክዋኔ ኦዲት እና በታክስ ዕዳ አስተዳደር ዙሪያ የተሰጡ ዋና ዋና የስልጠና ርዕሶች ናቸው።

በማዕከሉ በሚሰጡ ስልጠናዎች ሴቶችና ወጣቶች የተሳትፎ ድርሻን ቢያንስ 40 ከመቶ ለማድረስ ታቅዶ፣ በበጀት ዓመቱ ስልጠና ከተሠጣቸው 4,328 አመራሮችና ባለሙያዎች ውስጥ 1,592 ሴት አመራሮችና ባለሙያዎች ሲሆኑ የተሳትፎ ድርሻቸውም 37 በመቶ ሲሆን ከአመራሮች አኳያ ስልጠና ከተካፈሉ 1009 ወንድና ሴት አመራሮች ውስጥ 312 ሰልጣኞች ሴት አመራሮች ሲሆኑ የአፈጻጸም ድርሻቸውም 31 በመቶ ይይዛል።

ለአዲስ ቅጥር ተወዳደሪዎች ፈተና ከመስጠት አኳያ በአጠቃላይ ለፈተና በቀረቡ በ22(ሃያ ሁለት) የሥራ መደቦች ለ434 ተወዳዳሪዎች ፈተና የመስጠት ስራ እንዲሁም ለደረጃ ዕድገት ተወዳዳሪዎች ፈተና ከመስጠት አንጻር የደረጃ ዕድገት ተወዳዳሪዎችን ብቃት ለመመዘን ፈተና እንዲሰጥ ጥያቄ ለቀረበላቸው 66 የሥራ መደቦች ለፈተናው ለቀረቡ 251 ተወዳዳሪዎች ፈተና ተሰጥቶ የሁለቱንም ውጤት ለሚመለከተዉ አካል የማስተላለፍ ሥራ ተሰርቷል።

## 2.3 የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል አፈጻጸም

### ➲ የበጀት አስተዳደር ስራዎች አፈጻጸም

ሰንጠረዥ 2 የሀገር ውስጥ ታክስ የበጀት ዓመቱ አጠቃቀም በወጪ ሂሣብ መደቦች

| ተ.ቁ | ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች | እስከ ሰኔ 30 ድረስ የተስተካከለ ዓመታዊ በጀት | የ12 ወራት የበጀት ዕቅድ | የ12 ወራት የበጀት ክንውን | የበጀት አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሥራ አመራር ፕሮግራም | 2,552,725,774.51 | 2,552,725,774.51 | 2,489,351,772.82 | 97.52 |
| 2 | ሀገር ውስጥ ገቢ አሰባሰብ | 556,844,423.22 | 556,844,423.22 | 545,769,830.59 | 98.01 |
| 3 | የታክስ ህግ ተገዥነት | 502,332,726.81 | 502,332,726.81 | 483,103,705.24 | 96.17 |
| 3.1 | የታክስ ስወራና ማጭበርበር ተግባራትን መከላከል | 474,400,265.94 | 474,400,265.94 | 459,314,741.87 | 96.82 |
| 3.2 | የታክስ ፍትሐብሔር ክስ ጉዳዮች ውጤታማነት | 8,667,478.87 | 8,667,478.87 | 7,279,129.49 | 83.98 |
| 3.3 | የታክስ ከፋዮች ትምህርት | 19,264,982.00 | 19,264,982.00 | 16,509,833.88 | 85.70 |
| 4 | ዘመናዊ የመረጃ ስርዓት | 127,303,086.35 | 127,303,086.35 | 94,494,293.16 | 74.23 |
| 4.1 | የታክስ የመረጃ ቴክኖሎጂ ልማትና አጠቃቀም | 118,190,600.99 | 118,190,600.99 | 86,342,739.91 | 73.05 |
| 4.2 | የታክስ መረጃ ማጠናቀርና ማሰራጨት | 9,112,485.36 | 9,112,485.36 | 8,151,553.25 | 89.45 |
| **የመደበኛ በጀት ጠቅላላ ድምር** | | **3,739,206,010.89** | **3,739,206,010.89** | **3,612,719,601.81** | **96.62** |
| 5 | **የካፒታል ፕሮጀክቶች** | **841,651,088.00** | **841,651,088.00** | **685,145,097.71** | **81.40** |
| 5.1 | የተቀናጀ የታክስ አስተዳደር ስርዓት | 52,666,670.00 | 52,666,670.00 | - | - |
| 5.2 | የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች | 788,984,418.00 | 788,984,418.00 | 685,145,097.71 | 86.84 |
| **ጠቅላላ ድምር** | | **4,580,857,098.89** | **4,580,857,098.89** | **4,297,864,699.52** | **93.82** |

በሌላ በኩል ለመደበኛ በጀት ብር 100,064,488.56 እና ለካፒታል ፕሮጀክት ብር 178,878,316.40 በድምሩ ብር 278,942,804.96 ለቅድመ ክፍያ ተከፍሏል፡፡ ከዚህ አኳያ የበጀት አፈጻጸሙ የመደበኛ በጀት አፈጻጸም ጥቅም ላይ ከዋለው አንጻር 96.62 በመቶ የተፈጸመ ሲሆን አፈጻጸሙ ቅድመ ክፍያን ጨምሮ 99.29 በመቶ ነው፡፡ የካፒታል ፕሮጀክት አፈጻጸም ጥቅም ላይ ከዋለው አንጻር 81.40 በመቶ የተፈጸመ ሲሆን አፈጻጸሙ ቅድመ ክፍያን ጨምሮ 102.66 በመቶ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ስራ ተሰርቶ በአማካሪ ድርጅቱ የክፍያ ሰርተፍኬት ቀርቦ በበጀት እጥረት ሳይከፈል የዞረ 431.19 ሚሊዮን በግሬስ ፔሪድ እንዲከፈል ጥያቄ ለገንዘብ ሚኒስቴር ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 3 የጉምሩክ ኮሚሽን የ12 ወራት የበጀት አጠቃቀም በወጪ ሂሣብ መደቦች

| ተ. ቁ | ኘሮግራሞችና ኘሮጀክቶች | እስከ ሰኔ 30 ድረስ የተስተካከለ ዓመታዊ በጀት | የ12 ወራት የበጀት ዕቅድ | የ12 ወራት የበጀት ክንውን | የበጀት አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ስራ አመራር ፐሮግራም | 4,507,226,000.93 | 4,471,395,968.99 | 4,439,243,679.38 | 98.5 |
| 2 | የገቢ አሰባሰብ ፐሮግራም | 1,106,532,023.32 | 1,100,829,206.53 | 1,096,019,068.45 | 99.0 |
| 3 | የህግ ማስከበር ፐሮግራም | 679,626,138.58 | 670,991,855.77 | 669,646,151.01 | 98.5 |
| 3.1 | የታክስ ስወራና ማጭበርበር ተግባራትን መከላከል | 568,345,140.99 | 561,486,595.93 | 561,284,187.16 | 98.8 |
| 3.2 | የታክስ ፍትሀብሔር ጉዳዮችን ውጤታማ ማድረግ | 9,108,447.56 | 8,492,675.34 | 8,447,591.51 | 92.7 |
| 3.3 | በታክስና ቀረጥ ዙሪያ ለህብረተሰቡ ትምህርት መስጠት | 102,172,550.03 | 101,012,584.50 | 99,914,372.34 | 97.8 |
| **የመደበኛ በጀት ጠቅላላ ድምር** | | **6,293,384,162.83** | **6,243,217,031.29** | **6,204,908,898.84** | **98.6** |
| 4 | **የካፒታል ኘሮጀክቶች** | **1,451,610,771.51** | **1,415,147,676.84** | **1,377,879,156.46** | **94.9** |
| 4.1 | የኮንስትራክሽን ፐሮጀክቶች | 1,377,506,869.00 | 1,341,043,774.33 | 1,314,735,920.24 | 95.4 |
| 4.2 | ሲንግል ዊንዶ | 74,103,902.51 | 74,103,902.51 | 63,143,236.22 | 85.2 |
| **ጠቅላላ ድምር** | | **7,744,994,934.34** | **7,658,364,708.13** | **7,582,788,055.30** | **97.9** |

ሰንጠረዥ 4 የሃገር ውስጥ ታክስና የጉምሩክ ኮሚሽን የ12 ወራት የበጀት አጠቃቀም

| ተ. ቁ | በሴክተር እና በወጪ መደብ | የተስተካከለ ዓመታዊ በጀት | የ12 ወራት የበጀት ዕቅድ | የ12 ወራት በጀት ክንውን | አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሀገር ውስጥ | 3,739,206,010.89 | 3,739,206,010.89 | 3,612,719,601.81 | 96.62 |
| 2 | ጉምሩክ | 6,293,384,162.83 | 6,243,217,031.29 | 6,204,908,898.84 | 98.6 |
| **የመደበኛ በጀት ድምር** | | **10,032,590,173.72** | **9,982,423,042.18** | **9,817,628,500.65** | **98.35** |
| 1 | ሀገር ውስጥ | 841,651,088.00 | 841,651,088.00 | 685,145,097.71 | 81.4 |
| 2 | ጉምሩክ | 1,451,610,771.51 | 1,415,147,676.84 | 1,377,879,156.46 | 94.9 |
| **ካፒታል ድምር** | | **2,293,261,859.51** | **2,256,798,764.84** | **2,063,024,254.17** | **89.96** |
| **ጠቅላላ የበጀት ድምር** | | **12,325,852,033.23** | **12,239,221,807.02** | **11,880,652,754.82** | **97.07** |

### ➲ የውስጥ ኦዲት ስራዎች አፈጻጸም

በሀገር ውስጥ ታክስ በዋና መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች በፌደራል ዋና ኦዲተር ግኝቶች ላይ ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ ሪፖርት የማቅረብ ስራዎች አፈጻጸም ከ2008 እስከ 2014 በጀት ዓመት በዋናው መ/ቤት እና በአስራ ሁለት ቅ/ጽ/ቤቶች ተመዝግቦ ከሚገኝ በድምሩ ብር 13,280,552,016.34 በቁጥር 258 ግኝት ውስጥ ሙሉ በሙሉ 64፣ በከፊል 46 ግኝቶች ላይ ማስተካከያ ተደርጎ በድምሩ ብር 4,297,107,803.68 ማስተካከያ ተደርጎ ሪፖርት ወጪ ሆኖ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር፣ ለገንዘብ ሚኒስቴር፣ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለፕላን በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ለመንግስት ወጭ አስተዳደር ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እና ለሚንስትር ጽ/ቤት ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 5 የኋላ ዘመናት የፌዴራል ኦዲት ግኝት ማስተካከያ አፈጻጸም

| ተ.ቁ | የእርምጃ አወሳሰድ | እርምጃ የተወሰደበት የገንዘብ መጠን በብር |
|---|---|---|
| 1 | በገንዘብ የተሰበሰቡ | 209,207,042.52 |
| 2 | በመመሪያ ቁጥር 137/2010 መቀጫው የተነሳ | 29,293,874.55 |
| 3 | በመመሪያ ቁጥር 64/2012 የተሰረዘ | 19,772,986.60 |
| 4 | ሰነድ አቅርበው የተካካሰ | 16,823,280.28 |
| 5 | ያላሳወቁት ገቢ እንደሌለ በታክስ ኦዲት የተረጋገጠ | 15,278,688.38 |
| 6 | በፌዴራል ኦዲተር ከግኝት የተቀናነሰ | 3,749,212,743.03 |
| 7 | በታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት የተሻረ | 402,822.22 |
| 8 | የሂሳብ ምዝገባ ማስተካከያ የተደረገለት | 21,486.46 |
| 9 | ውል ስምምነቱ ተሻሽሎ ዜሮ የተወሰነ | 15,776,925.24 |
| 10 | በተመላሽ የተወሰነ | 540,766.74 |
| 11 | ወደ አዲስ አበባ ገቢዎች የተዘዋወረ የጡረታና የሥራ ግብር | 220,208,858.48 |
| 12 | ውል ስምምነት ገብተው በመክፈላቸው ከግኝት የወጣ | 3,332,326.09 |
| 13 | ከተመላሽ የተካካሰ | 17,236,003.09 |
| **ድምር** | | **4,297,107,803.68** |

**የውስጥ ኦዲት ግኝት ማስተካከያ ሥራዎች አፈጻጸም፡-** የ2015 በጀት ዓመት 4ኛ፣ የ2016 በጀት ዓመት 1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ሩብ አመታት ከግዥና ፋይናንስ፣ ከንብረት አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት፣ ከሰው ሃብት፣ ከገቢ ሂሳቦች አስተዳደር፣ ከታክስ ኦዲት እና ከታክስ ማጭበርበርና ምርመራ

ዳይሬክቶሬቶች ተመዝግቦ ከሚገኝ በድምሩ ብር 1,703,109,694.65 በቁጥር 142 ግኝቶች ውስጥ የክትትል ሥራ በመስራት የቀረቡ ምላሾችን ትክክኛነት በማረጋገጥና ምዝገባ በማከናወን ሙሉ በሙሉ 44 ግኝቶች በድምሩ ብር 1,421,813,556.76 ማስተካከያ ተደርጎ ሪፖርት ወጪ ሆኖ ለገንዘብ ሚኒስቴር፣ ለሚኒስትር ጽ/ቤት እና ለተቋማዊ አቅምና ድጋፍ ጽ/ቤት ቀርቧል፤

**የ2015 በጀት ዓመት የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ግኝትን አፈጻጸምን በተመለከተ:-**

| ተ.ቁ | የቅ/ጽ/ቤቱ ስም | የቅ/ጽ/ቤቶች ረቂቅ የሥራ አመራር ሪፓርት ላይ በግኝት የተያዘ | የቅ/ጽ/ቤት የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፓርት ላይ በግኝት የተያዘ | የሚኒስቴር መ/ቤቱ የተጠቃለለ ረቂቅ የኦዲት ሪፓርት ላይ በግኝት የተያዘ | ከረቂቅ ሪፓርት እስከ ማጠቃለያ ሪፓርት የተደረገ መስተካከያ | የሚኒስቴር መ/ቤቱ የተጠቃለለ የመጨረሻ የኦዲት ሪፓርት ላይ በግኝት የተያዘ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ | 4,621,046,421.09 | 4,129,598,289.20 | 4,195,484,794.54 | 449,948,707.16 | 4,171,097,713.93 |
| 2 | መካከለኛ ቁ.1 | 11,919,666,216.09 | 975,832,389.62 | 1,186,069,132.99 | 10,852,760,241.14 | 1,066,905,974.95 |
| 3 | መካከለኛ ቁ.2 | | | 1,140,297,455.51 | -1,140,297,455.51 | 1,140,297,455.51 |
| 4 | ምዕራብ አ/አ | 2,790,723,322.32 | 1,883,405,618.39 | 1,882,564,702.61 | 2,133,107,995.21 | 657,615,327.11 |
| 5 | ምስራቅ አ/አ/ | 1,900,763,971.81 | 1,587,293,344.31 | 1,577,902,586.65 | 1,303,235,328.01 | 597,528,643.80 |
| 6 | ሰሜን ምዕራብ | 609,190,501.17 | 546,063,381.75 | 537,847,219.35 | 297,462,319.66 | 311,728,181.51 |
| 7 | አዳማ ቅ/ጽ/ቤት | 184,915,362.71 | 174,310,694.37 | 179,257,878.71 | 73,195,024.68 | 111,720,338.03 |
| 8 | ድሬዳዋ | 158,682,470.64 | 66,811,503.89 | 62,265,887.07 | 108,082,043.91 | 50,600,426.73 |
| 9 | ሃዋሳ | 835,178,015.16 | 833,267,999.42 | 830,432,695.19 | 818,008,874.09 | 17,169,141.07 |
| 10 | ጅማ | 518,798,669.76 | 86,418,934.32 | 173,220,916.83 | 374,453,196.45 | 144,345,473.31 |
| 11 | ዋና መ/ቤት | 627,331,849.89 | 1,876,176,398.69 | 1,872,700,877.69 | 602,971,640.75 | 24,360,209.14 |
| ጠ/ድምር | | 24,166,296,800.64 | 12,159,178,553.96 | 13,638,044,147.14 | 15,872,927,915.55 | 8,293,368,885.09 |

**የጉምሩክ ኮሚሽን የኦዲት ግኝት ማስተካከያ ስራዎች አፈፃፀም:-** በበጀት ዓመቱ ነቀፌታ ያለበት የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት እና የውስጥ ኦዲት ግኝት ያለበትን መጠን በመቀነስ ወደ 12 በመቶ ለማድረስ ወይም በብር 6,521,862,530.76 ላይ የማስተካከያ እርምጃ ለመዉሰድ ታቅዶ በብር 1,147,987,036.72 ወይም 17.60 በመቶ ላይ የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ ተችሏል። ስለሆነም ነቀፌታ ያለበት የኦዲት ግኝት ብር 5,373,875,494.04 ወይም 82.40 በመቶ በመሆኑ የዕቅድ አፈፃፀሙ 14.56 በመቶ ሊሆን ችሏል።እስከ 2014 በጀት ዓመት ማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደበት አጠቃላይ የፌደራል ኦዲት ግኝት ብዛት 161፣ በገንዘብ ብር 7.39 ቢሊዮን ሲሆን፣ በ12 ወሩ ማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ የታቀደው ግኝት በገንዘብ ብር 6.51 ቢሊዮን ውስጥ ብር 1.13 ቢሊዮን ወይም 17.40 በመቶ የማስተካከያ እርምጃ ተወስዷል። እርምጃ ያልተወሰደበት ብር 6,259 ሚሊዮን ወደ ቀጣይ ዞሯል።

የውስጥ ኦዲት ግኝት ማስተካከያ እርምጃን በተመለከተ ከ2011 እስከ 2014 በጀት ዓመት ብዛታቸው 141 የኦዲት ግኝቶች በገንዘብ ብር 17.28 ሚሊዮን ነው፤ከዚህ ውስጥ በ12 ወራት ማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ የታቀደው በ15.21 ሚሊዮን ብር ግኝት ላይ ሲሆን፣ እርምጃ የተወሰደው በ13.43 ሚሊዮን ብር ላይ በመሆኑ አፈጻጸሙ 88.30 በመቶ ሊሆን ችሏል። እርምጃ ያልተወሰደበት ብር 3.85 ሚሊዮን ወደ ቀጣይ ዞሯል።

**የሀገር ውስጥ ታክስ የንብረት አስተዳደር አፈጻጸም፡-** ከየሥራ ክፍሎቹ በሚቀርቡ ጥያቄዎች መሰረት ግዥዎች በወቅቱና በጥራት ተፈጽመው የሥራ ግብዓቶች እንዲቀርቡ ተደርጓል፣ በተለያየ ዓይነትና መጠን የሚገለጹ በግዥ የቀረቡ እና ተመላሽ የተደረጉ ቋሚ ዕቃዎች በአግባቡ ገቢ እና ወጪ በማድረግ ለሥራ ክፍሎች እና ቅ/ጽ/ቤቶች በድጋፍ መልክ በማሰራጨት ለገቢ አሰባሰቡ ምቹ ሁኔታን የመፍጠር ሥራ ተሰርቷል። ከስራ ክፍሎች የቀረቡ ጥያቆዎችን መሰረት በማድረግ የጥገናና ገጠማ ስራዎችን በማከናወን ንብረቶች በአግባቡ ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ፣ በተለያየ ደረጃ የተበላሹ ተሽከርካሪዎችን በተቋም ጋራዥ፣ በግል ጋራዥ፣ በካምፓኒ እና በኢንሹራንስ እንዲጠገኑ በማድረግ ለገቢ አሰባሰቡ ምቹ ሁኔታን የመፍጠር ስራ ተሰርቷል። በተቋም ጋራዥ በተደረጉ ጥገናዎች በውጪ ገራዥ ቢጠገኑ ይወጣ የነበረውን ወጪ ለመቀነስ ጥረት ተደርጓል።

በበጀት ዓመቱ ወጪን ከመቀነስ አንጻር ሁለገብ የጥገና አገልግሎት በመስጠት ብር 2,750,000 ለማዳን ታቅዶ 3,174 የጥገና አገልግሎት በመስጠት ብር 6,260,000.00 ማዳን ተችሏል።የተሽከርካሪ ጥገናን በተመለከተ በውስጥ አቅም የጥገና አገልግሎቶችን በመስጠት ብር 1,500,000.00 ለማዳን ታቅዶ ብር 1,414,565.35 (94.3%) ማከናወን ተችሏል። በጨረታ የተወገዱ ተሽከርካሪዎች፣ሞተር ሳይክሎችና ሊፍቶች ሽያጭን በተመለከተ ብር 4,451,421.6 በመሸጥ ገቢ ተገኝቷል። ለመ/ቤቱ አገልግሎት እንደማይሰጡ በባለሙያ ማረጋገጫ የተሰጠባቸው ከህንጻ "ሐ" ግንባታ ጋር ተያይዞ የተነሱ የቢሮ መገልገያዎች እና በምድረ-ግቢ ግንባታ ምክንያት የተነሱ ኮብል ስቶንና ድንጋይ፣ ተመላሽ የተደረጉ መለዋወጫች፣ ጎማዎች፣ኮንቲነሮች፣ ቆርቆሮች፣ አልባሳትና የመሳሰሉ ንብረቶችን ለተለያዩ ተቋማት እና በጎ አድራጎት ድርጅቶች ብር 16,834,792.63 የሆኑ በስጦታ የማስወገድ ሥራ ተሰርቷል።

**የኮሚሽኑ ንብረት አስተዳደር አፈጻጸም፡-** በ12 ወራት ዉስጥ ለመንግስት አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ብዛታቸው 12,137 የሚሆኑ ግምታዊ ዋጋቸዉ ብር 14.83 ሚሊዮን የሚገመቱ የተለያዩ ንብረቶች ተለይተዉ ተወግደዋል። በግብዓት አቅርቦት ዙሪያ ቅ/ጽ/ቤቶችን ለመደገፍ በተደረገው ጥረት በብር 394,211,657.37 የሚገመቱ 15,507 የተለያዩ ቋሚና አላቂ እቃዎች እንዲሰራጩ ተደርጓል። ከብልሽት በፊት ንብረቶችን የቅድመ ብልሽት እንክብካቤ (Preventive Maintainance) በማድረግ ለተለያዩ የቢሮ ንብረቶች፣ ኤሌክትሮኒክ ዕቃዎች፣ ጀኔሬተሮች፣ የፍሳሽ መስመሮች፣ የቧንቧ መስመሮች፣ የህንጻ ክፍሎችና ተገጣጣሚዎች ጥገና እና ለተሽከርካሪዎች ቴክኒክ ምርመራ በማድረግ በአጠቃላይ ለ1,848 ዕቃዎች በተቋሙ ባለሙያዎች ቅድመ ጥገና በመከናወኑ ብር 27,032,150.00 ሊያስወጣ የሚችል ብልሽትን ማዳን ተችሏል። እንዲሁም 3,614 የተለያዩ ንብረቶች ተሽከርካሪን ጨምሮ የተበላሹ ንብረቶችን በኮሚሽኑ ባለሙያዎች በመጠገን ብር 44,141,150.00 ወጪ ማዳን ተችሏል፤ በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ የንብረት አያያዝ በማሻሻል የጥገና ወጪዎችን በ169.01 ሚሊዮን ብር ለመቀነስ ታቅዶ የንብረቶች ጥገናና ቅድመ ብልሽት ጥገና በማድረግ 71.17 ሚሊዮን ብር በማዳን የእቅዱን 42.11% የጥገና ወጪ መቀነስ ተችሏል።

## 2.4 የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አሰራርንና ውጤታማነት ስራዎች አፈጻጸም

### ➲ ለነባርና አዲስ ቴክኖሎጂዎች የኮንፊግሬሽንና ኢንስታሌሽን ሥራ ማከናወን

- የኢ-ታክስ ትሬኒንግ ማሽኖችና GPRS ሰርቨር ማሽን ላይ የነበሩ ፍሪዝ የማድረግና ተያያዥ ችግሮች ከአሮጌው ሰርቨር ወደ አዲስ ሰርቨር የማሸጋገር ስራ ተሰርቷል፣
- የሲግታስ ዳታቤዝ ባካፕ የሚወሰድበትን ጊዜ እና የሚወሰደውን የባካፕ አይነት በአዲስ መልክ በመከለስ Full backup, Incremental Backup, Archive log backup እና Cumulative Backup እንዲወሰድ ተደርጎ ኮንፊገር የማድረግ ስራ ተሰርቷል፣
- የEtax Application የተጫነባቸውን ሰርቨሮች ከweblogic server(version:10.3.5.0) ወደ weblogic server (version:12.2.1.4.0) አፕግሬድ ለማድረግ የሚያስችል የሙከራ ስራ Etax Training application server ላይ ተሰርቷል፣
- የኤክስቼንጅ ሜል ሰርቨር ላይ የነበሩ ችግሮች በዘላቂነት እንዲፈቱ ተደርጓል፣
- ለባክአፕ የሚያገለግል የVPN መስመር በኢንሳ እና በሚኒስትር መ/ቤቱ በኩል ተዘርግቶ ቀሪዎቹ አስፈላጊ የኮንፊገሬሽን ስራዎችን የማከናወንና ባክአፕ ለመያዝ የሚያስፈልጉ ስራዎች በሂደት ላይ ይገኛሉ፣
- ለምስራቅ እና ለመካከለኛ ቁጥር-1 ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት ቢሮ ማደራጀት እና አዲስ የኔትዎርክ ዝርጋታ ሥራ ላይ አስፈላጊውን ድጋፍ የማድረግና የኔትዎርክ ዝርጋታ የሚያስፈልጉ ስዊቾችን የማዘጋጀት እና የኮንፊግሬሽን ስራ ተሰርቷል።
- የምዕራብ አ/አ/አ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት የመጠባበቂያ ዳታ መስመር (BackUp) ስራ ላይ ለማዋል አዲስ Layer 3 ስዊች ላይ የቢጂፒ ኮንፊግሬሽን ተሰርቶ ስራ እንዲጀምር ተደርጓል፣
- ለሀዋሳ እና ለኮምቦልቻ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት Antivirus system ችግር በማጋጠሙ ምክንያት ለሁለቱም ቅ/ጽ/ቤቶች እንደ አዲስ Redeploy ተደርጓል፣ ለአዳማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ደግሞ የኮንፊገሬሽን ስራ ተሰርቷል፣
- ለአዋሽ ጉምሩክ የባለ 48-Port Switch ኮንፊገር ተደርጎ ተሰጥቷል።
- ለDigital Signage Solutions ሰርቨር ተዘጋጅቶ አስፈላጊው የኮንፊገሬሽን ስራ ተከናውኗል።
- ጉምሩክ ኮሚሽን በጠየቀተ መሰረት የFTP SERVER ተዘጋጅቶ አስፈላጊው የኮንፊገሬሽን ስራ ተከናውኗል።
- ለገቢዎች ዳታ ቤዝ ክፍል፣ ለሦፍት ዌር ፣ ለኔትወርክ፣ ለሴኩሪቲ እና ለጉምሩክ ዳታቤዝ ቡድኖች ሙያዊ ድጋፍ ተደርጓል።
- በዩ.ኤስ.አይ ባለሙያዎች ሙሉ የሳንስዊች የሌብል ስራ እንዲሰራ ተደረጓል።
- ግብር ከፋዮች ደረሰኝ በኢፒደመንት በኩል የሚልኩበት ተቋርጦ በዳታ ማዕከል ሲስተም አስተዳደር እና በዳታቤዝ ቡድን በጋራ በመሆን ተፈቷል።
- ለመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት የሚሆን አንድ ሰርቨር በቀረበው ጥያቄ መሰረት ለጽ/ቤቱ እንዲሰጠጥ ተደርጓል።
- የአዳማ እና ሃዋሳ ቅ/ጽ/ቤት አዲስ ህንፃዎች ግንባታ ስራ የደረሰበትን ደረጃ በመስክ በመገኘት ጉብኝት ተደርጎ ከቴክኖሎጂ አንፃር በተለይ የኔትዎርክ ዝርጋታው ላይ ምክረ ሃሳብ ተሰጥቶበታል።
- ሁሉንም የግብር አይነቶች የማሳወቂ እና የመክፈያ ጊዜን ወደ ሲስተም ኮንፊገር ተደርጎል፣

- 53 አዳዲስ የታክስ ማዕከላት ተፍጥረዋል፤
- የትግራይ ክልል አዲስ የዞንና የወረዳ አወቃቀር፣ ለኦሮሚያ ክልል ሸገር ከተማ አዲስ አወቃቀር፣ ለማዕከላዊ ኢትዮጵያ ዞንና ወረዳ የስም ማስተካከያ፣ ለደቡብ ኢትዮጵያ የዞንና የወረዳ መዋቅር ተስርቷል፡፡
- ለሜክሲኮ መረጃ ማዕከል ዳታ ሴንተር እና ፓወር ክፍል የበር አዲስ አክሰስ ኮንትሮለር እንዲገጠም ተደርጓል፡፡
- ለኤቪአር ኢንስታሌሽን የሚሆን የኤሌክትሪክ ገመድ ዝርጋታ እንዲጠናቀቅ ተደርጓል፡፡
- የሲዳማ ክልል 13፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የ44፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል 52 እና ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የተላከ የ34 ታክስ ማዕከላትና በባንክ አካዉንት እና በቴሌብር ክፍያ መክፍል እንዲችሉ እያንዳንዱን ታክስ ሴንተር ኮንፊገር የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡
- የሲንግል ዊንዶ መረጃ ማዕከልን እንደዋና መረጃ ማዕከል ከሚያስፈልጉት በዋነኛነት የኔትወርክ ዝርጋታ ሲሆን የቴሌ ብሮድባንድ መስመሮችን ከህንጻ ሀ ወደ ህንጻ መ ለማዞር ጥያቄ ለኢትዮ ቴሌኮም ቀርቦ በባለሙያዎች ታይቶ የዳክት ሲስተም እነደ አዲስ ለመስራትና መስመሩን ለማዞር በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

የዳታ ማዕከል መሰረተ ልማት ጥገናና ደህንነት ክትትል ከማድረግ፣ የመጠባበቂያ ዳታ ማዕከል ምስረታ አስቻይ ሥራዎችን ከማከናወን፣ አዲስ ለሚመሰረቱ ስርዓቶች እና ከ3ኛ ወገን ለሚሰበሰቡ የተለያዩ መረጃዎች የመረጃ ቋት ከማደራጀት አኳያ የሚከተሉት ተግባራት ተከናዉነዋል፡፡

- በዳታ ማዕከል ያሉ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት መሣሪያዎች እንደ Storage and Servers, Uninterrupted Power Supply (UPS), Air Conditioner (AC), Core Switches, Routers, Telecom apparatus, Electric Installation እና የመሳሰሉ የመገናኛ መሣሪያዎች እንዲሁም የዳታቤዝ፣ የአፕሊኬሽን፣ ኤዲና ዲኤንኤስ(Active Directory/AD & Domain Name/DNS)፤ የደህንነትና የመገናኛ መሳሪያዎች የማስተዳደር፣ ደህንነቱን የመከታተል ሥራ፣ መደበኛ ጥገናና አጠቃላይ የዳታ ማዕከሉን መሳሪያዎች በተገቢው ሁኔታ ሥራ መስራታቸውን የመከታተል ስራ ተሰርቷል፣
- በየቀኑና በየሳምነቱ የሚወሰዱትን የሲግታስ፣ የአሻራ ዳታቤዝ፣ የኢፔይመንትና የናሽናል አይዲ ስቴጂንግ ዳታቤዝ እና የታስ ዳታቤዝ መጠባበቂያ(Backup) የመከታተል ስራ ተሰርቷል፣
- ከኢንሳ እና ሚንት በተጠየቀው መሰረት የዳታ ማእከሉን የInfrastructure አሁናዊ ሁኔታ የሚያሳይ መረጃ ተዘጋጅቶ ተልኳል፣
- የተበላሹ 15 የኔታፕ ስቶሬጅ ዲስኮች በአዲስ ተቀይረው ወደ ስራ እንዲገቡ ሲደረግ፣ ቀድመው በድጋፍ ሰጪው ዩኤስአይ(USI) ድርጅት መተካት የነበረባቸው 10 የኔትአፕ እና 1 የኤችፒ ዲስክ ተተክተው ስራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፣
- የዳታ ቤዞችንና የአፕልኬሽኖችን የቦታ (Space) አጠቃቀምን የማጥናትና የማስተካከያ ስራ ተሰርቷል፡፡ እንዲሁም ሌብል(Label) ያልተደረጉ ሰርቨሮች በቂ ምልክት እንዲኖራቸው ተደርጓል፣
- ዋና ዋና የገቢዎችና የጉምሩክ ዳታቤዝ መረጃዎች ለጥንቃቄ ሲባል በቴፕ ባክአፕ እንዲያዙ ተደርጓል፣

- በመረጃ ማእከል ዉስጥ ያሉትን የሲ.ሲ. ቲቪ. ካሜራዎች የፌርምዌር አፕዴት የማድረግ ስራ ተከናውኗል፣
- አሮጌው ሳንስዊች እና ከእሱ ጋር ተዘርግተው የነበሩ የፋይበር ቻናል ኬብሎችን የመተካት ስራ ተሰርቷል፣
- የቆዩ ሎጎችን(Log files) በማስወገድ አላግባብ የተያዙ ቦታዎችን የማስለቀቅና በአዲስ መልኩ የመጠቀም ስራ ተሰርቷል፣
- የሲግታስ፣ የኢታክስ እና የአሻራ ዳታቤዞችና አፕልኬሽን ሰርቨር አክሰስ ሎግና ትሬስ ፋይሎችን የመፈተሽ ስራ ተሰርቷል፣
- የሲግታስን መጠባበቂያ ዳታቤዝ (SIGTAS STANDBY Database) የመከታተልና የማስተዳደር ስራ ተሰርቷል።
- የሲግታስ ዳታቤዝ ባካፕ የሚወሰድበትን ጊዜ እና የሚወሰደውን የባካፕ አይነት በአዲስ መልክ በመከለስ Full backup, Incremental Backup, Archive log backup እና Cumulative Backup እንዲወስድ ተደርጎ ኮንፊገር የማድረግ ስራ ተሰርቷል።
- የሲስተም መቆራረጥ እንዳያጋጥም ከስራ ሰዓት ውጭ እንዲሁም ቅዳሜና እሁድንም ጭምር የዳታ ሴንተርና የፓወር ክፍል ክትትል እየተደረገ ይገኛል።
- የገቢዎች እና የጉምሩክ የባክአፕ ፋይል ወደ ቴፕ እንዲዘዋወር በጠየቁት መሰረት ስራው ተከናውኗል፤
- የTWM Server ላይ የነበረ ከ20Tb በላይ Custom ECMS ዴታ ቤዝ መረጃ ወደ ቴፕ ላይብራሪ ባክ አፕ ተይዟል።
- በገቢዎች ሚኒስቴርና በጉምሩክ ኮሚሽን ዋ/መ/ቤት ስቶር ውስጥ በችግር ምክንያት ተመላሽ የሆኑትን ኮምፒውተሮች፣ ፕሪንተሮች፣ ላፕቶፖች፣ ሰርቨሮች እንዲሁም የኔትወርክ እቃዎችን ድጋሚ ወደ አገልግሎት እዲገቡ እና መወገድ ያለባቸዉን የመለየት ስራ ተሰርቷል።

የመረጃ ደህንነት ፓሊሲዎች ተግባራዊ ማድረግ እና ቀድመው በውስጥ አቅም የለሙ የITSM, Letter Management, የመሳሰሉትን በማሻሻል ወደ Enterprise Resource Planning(ERP) እና Electronic Document Management System(EDMS)ን Customise በማድረግ ወረቀት አልባ አሰራር ከመተግበር አኳያ የተፈጸሙ ስራዎች ናቸዉ።

## የደብዳቤ መጻጻፊያ (Letter Management)

- የተቋሙን ሥራዎችን በወረቀት አልባ ስርዓት ከማስደገፍ አንጻር እንደ ጉምሩክ ኮሚሽን በገቢዎች ሚኒስቴር ሥራውን ለማስጀመር አቅጣጫ በመሰጠቱ አስፈላጊው ስልጠና ቀድሞ የተሰጠ ሲሆን ቀሪ የድጋፍ ስራዎች በመከናወን ላይ ናቸው።
- የደብዳቤ መጻጻፊያ ሲስተም ላይ የSearch ማድረጊያ የተሰራ ሲሆን፤ ተጨማሪ ማሻሻያዎች እየተሰሩ ናቸው።
- (Bulk letter, Email integartation etc...)
- የሌተር ማኔጅመንት ሲስተም ወደ ጉምሩክ ማስተላለፍ ስራ አስፈላጊውን ድጋፍ ተደረጓል።

## ኢ.አር.ፒ. እና ኢ.ዲ.ኤም.ኤስ.(ERP እና EDMS)

- እነዚህን ሁለት ትላልቅ የተቋም አስተዳደራዊ ስርዓቶች ሙሉ በሙሉ ለመተግበር እንዲቻል ከአለም ባንክ እና መሰል ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች ጋር ምክክር፣ የፍላጎት መግለጫ እና አስፈላጊ የቴክኖሎጂ መሣሪያዎች ዝርዝር እስፔሲፊኬሽን ቀርቧል።

ነባር ለሆኑ የዶመስቲክ ኮር ሲስተሞችን ከማሻሻል፣ አፕሊኬሽን ሲስተሞቹን ስታብላይዝ አድርጎ ከማስቀጠል አንጻር በኢሹ ሊስት ለተመዘገቡት እንደ ቅደም ተከተላቸው አቶሜት ከማድረግ አኳያ የሚከተሉት ተግባራት ተፈጽመዋል።

- የፋይዳ(FAYDA) ሲስተምን ከTIN/SIGTAS እና አሻራ ሲስተም ጋር ለማቀናጀት የሚያስችል አፕልኬሽን በማልማት እና በሲግታስ ፎርም ላይ ተገቢውን ማሻሻያ በማድረግ የሙከራ ሥራው ተጠናቆ፣ ሲግታስ ፕሮዳክሽን ዳታቤዝ እና አፕልኬሽን ሰርቨር ላይ ኮንፊገር እና ዲፕሎይ ተደርጓል። በመቀጠልም በአዲስ አበባ ገቢዎች የቦሌ ክ/ከ/አ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት የፓይለት ትግበራ በማከናወን በሁሉም የከተማ እና ክልል ገቢዎች ከጥቅምት ወር 2016 ጀምሮ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሆኗል።
- አዲሱ የግብር ከፋይ መለያ (TIN) ምዝገባ የአሰራር ስርአት ከፋይዳ(Digital Identification system/Fayda) ጋር ተቀናጅቶ እንዲተገበር በተቀናጀ የታክስ አስተዳደር ስርአት(SIGTAS) ላይ ማሻሻያዎች ተደርገዋል።
- ሲግታስ(SIGTAS Home Page) ላይ የTIN አመዘጋገብ መመሪያ የሚያሳውቅ ማሻሻያ ተደርጓል።
- በሲግታስ ላይ የተደረጉ ተጨማሪ ማሻሻያ እና ማስተካከያዎችን በተመለከተ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ እና የደቡብ ኢትዮጵያ የክልሉ ታክስ ማዕከል በአዲስ መልክ የተከፈተ ሲሆን፤ የደቡብ ኢትዮጵያ እና ማዕከላዊ ኢትዮጵያ የዞን እና ወረዳ ማዕከላት በተመሳሳይ በሲግታስ ስርዓት ላይ እንዲከፈቱ ሆኗል።
- በኦሮሚያ ገቢዎች ቢሮ ስር ለሚገኙ የምስራቅ ቦረና ዞን 3 ወረዳዎች በሲግታስ ስርዓት ላይ ተከፍተዋል።
- ከፌደራል ታክስ ማዕከላት ወደ አዲስ አበባ የስራ ግብር አካውን የተዛወረላቸው የሚያዩበት ሪፖርት ለምቷል።
- Schedule c mining (የማዕድን ግብር ) ግብር ከፋዮች በኢትዮጵያ(E.C) ማሳወቂያ ተሰርቶለታል።

ነባር ለሆኑ የኮርፖሬት አገልግሎት የሶፍትዌር ፕሮግራሞች ተገቢውን ማሻሻያ ከማድረግ አኳያ፦

- የገቢዎች ዋናው መስሪያ ቤት የሰው ሃብት ሲስተም ላይ የተደረገ ማሻሻያ በተመለከተ ማኔጀሪያል ሪፖርት ቅርንጫፎችን እንዲያሳይ ማስተካከያ ማድረግ ፣ ተደጋግመው የነበሩ ዳታዎች (Dublicate) ፣ የትምህርት፣ የትውልድ ቀን ፣ የስራ ልምድ ፣ በስትራክቸር ለውጥ ምክንያት የተሰረዙትን ፣ በስህተት የተመዘገበ መረጃዎችን ማስተካከል እና እስትራክቸር (Split, Merge, close etc.) ማሻሻያ ስራ ተከናውኗል።
- ለሰው ሃብት ዳይሬክቶሬት የባዮሚትሪክ አቴንዳንስ ሲስተም ላይ አስፈላጊውን UAT ሪፖርት ተዘጋጅቶ ተልኳል።

- የጉምሩክ ኮሚሽን የሰው ሃብት ሲስተም የተደረገ ማሻሻያን በተመለከተ User-friendly፣ interface amendment ፣ Performance issues ፣ Change of structure (move, close structure, and position)፣Termination restore Enable and disable user access እና የመሳሰሉ ተጨማሪ ማሻሻያዎች ተደርገዋል፡፡

በተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎቶችን አቶሜት ለማድረግ አዲስ ጥናት የተደረገባቸውና በአዲስ መልክ የሚበለጽጉ ሶፍትዌር ፕሮግራሞችን ማልማት፣ እንዲሁም በፕሮጀክት ለተያዙት ስርዓቶች (የITAS, eInvoice, DW & BI) አስፈላጊውን ድጋፍ ከማድረግ አኳያ፡-

- በተቋሙ በተያዘው የገቢ ማሳደጊያ ዕቅድ መሰረት ደረሰኝ የመቀበል ባህልን ለማሳደግና የገቢ አሰባሰቡን ለማሳደግ በሚያስችል መልኩ በማዕከሉ ባለሙያዎች የሎተሪ ማውጫ (Lottery Draw System) ስርዓት ለምቶ በፍተሻ ላይ ይገኛል፡፡
- በሰው ሃብት ለሚተዳደረው የባዮሜትሪክ አቴንዳንስ ሲስተም ላይ አስፈላጊው የቴክኒክ ድጋፍ ተደርጓል፣
- ለተቋሙ ሰራተኞች የብድር እና ቁጠባ የሲስተም ግዢ ቴክኒካል ሰነድ ማዘጋጀት እና ግምገማ ላይ አስፈላጊው ድጋፍ ተደርጓል፣
- የወጪ መጋራት (Cost sharing) ሲስተም የማስተካከያ ስራዎች ድጋፍ ተደረጓል፣
- በኤሌክትሮኒክስ ስርዓት(E-invoicing) የህግ ማዕቀፍ ዝግጅት አስፈላጊውን ድጋፍ ተደርጓል፣
- ለ e-invoicing project ዲፕሎይመንት ሰርቨሮችን የማዘጋጀትና አስፈላጊውን የፖርት፣ አይፒና ኔትወርክ ኮንፊገር በማድረግ ለፕሮጀክቱሰርቨሮቹን ዝግጁ የማድረግ ስራ ተከናውኗል፡፡
- E-Invoice, DW and BI ፕሮጀክቶች አስፈላጊው የቴክኒክ ግብዓትና ድጋፍ ተደርጓል፣
- የGPRS ሰርቨር ወይም የመረጃ ቋቱ ሲቋረጥ ዜድ ሪፖርት ዳታዎችን ወደ ዳታቤዝ ማስገባት ተችሏል፡፡
- ለብድር እና ቁጠባ የሲስተም ግዢ ቴክኒካል ሰነድ ማዘጋጀት እና በግምገማ በማከናውን ድጋፍ ተደርጎል፡፡

የሲስተሞች የኔትወርክና የሴኩሪቲ አገልግሎት ከማሻሻል አንጻር የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፡፡

- በመረጃ ቴክኖሎጂ ማዕከል በሲስተም አስተዳደር ለሚተዳደሩ ሲስተሞች የአድሚን ፕሪቭሌጅ የማጣራት ስራ በማከናወን ሙሉ በሙሉ የአድሚኒስትሬሽን የይለፍ ቃል እንዲቀየር ተደርጓል፣
- የክፍያ አገልግሎት የሚሰጡ የኔትወርክ ግንኙነቶችን የበለጠ ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆን እንዲችል ኮኔክሽኖቹ በፋየርዎል በኩል እንዲሆኑ የሙከራ ስራ እየተከናወነ ይገኛል፣
- ከዋ/መ/ቤትና ከቅ/ጽ/ቤቶች ያልተፈቀዱ ሳይቶችን በቪፒኤን በኩል በመጠቀም የሚሞክሩ የኢንተርኔት ተጠቃሚዎችን አገልግሎትን የማቋረጥ ስራ ተከናውኗል፣
- በገቢዎች ሚኒስቴር ዋናው መ/ቤት፣ በጉምሩክ ኮሚሽን ዋናው መ/ቤት እና ቅርንጫፍ መ/ቤቶች እንዲሁም በዋናው Data center ላይ ሊደርሱ ወይም ሊያጋጥሙ የሚችሉ ማናቸውንም የደህንነት ስጋቶች(Security threats) በተመለከተ በዋናው Data center ባሉት external እና internal firewall ላይ ክትትል ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በዋናው Data center ለሚገኘው የInternal firewall backup ተወስዷል፣

- የራንሰምዌር ቫይረስን (Ransom Ware Virus) ለመከላከል የሲስተም ፖሊሲዎችን የመፈተሽ እንዲሁም ሲስተሞችን አፕዴት የማድረግ ስራ፣ በቅ/ጽ/ቤት የሚገኙትንም አንቲቫይረስ ሰርቨር የሌላቸውን ሰርቨር የማዘጋጀት እና እንደ አዲስ የመጫን ስራ ተከናውኗል፣
- አጠቃላይ የጸረ-ቫይረስ ሲስተሞች ክትትል፣ የፋየርዎሎች ክትትል እንዲሁም የኔትወርክ ደህንነት ስራዎች የክትትል ስራዎች ተከናውኗል፣
- በመ/ቤቱ ያሉትን ኮምፒዩተሮችና ተዛማጅ የቴክኖሎጂ እቃዎች በተለያየ በኮሚሽኑ ኮምፒዩተሮች አንቲቫይረስ የተጫነባቸዉና ያልተጫነባቸዉን የመለየት እና የመጫን ስራ ተከናውኗል፣
- የኢታክስ፤የሲግታስ እና የኢፔይመንት አፕልኬሽን ሰርቪሶችን የመከታተል፤ሲቆሙ የማስነሳት ሥራ ተሰርቷል፡፡

**በሲግታስ/ኢክፍያ እና ኢፋይሊን (SIGTAS/eTax) ሲስተም ላይ የተደረጉ ማሻሻያዎችን በተመለከተ**

- የE-Payment Expnasion ማሻሻያን ተከትሎ ሰው በቀላሉ ውሳኔ ማሳወቂያን እየቀየረ ለብልሹ አሰራር ክፍተት ይፈጥር የነበረውን Modify Assessment በማስቀረት ማንኛውም ልዩነት ሲኖር Reassessment ብቻ በማድረግ ማን? መቼ? ለምን? እንደወሰነው በግልጽ ተጠያቂነት በሚያሳይ ሁኔታ ለምቷል፦
    - የተጨማሪ እሴት ታክስ የሽያጭ/የግዢ ልዩነት ሲኖር የታክስ ኦፊሰሮች ማስገባት አይችሉም ነበር አሁን ግን ተጨማሪ የግዢ ደረሰኝ እና የሽያጭ ደረሰኝ ልዩነት ሲኖር Reassessment በማድረግ መመዝገብ እንዲችሉ ተደርጓል
    - የክልሎች ወጪ መረጃ ማየት እና ማስተካከያ ማድረግ (በተለይ የክልሎች የጋራ ገቢ ላይ ) ተንጠልጣይ ሂሳብ (Suspense) ለማጥራት እና ከተለያዩ አካላት ለሚቀርቡ የመረጃ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት የሰራተኞች ወጪ ዝርዝር ላይ ማስተካከያ ሲኖር Reassessment በማድረግ መመዝገብ እንዲችሉ ተደርጓል
    - የስራ ግብር ማስታወቂያ የሰራተኞች ዝርዝር ላይ ማስተካከያ ሲኖር Reassessment በማድረግ መመዝገብ እንዲችሉ ተደርጓል
    - የቅድመ ግብር ክፍያ (Withholding tax) እና በገዥው የሚሰበሰብ የተጨማሪ እሴት ታክስ (Vat Withholding ) ላይ ማስተካከያ ሲኖር Reassessment በማድረግ መመዝገብ እንዲችሉ ተደርጓል
    - የሀብትና ዕዳ መግለጫ (Balance sheet) ላይ ማስተካከያ ሲኖር Reassessment በማድረግ መመዝገብ እንዲችሉ ተደርጓል፡፡
    - የኤክሳይዝ ታክስ ተጨማሪ የግዢ ደረሰኝ እና የሽያጭ ደረሰኝ ልዩነት ሲኖር Reassessment በማድረግ መመዝገብ እንዲችሉ ተደርጓል፡፡
    - የተጨማሪ እሴት ታክስ ክሬዲት እና ኢ-ክፍያዎች ከማስፋፊያ በኂላ ዝርዝር ተሰርቷል
    - የማስታወቂያ ጊዜው ከመድረሱ በፊት ወይም ማስታወቂያ ያልቀረበበት ክፍያ /Advance Payment/ ታክስ ከፋዩ መክፈል ቢፈልግ መክፈል ያስችላል፣
    - በታክስ ከፋዩ ሊከፈል የሚገባውን ክፍያ (ፍሬ ግብር ፣ ወለድና መቀጫ) አስልቶ እና ታክስ ከፋዩም ይህንን አይቶ ክፍያ እንዲፈጽም ያስችላል፣

- በኢ-ፋይሊንግም ሆነ በሲግታስ ላስታወቁ ግብር ከፋዮች ማንኛውም ውሳኔና የክፍያ ማረጋገጫ በSMS, ኢሜል እና ኢ-ፋይሊንግ message center (ኢ-ፋይል ለሚያደርጉ) መላክ፣
- በአንድ የሰነድ ቁጥር / Document No./ በከፊል ወይም ከአንድ ጊዜ በላይ መክፈል ያስችላል፣ከታክስ ውጪ የሆኑ ልዩ ልዩ አስተዳደራዊ መቀጮዎችንና ክፍያዎችን መክፈል ያስችላል ፣
- ዘግይተው የሚከፈሉ ክፍያዎች፣ የዕዳ ክፍያዎች፣ በኦዲት ግኝት የሚከፈሉ ክፍያዎችን ለማስተናገድ ያስችላል

**የኤሌክትሮኒክ ታክስ (E-Tax) አጠቃቀምን በተመለከተ፡-**

**በኢ-ፋይሊንግ ሲስተም ላይ ማሻሻያዎች ማድረግን በተመለከተ፦**

- በኢፋይሊንግ ሲስተም ላይ ለስርዓቱ ተጠቃሚዎች በድግግሞሽ TASS ላይም ማሳወቅ ሳይጠበቅባቸው አገልግሎቱን ያቀላጠፈ ወደ 9 ማሻሻያዎች ተካተው የለማው ስርዓት የሙከራ ስራ ተከናውኖ ተግባራዊ ሆኗል::
  - የተጨማሪ እሴት ታክስ ግዥ አፕሎድ ቀድሞ ካለው ፍጥነት እንዲጨምር ተሰርቷል::
  - የተጨማሪ እሴት ታክስ አፕሎድ ቴምፕሌት (ማሳወቂያ አባሪ) ኢ-ፋይሊንግ ላይ ተጭኗል፣
  - የሻት ሽያጭ (sales detail) ፎርም ተሰርቷል፣
  - የደሞዝ ገቢ ግብር የሰረተኞች ዝርዝር መረጃ አንድ በአንድ እንዲመዘግብ ማስቻልና የአፕሎድ ፍጥነትን ማሻሻያዎችን አድርጓል::
  - የዊዝሆልዲንግ ኦን ፔይመንት አፕሎድ ፍጥነትን ማሻሻያዎችን አድርጓል::
  - የግብር ማሳወቂያ ጊዜ ስደርስና ሲያልፍ አስፈላጊውን ማሳወቂያ በአጭር ሞባይል መልእክትና በኢሜይል መላክ ተሰርቷል፣
  - በኢፋይሊንግ ፖርታል ላይ ግብር ከፋዮች የሚገጥማቸውን ችግር መልእክት ለመላክ የሜሴጅ ሴንተር እንዲሰራ ማስቻልና አባሪ ዶክመንት እንዲቀበል ማሻሻያዎችን አድርጓል::
  - የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ያልሆኑ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ግዢን ሲፈፅሙ ዝርዝር የግብይት መረጃ መመዝገቢያ ፎርም ተሰርቷል፣
  - የተጨማሪ እሴት ታክስ ዝርዝር የግብይት መረጃ ሲገባ MRC ቁጥር ትክክል መሆኑን አረጋግጦ እንዲቀበል እንዲሁም በማሽን ያልተቆረጡ ደረሰኞች ለማስገባት ደግሞ M ከፊት በማድረግ እንዲያስገባ ተደርጎ ተሻሽሏል::
  - የጡረታ የንግድ አይነት ዝርዝር ማስገቢያ ፎርም ተሰርቷል
  - ማንኛውም ውሳኔ በመዝገብ ቤት በኩል ኤሌንትሮኒካሊ መድረስ የሚያስችል ስራ ተሰርቷል

- የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጲያ ክልል የቴምብር ቀረጥ ኮንፊገሬሽን ተሰርቷል፡፡

**በኢ-ፔይመንት ሲስተም ላይ ማሻሻያዎች ማድረግን በተመለከተ፡-**

- በኢ.ታክስ ፋይል ያደረጉ ግብር ከፋዮች በተመለከተ ወደ ደራሽ የሄዱ ፣በማንዋል የከፈሉ፣ ደራሽ ላይ ክፍያቸው የሚታይ ፣ በኢ-ክፍያ የከፈሉ እና መክፈል የሚገባቸው ሆነው ያልከፈሉትን የሚያሳይ ሪፖርት ለምቷል፤
- የአዲስ አበባ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ግብር ከፋዮቹ የኢ-ፔይመንት ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል የቴሌብር ሾርት ኮዶችን ከባንክ ሂሳብ ቁጥሮች ጋር የማስተሳሰር ስራ ሲግታስ እና ኢፔይመንት ስቴጅንግ ሲስተም ላይ ተሰርቷል
- በኢ.ፋይሊንግ ጊዜ ከሚከፈሉ ክፍያዎች ውጪ ያሉ የውዝፍ ክፍያ፣ የከፊል ክፍያ፣ የኦዲት ግኝትና የዕዳ ክፍያ፣ የቅድመ ክፍያ እና የመሳሰሉ የክፍያ ዓይነቶችን በተናጥልና በጥቅል ማስከፈል የሚያስችል የኢ-ክፍያ ማስፋፊያ አማራጭ/e-payment expansion: /የሲስተም ማልማት ስራው ተጠናቆ፣ እንዲሁም ፍተሻ ሙከራ ተከናውኖ ከጥር 01፣ 2016 ዓ.ም. ወደ ፕሮዳክሽን ገብቷል፡፡
- የኢፔይመንት ማስፋፊያ (Epayment partial payment) በደረሽ በኩል ያሉት ክፍያዎች ማስተናገድ የሚቻልበት ሁኔታ Diffrenet scenario) በደራሽ በኩል እንዲቀናነሱ እና በቴሌብር በኩል የሚከፈሉ ከፊል ክፍያዎች ወደ ደራሽ እንዲላኩ የማስቻል ስራ ተሰርቷል፡፡ በደራሽ በኩል ያለው በአንድ ቀን ውስጥ በተደጋጋሚ ሊከፈሉ ለሚችሉ ክፍያዎች የማቀናነስ ጉዳይ በሂደት ላይ ነው፡፡
- በኢ-ፔይመንት ሲስተም ላይ ባንኮች፣ ቴሌኮሞች በኢ-ፔይመንት ተሳታፊ ማድረግ፤
- የCBE_BIRR የክፍያ ፕላት ፎርም ስርዓት አስፈላጊ የቅድመ ዝግጅት (ለሙከራ የሚሆን API ተሰርቷል)፡፡
- በኢፔይመንት ተሳታፊ ለመሆን ሙከራቸውን አከናውነው ማረጋገጫ የተላከላቸውና ስራ የጀመሩ 2 ባንኮች አማራ ባንክ እና ፀሃይ ባንክ ናቸው፡፡
- በኢፔይመንት ተሳታፊ ለመሆን በሙከራ ላይ ያሉ 6 ባንኮች ሲሆኑ እነሱም ሲንቄ ባንክ ፣ ረሚስ ባንክ ፣ አሃዱ ባንክ፣ ጎህ ባንክ፣ ሸበሌ ባንክ እና ፀደይ ባንክ ናቸው

**የጉምሩክ ስራ አመራር ስርዓት (ECMS):-** ኮሚሽኑ አለም አቀፍ ደረጃውን ከጠበቀ የጉምሩክ አሰራር ጋር የተጣጣመና የተቀላጠፈ የጉምሩክ አገልግሎት (የወደብ ዕቃ ትልልፍ እና ዕቃ አወጣጥ ጊዜንና ደህንነትን ጨምሮ ለመስጠት የሚያስችል አሰራር ስርዓት ነው፡፡ በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተከናወኑ ስራዎችን በተመለከተ ዋና ዋናዎቹ፡-የጉምሩክ ስራ አመራር ስርዓት የድጋፍና የጥገና ፕሮጀክት ውል ውስጥ የሚገኙትን ችግሮች በመለየት ለአልሚው ድርጅት በማቅረብ የተሰሩ የማስተካከያ ስራዎች፡-

- የዋጋ ትመና ስርዓትን ከጉምሩክ ስራ አመራር ስርዓት ጋር የማስተሳሰር፣የማልማት እና በድጋሚ የፍተሻ ስራ ተከናውኗል፤
- በዋጋ ትመና ስርዓቱ እንዲካተቱ ግብአት የቀረበባቸው ስራዎችን በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ማስጀመር የሚያስችል ሁኔታዎች የተሟሉ መሆኑን በማረጋገጥ እና
- ያልተጠናቀቁ እና ውሳኔ የሚፈልጉ ስራዎችን በመዘርዝር ለአልሚ ድርጅት የማቅረብ ስራ ተከናውኗል፡፡

እንዲሁም ለ619 አዳዲስ የታሪፍ ቁጥሮች የአስገዳጅና አማራጭ የእቃ መረጃ መጠይቆችን በማዘጋጀት ከየዋጋ ትመና ስርዓት ጋር የማናበብ እና በየጊዜው ወቅታዊ የማድረግ ስራ ተከናውኗል፤ አንድ የባንክ ፈቃድ ከአንድ ጊዜ በላይ በጉምሩክ ሰራ አመራር ስርዓት ውስጥ ጥቅም ላይ እንዳይውል የሚቆጣጠረውን የአሰራር ማስተካከያ በማልማት ወደ ትግበራ ማስገባት ተችሏል፡፡ ቀደም ሲል የተጀመሩ የክፍልፋይ የባንክ ፈቃድ ሰነዶችን በልዩ ሁኔታ ማስተናገድ የሚችል የስርዓት ለውጥ ተደርጓል፤ የጉምሩክ ስራ አመራር ስርዓት ከቴሌብር ስርዓት ጋር የማስተሳሰር ስራ የተጀመረ ሲሆን በዚህም መሰረት ኤፒአይ የማልማት ስራው በአልሚው ድርጅት ተጠናቀው ከኢቲዮ ቴሌኮም ጋር በመሆን የፍተሻ ስራዎችን በማጠናቀቅ የፍተሻ ውጤቶች ለአልሚው ድርጅት ተልኳል፡፡ አዳዲስ የሪፖርት አሰራሮችን በማልማትና በመፈተሽ ወደ ትግበራ ማስገባት ተችሏል፤ እንዲሁም አውቶ ካንስሌሽን የሲስተም ማስተካከያ ተደርጓል፡፡የተሰብሳቢ ውዝፍ እዳ አሰራር ማኑዋልን በቴክኖሎጂ ለማስደገፍ የስራ ሂደት ትንተና ተዘጋጅቷል፡፡ የኤሌክትሮኒክስ ታሪፍ መጽሐፍ ረቂቅ ተዘጋጅቷል፡፡

**የኢትዮጵያ የኤሌክትሮኒክ አንድ መስኮት አገልግሎት የማጎልበቻ ምዕራፍ አፈፃፀም በተመለከተ** የማልማትና የፍተሻ ስራቸው ተጠናቆ ወደ ትግበራ የገቡ ስርአቶች፡- የተቆጣጣሪና ተጓዳኝ መስሪያቦቶች ተቀናጀ የስጋት አስተዳደር ስርዓት፤ የቅድመ ጥንቃቄ እና ቁጥጥር አስተዳደር ስርዓት የአንድ መስኮት ዳታ ዌርሀውስ ሶሉሽን ስርዓት የማልማት ስራ የጉምሩክ አንድ መስኮት ሰርቪስ ሌቭል አስተዳደር ስርዓት የማልማት ስራ እንዲሁም የፍተሻ ስራ፤ የጉምሩክ አንድ መስኮት ኢሹ ትራኪንግ ስርዓት ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት በዚህ በጀት ዓመት ከተጠየቁ 4,010 የማስተካከያ ጥያቄዎች ውስጥ 3,462 የማስተካከያ ስራ መስራት ተችሏል፡፡ ከዚህም ጋር በተያያዘ አብዛኛው የተቆጣጣሪ ተቋማትና ፈቃድ ሰጪ ተቋማት የስታንዳርንድ ጊዜአቸውን በደብዳቤ ባሳወቁት መሰረት የመጀመሪያው የተቋማት የጊዜ አፈፃፀም የሚያሳይ ሪፖርት ተዘጋቷል፡፡

**የኢትዮጵያ የኤሌክትሮኒክስ አንድ መስኮት አገልግሎት የሶፍትዌር ማማከር፣ የኔትወርክ መሠረተ ልማት እና የዳታ ሴንተር ልማትና ግንባታ ፕሮጀክት፡-** በገቢዎች ሚኒስቴር የሚገኘውን የኤሌክትሮኒክ አንድ መስኮት የዳታ ማዕከል ተጠናቋል፡፡ የዳታ ማዕከሉ የኔትዎርክ መሰረተ ልማት ዝርጋታ ሁለተኛ ዙር የቅደመ ፍተሻ (Preliminary test) በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የተከናወነ ሲሆን ውጤቱን ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር በመላክ የሚቀጥሉትን የፍተሻ ስራዎችን ለመስራት በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡ ከብሔራዊ ባንክና ከንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጋር በመሆን በገቢዎች ሚኒስቴር የሚገኘውን የጉምሩክ አንድ መስኮት ዳታ ማዕከል ከተጓዳኝ መስሪያ ቤቶች ደህንነቱ በተጠበቀ ኔትዎርክ የማስተሳሰር ስራ ተጀምሯል፡፡

**የኢትዮጵያ የኤሌክትሮኒክ አንድ መስኮት አገልግሎት የተቀናጀ የሳይበር ደህንነት ማማከር አገልግሎት ፕሮጀክት አፈፃፀም:-** ከኢንፎርሜሽን መረብ አስተዳደር ጋር በጋራ በመቀናጀት የሳይበር ደህንነት ስልጠናዎችን ለከፍተኛ አመራሮች መስጠት ተችሏል፤ የሳይበር ደህንነት ኦዲት እና ኢቫሉዌሽን የሳይበር ደህንነት ለማረጋገጥ ሁለት ዙር የሶፍትዌር እና የሀርድዌር ኦዲት በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ የተካሄደ ሲሆን በዚህ መሰረት የተጠቆሙትን የሳይበር ደህንነት ምክረ-ሀሳቦችን በሶፍትዌርች እና በሀርድዌሮች የማካተት ስራዎች ተሰርቷል፡፡

**የኮሜሳ ኢ.ዲ.ኤፍ. 11 - የንግድ ማሳለጥ እና ቀጠናዊ ትስስር ፕሮጀክት አፈፃፀም:-** የኮሜሳ ፕሮጀክት ጋር ተያያዥ የሆኑ የሀርድዌር መሰረተ-ልማት ግዢዎችን የኮንትራት ስምምነት በአቅራቢውና በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር በኩል የተከናወነ ቢሆንም በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ቅድመ ክፍያ መክፈል ባለመቻሉ እቃዎቹም ማስገባት አልተቻለም፡፡ የኦራክል የኢንተግሬሽን ፕላትፎርም ግዥ በማከናወን ርክክብ ለማድረግ በፍተሻ ላይ ይገኛል፤ ከዚህም በተጨማሪ የኢትዮጵያ ኤሌክትሮኒክስ አንድ መስኮት አገልግሎት በኮሜሳ የተዘጋጀውን የ21 አባል አገራት የኤሌክትሮኒክ አንድ መስኮት የቴክኒካል ዎርኪንግ ግሩፕ ስብሰባ ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ አበባ በማካሄድ የአገሪቱን የቴክኖሎጂ አቅም ለአፍሪካ አገራት ለማስተዋወቅ ተችሏ፡፡፤ የኮሜሳ ፕሮጀክት አካል የሆነው የኢትዮጵያ ኤሌክትሮኒክ አንድ መስኮትን ከኬንያ አንድ መስኮት አገልግሎት ጋር የማስተሳሰር እና ከኮሜሳ ኤሌክትሮኒክ ሰርቲፊኬት ስርዓት ጋር ለማስተሳሰር የማልማት ስራው ተጠናቋል፡፡

**የኢትዮጵያ ጉምሩክ ዩኒፓስ ስርዓት ቅድመ-ፕሮጀክት አፈፃፀም ስንመለከት:-** በተቋቋመው ብሔራዊ የቴክኒካል ታስክ ፎርስ ኮሚቴ ውስጥ የጉምሩክ የመረጃ ቴክኖሎጂ ስርዓቶችን ላይ የሚከሰቱ ችግሮችን በመለየት የአጭር ጊዜ፣ መካከለኛ ጊዜ እንዲሁም የረጅም ጊዜ መፍትሔ እንዲሰጥ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት ችግሮችን በመለየት በመመዝገብ እንዲሁም የአጭር ጊዜ መፍትሔ የተሰጠ ሲሆን በዚሁ መሰረት የኢትዮጵያ ጉምሩክ ስራ አመራር ስርዓት አገልግሎት እንዳይቋረጥ የተለያዩ ማስተካከተያ ስራዎች መስራት ተችሏል፡፡ በመቀጠልም የመካከለኛ ጊዜ መፍትሔ ከመስጠት አንፃር ስራዎች በመሰራት ላይ የሚገኙ ሲሆን ከስራዎቹም ውስጥ አንዱ የስቶሬጅ ግዥ መፈፀም አንዱ ሲሆን ለዚህም ስፔሲፊኬሽን ተዘጋጅቷል፡፡ ከረጅም ጊዜ የመፍትሔ ሐሳቦች አንዱ በጉምሩክ ስር የሚገኙ የተለያዩ የቴክኖሎጂ ስርዓቶችን በአንድ ስርዓት ለማቀፍ የሚያስችል በኮሪያ መንግስት ድጋፍ የሚደረግለት የኢትዮጵያ ጉምሩክ ዩኒ-ፓስ ስርዓት ፕሮጀክት ከኮይካ ድርጅት ጋር በመተባበር ፕሮጀክቱን ማስጀምር የሚያስችል የኢትዮጵያ ጉምሩክ ዩኒ ፓስ ስርዓት ፕሮጀክት አዋጭነት ጥናት (Feasibility Study) ከመረጃ ቴክኖሎጂ ልማትና አስተዳደር ማዕከል ጋር በጋራ በመሆን ተከናውኗል፡፡

**ስካኒንግ ማሽን አጠቃቀም፦** በአጠቃላይ ከ29 ማሽኖች ውስጥ 14 ማሽኖች በስራ ላይ፤8 ማሽኖች መጠነኛ ጥገና የሚያስፈልጋቸው፤ 3 ማሽኖች በጥገና ሂደት ያሉ፤ 1 የሞያሌ ኤክስሬይ ማሽን ያለስራ የቆመ እና 3 ማሽኖች በእርጅና ምክንያት የሚወገዱ ናቸው፡፡ እስካሁን ለማሽኖቹ በድምሩ 113 ጊዜ የቅድመ ብልሽት እንክብካቤ ተከናውኗል፡፡ የስካኒንግ ማሽን የፍተሻ ስራ በሰው ሰራሽ አስተውሎት (Artificial Intelligence) የታገዘ እንዲሆን

ለማስቻል ከተለያዩ ተቋማት በኮንትሮባንድ ሊገቡና ሊወጡ የሚችሉ ዕቃዎችን የኤክስሬይ ምስል መረጃ የማሰባሰብ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ እስካሁን በስካኒንግ ማሽን በተደረገ ክትትልና ቁጥጥር 344,944 የተለያዩ የጥቅልና ጭነት ፍተሻ ተካሂዶ ብር 33,920,830 ግምታዊ ዋጋ ያላቸው ዕቃዎች ተይዘዋል፡፡

### የኢትዮጵያ የኤሌክትሮኒክ ካርጎ ትራኪንግ ፕሮጀክት አፈጻጸም

የኤሌክትሮኒክ ካርጎ ትራኪንግ ስርዓትን ተግባራዊ በማድረግ ወደ አገር የሚገቡ እና ከአገር የሚወጡ ጭነቶች ደህንነታቸው ተጠብቆ ወደ መዳረሻቸው እንዲደርሱ፣ ገቢና ወጪ ዕቃዎች በተፈቀደላቸው ጊዜና መስመር መጓዛቸውን ለማረጋገጥና ጭነቱን በመክፈት የሚደረግ ቅሸባ እና የዕቃ ለውጥን ለመከላከል ከማስቻሉም በላይ የጉምሩክ ኬላዎችን በመቀነስ በፍተሻ ኬላዎች ላይ የሚባክንን ጊዜ ማስቀረት ያሚያስችል ቴክኖሎጂ ሲሆን፣ ህገ-ወጥ ተግባር ከተፈጸመ ደግሞ ፈጣን ምላሽ ለመስጠት መረጃን ወዲያውኑ ለማዕከል ማድረስ ያስችላል፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ቴክኖሎጂውን ለመጠቀም ባደረገው ከፍተኛ ጥረት አሁን ላይ አፈጻጸሙ 98 በመቶ በላይ ደርሷል፤ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፡-

- **ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቁ ስራዎች፡-** የሶፍትዌር ልማት ስራዎች (Usere acceptance test)፤ የሴንተራል ሞንተሪንግ ሴንተር፣የዳታ ሴንተር እና የአይቲ ክፍል የቢሮ ግንባታ፣የAC ገጠማ፣ Video wall ገጠማ፣ የኔትዎርክ ኢንስታሌሽንና ኮንፍግሬሽን የኤሌክትሪክ ዝርጋታ፣አምስት የፈጣን ምላሽ መስጫ ተሽከርካሪዎች ላይ የካሜራ ገጠማ ፣የinstallation ስራ እና configuration ስራ ፤በጋላፊና ደወሌ የስማርት ጌት የinstallation እና የሼድ(ቢሮ) ግንባታ ስራ ፤ እንዲሁም በቅ/ጽ/ቤቶችና በኢንዱስትሪ ፓርኮች የካሜራ(CCTV) ተከላ ስራ ፣ የኔትዎርክ ዝርጋታ እና የፋይበር ኬብል ዝርጋታ ስራ ተጠናቀዋል፡፡
- **ያልተጠናቀቁ ስራዎች፡-** የሶፍትዌር ልማቱ 8 ሞጅሎች የማልማት ስራው ተጠናቋል፤ አስተያየት በተሰጠባቸው ላይ የማስተካከያ ስራ በሂደት ላይ ይገኛል፡፡
- **ስልጠና፡-** በሦስት ዙር ለ74 ባለሙያዎች በሶፍትዌሩ ላይ ስልጠና ተስጥቷል፡፡እንዲሁም የኢትዮጵያ ኤሌክትሮኒክ ካርጎ ትራኪንግ የአሰራር ማንዋል እና መመሪያ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡በተጨማሪም ለባለድርሻ አካላት በኢትዮጵያ ኤሌክትሮኒክ ካርጎ ትራኪንግ ሲስተም ፕሮጀክት ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

**ስማርት ቦርደር ማኔጅመንት ፕሮጀክት የኔትወርክ መሠረት ልማት፡-** የጉምሩክ ስማርት ቦርደር ማኔጅመንት ሥርአትን በተመለከተ ለሙከራ ትግበራ የሚያስፈልጉ የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት የመለየት ስራ፤ አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶች ማለትም ሰርቨሮች፣ የኔተትወርክ እቃዎች /ራውተርና ስዊቶች/፣ የኔትወርክ ደህንነት እቃ በማሰባሰብና አስፈላጊው የተከላና ኢንፕልምንቴሽን ሥራዎች ተከናውነዋል፣ ከዚህ ጋር በተያያዘ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ የኢትዮ-ቴሌኮም መስመሮች /SMS, VPN,እና Internet …/ እንዲዘረጉና እንዲገናኙ ተደርጓል፡፡

**አርተፊሺያል ኢንተለጀንስን መሰረት ያደረገ ቻትቦት እና ፈቃድ አሰጣጥ ፕሮጀክት፡-** ፕሮጀክቱ የጉምሩክ አስተላላፊዎችን መረጃ፣ ስልጠና፣ ፈቃድ አሰጣጥ እና ስረዛ ድረስ ያለውን ሂደት በሲስተም የማስደገፍና፣ የቦንድድ መጋዘን ፈቃድ አሰጣጥ፣ መረጃ አያያዝ እና ስረዛ፣ ተገልጋዮች ባሉበት ሆነው

ጉዳያቸውን የሚከታተሉበት እና ቅሬታቸውን የሚያቀርቡበት እንዲሁም የደንበኞች በአራት ቋንቋዎች ስለተቋሙ አሰራሮች፣ ህጎች እና ቅድመ መረጃዎች ባሉበት ሆነው እንዲደርሳቸው አላማ በማድረግ ተቀርፆ በአርተፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት በኩል የሚለማ ፕሮጀክት ነው፡፡በ12 ወራት ከቦንድድ መጋዘን ፍቃድ አሰጣጥ ጋር በተያያዙ አሰራሮች ዙሪያ ግምገማ ተካሂዷል፤ በዚሁ መነሻነት የማሻሻያ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

## የአጋርነት እና የህዝብ ግንኙነት አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል አፈጻጸም

### ➲ የሀገር ውስጥ አጋርነትና ትብብርን ማሻሻል

ከስትራቴጂክ አጋር አካላት ጋር በቅድሚያ ሚናቸውን በመለየት ግንኙነት መፍጠር፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር የመግባቢያ ሰነድ መፈራረም፣ ቋሚ አደረጃጀት መፍጠር፣ የተፈረሙ ስምምነቶችን በጋራ ዕቅድ በማውጣት ተግባራዊ ማድረግ እና ተግባራዊ መሆናቸውን መከታተል፣ የሚከሰቱ ችግሮች ካሉ በጋራ መፍታትን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡

#### የሀገር ዉስጥ አጋርነት ስምምነትን በተመለከተ፡-

- አማራ ባንክ፣ ፀሐይ ባንክ እና ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የታክስ ክፍያ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ለማሰባሰብ የሚያስችል የአገልግሎት አሰጣጥ ስምምነት ሰነድ ተፈራርመዋል፡፡
- የገቢዎች ሚኒስቴር ፣ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር በደብዳቤዎችን እና ሰነዶችን ማድረስ የሁለቱ ወገኖች ኦፊሴላዊ ኢሜይሎች የሁለትዮሽ የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ (Delivery of letters and documents through official emails of the two parties) ፣ተዘጋጅቶ እና የህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ተመልክቶት ሰነድ በሰኔ 19/2016 ዓ.ም ተፈርሟል፡፡
- በገቢዎች ሚኒስቴር፣ ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር እና የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች አገልግሎት ዕውቅና ያገኙ ስደተኞን እና ጥገኝነት ጠያቂዎች በንግድ ሥራ ለመሰማራት እንዲችሉ በጋራ ስለመስራት፡ የተዘጋጀው የመግባቢያ ሰነድ ከታክስ ከፋዮች ምዝገባና አገልግሎት መጥቶ ወደ ህግ አገልግሎት ተልኮ አስተያየት ተሰጥቶበት የመጨረሻውን ቅርፅ ይዞ ተፈርሞ ለተግባራዊነቱ ሰነዱ ተሰራጭቷል፡፡
- ከንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚ/ር ጋር በኦንላየን አገልግሎት አሰጣጥና ተባብሮ ለመስራት የሁለትዮሽ የትብብር ስምምነት ተፈርሟል፡፡
- ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር የሚገባው የባካፕ አገልግሎት የውል ስምምነት ላይ የህግ አስተያየት ተጠይቆ የተሰጠው አሰተያየት የመረጃ ቴክኖሎጂ ማዕከል ሰነዱ ላይ ያሉ ቴክኒካዊ ነገሮች በደንብ በመፈተሽ የሚኒስቴር መ/ቤቱን ጥቅም እንዲያስከብር ሲል አስተያየት በመስጠቱ የመረጃ ቴክኖሎጂ ማዕከል የተሰጠውን አስተያየት እንዲያስተካክል ተመልሶ ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡

#### በአገር ውስጥ አጋር አካላት ለቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጠ ምላሽን በተመለከተ፡-

- የኢትዮጵያ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ጋር የሚኒስቴር መ/ቤታችን ለታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ጽ/ቤት ጋር በግብር ከፋዮች ቅሬታ አፈታትና  አገልገሎት አሰጣጥ ዙሪያ በጋራ በሚሰሩ ጉዳዮች ዙሪያ በአካል በመገኘት የተቋሙ  17 አመራሮች በተገኙበት  ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ያዘጋጀው የመነሻ ጽሁፍ ቀርቦ ውይይት ከተደረገ በኃላ

በቀጣዩ መድረክ በገቢዎች ሚኒስቴር የሚካሄድ መሆኑን እና የእንባ ጠባቂ ተቋም ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር በትብብር ሊሰራ የሚችለውን ሰነድ አዘጋጅቶ በእለቱ ለተቋማችን አመራሮች እንደሚያቀርቡ ከስምምነት ተደርሷል፡

- ደብረብረሃን ዩኒቨርሲቲ ላቀረበው የአብረን እንስራ ጥያቄውን በመቀበል አብረን ልንሰራ የምንችለው በምን በምን ዙሪያ እንደሆነ የሚገልጽ ዝርዝር መረጃ ተዘጋጅቶ የተቋማችን አመራሮች ባሉበት ፕሬዘንቴሽን (ገለጻ) ማድረግ እንዳለባቸው በውይይቱ ስምምነት ላይ ተደርሷል፡
- ሚኒሰቴር መ/ቤቱ ከመጋቢት 10-11 ቀን 2016 ዓ.ም ከእንባ ጠባቂ ተቋም አመራሮችና መርማሪዎች ጋር የገቢዎች ሚኒስቴር የታክስ ህጎች ላይ የሁለት ቀናት ግንዛቤ ማሥጨበጫ ስልጠና አካሂዷል፡፡
- የጉምሩክ ኮሚሽን መጋቢት 19 ቀን 2016 ዓ.ም ባዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ የገቢዎችና ጉምሩክ የባለሙያዎች ማህበር ለማቋቋም በታቀደው ውይይት መድረክ ላይ ተሳትፎ ተደረጓል፡፡
- የክርስቲያን በጎ አድራጎት እና ልማት ማህበራት ህብረት consortium of Christian Relief and Development Association (CCRDA) ባዘጋጀው የምርምር ማረጋገጫ እና የፖሊሲ ውይይት አውደ ጥናት ላይ ሚያዝያ 18 ቀን 2016 ዓ.ም ተሳትፎ ተደርጓል፣

**ለአገር ውስጥ አጋር አካላት የተሰጠ ድጋፍ፡-** የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና የውጭ ጉዳይ ኢንስቲቱይት በጋራ በመሆን በምስራቅ አፍሪካ አገራት ኮሚኒቲ አባልነት ፍላጎት እና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ፣የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ የቪሮስ (የኢጋድ አባላት ስምምነት) መፈፀም ምክክር ላይ ታህሳስ 23 ቀን 2016 ዓ.ም በተደረገው የውይይት መድረክ ተሳትፎ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ከውጭ ኦዲተሮች ማህበር ጋር የተጀመረውን ስራ ለማስቀጠል የሚያስችል ከታክስ ኦዲት፣ ከቦርዱ እና ከኛ ጋር የተዘጋጀው ፕሮፖዛል ለክብርት ሚ/ር ቀርቧል፡፡

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ባዘጋጀው የምክክር መድረክ ላይ ድራፍት ቴ/ሙ/ሥ ፋይናንሲንግ ስትራቴጂ ምክክር ዎርክሻፕ East Africa Skils for transformation and Regional integration project (EASTRIP) National Project Coordination Unit (NPCU). Advancing Ethiopia's T.V.E.T Excellence: A consultative workshop on the Draft Financing Strategy በሚል ርዕስ ላይ ለሁለት ቀን ተሳትፎ ተደረጓል፡፡

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የመንግስትና የግሉ ዘርፍ የንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ የመሪነት ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ በሚል ርዕስ ላይ ሐምሌ 18 እና 19 ቀን 2015 ዓ.ም በስካይ ላይት ሆቴል በተደረገው የውይይት መድረክ ተሳትፎ ተደርጓል፡፡

የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት በሚኒስቴር መ/ቤቱና በመካከለኛ አመራር ደረጃ እያገለግሉ የሚገኙትን አመራሮች የአንድ ቀን ስልጠና ለሥራ ክፍሎች እነዲሳተፉ አመቻችቷል፡፡ በተጨማሪም ጊግ ኢኮኖሚ በሚል ርእስ መስከረም 28/2016 ዓ.ም ከባለ ድርሻ ጋር ንግድና ቀጠናዊ ሚ/ር፣ የስራ ፈጠራና ክህሎት ሚ/ር እና ማህበራዊ ጉዳ ሚ/ር በጋራ ባዘጋጁት የውይይት መድረክ ላይ ተሳትፎ ተደርጓል፡፡

ቻፓ በዲጂታል ቴክኖሎጂ ኦን ላይን ክፍያን ለማካሄድ የግብር ከፋዩን የታክስ ክፍያ ለማስተላለፍ ለጠየቀው ጥያቄ ድርጅቱ ባንክ ባለመሆኑና የባንክ አገልግሎት የማይሰጥና ደንበኞችም የሌለው

በመሆኑ ፕላት ፎርም ብቻ ተይዞ የንግድ ማህበረሰብ ታክሱን በነሱ ፕላትፎርም በኩል ማስተላለፍ የማይቻል መሆኑ ተነግሯቸዋል፡፡

የውጭ ኦዲተሮችና የሂሳብ አዋቂዎች ማህበር በውላችን መሰረት ስራችንን እናስኪድ የሚል ጥያቄ አቅርበዋል በዚሁ ሃሳብ መሰረት በአካል መተው ከታክስ ኦዲት ዳይሬክቶሬት የስራ ሃላፊዎች ጋር በ20/03/16 ዓ.ም በተደረገ ውይይት ፎካል ፐርሰን ተቀይሮ በአዲስ መልክ ስራውን ለመቀጠል የሚያስችል ውይይት ተደርጓል፡፡

**በራሳቸው ተነሳሽነት የተገኘ የቴክኒክ ድጋፍ፦** በራሳቸው ተነሳሽነት የአቅም ግንባታ ድጋፍ ሲገኝ ስለተፈጻሚነቱ ድጋፍና ክትትል ማድርግ ታቅዶ የATI Workshop Series on Property Taxation ርዕስ ለ5 ሰዎች እና Webinar on taxation & Gender በሚል ርዕስ ለ6 ሰዎች፣ Webinar on "Supreme Audit Institutions (SAIs) as accountability stakeholders for tax systems that advance the SDGs" ለ9 የስራ ክፍሎች ተመቻችቷል፡፡

**በጉምሩክ ኮሚሽን የሀገር ውስጥ አጋር አካላት አጋርነትና ትብብር ሥራዎችን ከመፈጸም አኳያ፡-** ኮሚሽኑ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የመግባቢያ ስምምነቶችን በመፈራረም የሀገር ዉስጥ ትብብርን የማጠናከር ስራ 86 በመቶ ለማድረስ የታቀደ ሲሆን፤ክንውኑ 87.5 በመቶ በመሆኑ አፈፃፀሙ 101.74 በመቶ ነው፡፡ የሀገር ውስጥ አጋር አካላት አጋርነትና ትብብር ለማሻሻል ከተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ውስጥ ከአዲስ አበባ ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ጋር የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርሚል፡፡ ከዘጠኝ ድርጅቶች (ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ፣ ኤካ ኮተቤ አጠቃላይ ሆስፒታል፣ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ ከኢትዮጵያ ፈጣን መልእክት አገልግሎት ፣ኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት፣ ከኢትዮጵያ የምግብና መድሃኒት ባለስልጣን ፣ ኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርት እና ሎጅስቲክ አገልግሎት ድርጅት፣ የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን፣የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት) ጋር ለመፈራረም የስምምነት ሰነዶች ተዘጋጅተዋል፡፡ ከሃገር ውስጥ ባለድርሻ አካላት ጋር በተፈጠሩ ስምምነቶች የተከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ በተደረገ ዳሰሳ ጥናት ውጤታማነቱ 64.7 ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ስለሆነም በስምምነቶች መሠረት በቀጣይ ከሀገር ውስጥ አጋር አካላት ጋር ሰፊ ስራዎች መሰራት እንዳለባቸው ያመለክታል፡፡

**የዉጭ አጋርነት ስምምነት፦** ተቋሙ ተልዕኮውን ለማሳካት እንዲያስችለው ትብብር መፍጠር አስፈላጊ የሆነባቸውን አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶችን በመለየት፣ ትብብር ለመፍጠር የሚያስችሉ ስምምነቶችን ማፈራረም ታቅዶ የአውሮፓ ቻምበር በኢትዮጵያ የመግባቢያ ረቂቅ ስምምነት ሰነድ እንዲፈረም ክትትል የማድረግ፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከWorld Bank Group ጋር በመተባበር ለሚሠራቸው ሥራዎች (ኢንሼቲቭ) በቀረበ ዳሰሳ ላይ ውይይት የማድረግ እና የHMRC የቴክኒክና አቅም ግንባታ ድጋፍ የመግባቢያ ስምምነት ተፈርሚል፡፡

**ለዉጭ አጋር አካላት የተሰጠ ድጋፍ፡-** ከአጋር አካላት በሚቀርቡ አጀንዳዎች ዙሪያ ለሚነሱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች አስፈላጊውን ድጋፍ ማድርግ ታቅዶ፦

- BRITACOM Secretariat ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያለውን ልምድ በኦላይን ኮርስ እንዲያካፍል በጠየቀው መሰረት ለዘርፎቹ የተጠየቀ ሲሆን ምላሹንም ክትትል ተደርጓል፤ "Questionnaire of Promoting Tax Administration Digitalization Task Force" የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች እንዲሞሉ ድጋፍና ክትትል ተደርጓል፣

- ለአዲስ አበባ ገቢዎች ባለስልጣን በሚኒስቴር መ/ቤቱ የቴክኒክ እና አቅም ግንባታ ድጋፍ አሰጣጥ ዙሪያ የልምድ ልውውጥ ለዳሰሳ ጥናት ቡድኑ ማብራሪያ ተሰጥቷል፣
- አይ ኤም ኤፍ አፍሪ ቴክ ኢስት በኤክሳይዝ ታክስ የአቅም ግንባታ ስልጠና ላይ የተሳተፉ ባለሙያዎች በሊንክ በተላከ ፎርም እንዲሞላ በጠየቀው መሠረት ሊንኩ ለተሳታፊ ሰልጣኞች ተልኮ እንዲሞሉ ተደርጓል፣
- ከቢልና ሚሊንዳ ጌትስ ፋውንዴሽን የዲጀታላይዜሽን ዲያግኖስቲክ ፕሮጀክት ቡድን ጋር የዙም እና መድረክ ውይይቶች ተካሂዷል፣
- የአውሮፓ ቻምበር በኢትዮጵያ ባቀረበው የታክስ አስተዳደር ፖሊሲ ብሪፍ ውይይት መድረክ ላይ የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች እንዲሳተፉ ተደርጓል፣
- በኢትዮ - ጁብቲ የጋራ ሚኒስትሪያል ኮሚቴ የ16ኛ ቃለ-ጉባኤ እና የደረሰበት ደረጃ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ አስተያየት ተሰጥቷል፣
- የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባዘጋጀው የሳውዲ አረቢያ የመግባቢያ ስምምነት ረቂቅ ሰነድ የግብአት ማሰባሰቢያ ውይይት መድረክ ላይ ተሳትፎ ተደርጓል።

**የተገኘ የዉጭ የቴክኒክ ድጋፍ፦ ፦** የቴክኒክ ድጋፍ ፕሮፖዛል መንደፍና ማፀደቅ፣ ድጋፍ ከሚሰጡ አካላት ጋር የአፈፃፀም ሰነድ ማዘጋጀት እና ስለተፈጻሚነቱ ድጋፍና ክትትል ለማድርግ ታቅዶ፦

- የህዝባዊ ሪፐብሊክ ቻይና ኢምባሲ በላከው የድጋፍ ፕሮፖዛል ላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያለውን አስተያየት እንዲሰጥበት በጠየቀው መሰረት የአጭር እና የረጅም ጊዜ የትምህርት ዕድል ፍላጎት ለኢምባሲው የመላክ፣
- የChina-IMF Capacity Development Center በ"Tax Policy and Administration" እ/ኤ/አ ከሰኔ 24 - 28/2024 ዓ.ም በሚሰጠው ወርክሾፕ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተሳታፊ ዝርዝር ለድርጅቱ የመላክ፣
- BRITACOM በ5th Tax Administration Theme Day Event በሚል ርዕስ ለ5 ሰዎች በ"Current Issues in Tax Law Design (TLWD)" ወርክሾፕ ላይ 2 ሰው እንዲሳተፉ፣ በLLM Education programme on Taxation ለ3 ሠራተኞች ተመቻችቷል፣
- * 4ኛው BRITACOF የሚንስቴር መ/ቤቱ ተሳትፎ ክትትል እና ድጋፍ ተደርጓል፣
- በንጉሱ ገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤት (HMRC) የስጋት ሥራ አመራር እና በዋጋ ትልልፍ ኦዲት ቴክኒክ ድጋፍ እንዲገኝ ክትትል ተደርጓል፣
- በCATA senior leadership development programme 2024-2025 በሰጠው የስልጠና ዕድል የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተሳታፊ ዝርዝር ለHMRC ተልኳል፣
- የአይ ኤም ኤፍ አፍሪ ቴክ ኢስት የኤክሳይዝ ታክስ ስልጠና ለ46 ሠልጣኞች ስልጠናወ እንዲያገኙ፣ በታንዛኒያ በሚደርገው 26th AFE and ATI Steering Committee ስብሰባ ላይ 2 ሰዎች እንዲሳተፉ፣ በዛምቢያ ታክስ ባለስልጣን በIntegrated Tax Administration (ITAS) 4 ሰዎች ልምድ ልውውጥ እንዲገኝ፣ በStrengthing Revenue Administration for Gender Equality ወርክሾፕ ላይ 3 የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሰራተኞች እና በTransfer pricing 4 ሰዎች እንዲሳተፉ ድጋፍና ክትትል ተደርጓል፣
- ከአለም ባንክ ግሩፕ ጋር በጋራ በተዘጋጀ "International Conference in Digital tech solutions for tax Administration" የሁለት ቀናት ዎርክሾፕ የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች እንዲሳተፉ ተመቻችቷል፣ ለ8 የስራ ክፍሎች እስከ ቡድን መሪ ድረስ የተሞክሮ ልውውጥ እንዲያካሂድ ተመቻችቶ የልምድ ልውውጡ ተካሂዷል፣ ከግብር አሰባሰብ፣ ከግብር ከፋዮች

አገልግሎት፣ ከዲጅታላይዜሽን፣ ከሰው ሀይል አስተዳደርና አቅም ግንባታ አንፃር ለመደገፍ ስምምነት ላይ ተደርሷል፣

- የገቢዎች እና የጉምሩክ ከፍተኛ አመራሮች ከደቡብ አፍሪካ እና ኬንያ የገቢ አገልግሎት በታክስ እና በጉምሩክ አሰራሮች የልምድ ልውውጥ ጥያቄ ላይ ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡

**በጉምሩክ ኮሚሽን የውጭ ሀገራትና ድርጅቶችን አጋርነትና ትብብብር ከማሳደግ አኳያ፡-** የውጭ ሀገራትና ድርጅቶችን አጋርነትና ትብብብር ከማሳደግ አኳያ 86 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ 81.25 በመቶ በመከናወኑ የዕቅዱን 94.47 በመቶ ለመፈፀም ተችሏል፡፡ የተከናወኑ ዋና ዋና ስራዎችን በተመለከተ ከሁለት ሃገራት ጋር ሦስት ስምምነቶች ተፈርመዋል፤እነዚህም ከተባበሩት አረብ ኢሚሬትስ ጋር በጉምሩክ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ በጋራ የመረዳዳት ስምምነት ተፈርሟል፤ ከሩሲያ ጋር በጉምሩክ ዋጋ ትመና መረጃ ልውውጥ እና በህግ ማስከበር ላይ ያተኮሩ 2 ፕሮቶኮል ስምምነቶች ተፈርመዋል፡፡ እንዲሁም የ4 ስምምነቶች ሰነድ ዝግጅት ተጠናቋል፤ እነዚህም ከህንድ፣ከሳኡዲ አረቢያ እና ከሩሲያ ጋር 2ሰነዶች ናቸው፡፡ ሌሎች 3 በሂደት ላይ ያሉ የትብብር ማዕቀፎች እየተዘጋጁ ሲሆን እነዚህም ከሩዋንዳ፤ከደቡብ ኮሪያ፣እና የብሪክስ ስምምነቶች ናቸው፡፡ በዓለም ጉምሩኮች ድርጅት የተዘጋጀውን WCO CLiKC ስልጠና እንዲሳተፉ 277 የተቋሙ ሰራተኞች እንዲመዘገቡና የመጠቀሚያ አክሰስ እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን ፣በዚህ በጀት ዓመት 223 ሰራተኞች የተለያዮ ኮርሶችን በመውሰድ አጠናቀዋል፡፡

## የህዝብ ግንኙነት ሥራዎች አፈጻጸም

- በበጀት ዓመቱ 52 የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን አዘጋጅቶ ለማሰራጨት ታቅዶ 44ቱን የማሰራጨት ሥራ የተሰራ ሲሆን 52 የሬድዮ ፕሮግራሞችን አዘጋጅቶ ለማሰራጨት ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተሰራጭተዋል፡፡ 28ሺ 549 ያህል አዳዲስ የፌስቡክ ተከታዮችን በማፍራት አጠቃላይ የተከታዮች ቁጥር ወደ 214,285 ከፍ ሲል 2,245 ያህል አዳዲስ የዩቱዩብ ተከታዮችን በማፍራት የተከታይ ቁጥር ወደ 4,171 ከፍ ያለና የቴሌግራም ተከታዮችን ቁጥር ደግሞ ወደ 21,725 ከፍ ሊል ችሏል፡፡ በተጨማሪም በተቋሙ መረጃ ማስተላለፊያ ከ26 ሺህ በላይ የቲክ ቶክ ተከዮችን ቁጥር ማድረስ ተችሏል፡፡
- በማህበራዊ ሚዲያ መረጃዎችን ከማሰራጨት አንጻር በበጀት ዓመቱ ውስጥ 496 ያህል መረጃዎችን በማህበራዊ ሚዲያ ወይም ፌስቡክ እና በቴሌግራም ገጽ ለማሰራጨት ታቅዶ 668 መረጃዎችን ለመጫን ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 230 ያህል የዩቱዩብ እና የድህረገጽ መረጃዎች ተሰራጭተዋል፡፡
- በሚዲያ ሞኒተሪንግ የ52 ሳምንታት ሪፖርት የቀረበ ሲሆን አስራ ሁለት ‹‹ገቢያችን ህልውናችን›› እና አስራ ሁለት ‹‹እኛ ለእኛ›› ጋዜጦችን ከመረጃ ስብሰባ እስከ ህትመት እና ስርጭት ለማከናወን ታቅዶ ሙሉ ለሙሉ ተከናውነዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ 24 ኹነቶችን ለማስተባበር በዕቅድ ተይዞ 30 ሁነቶች የማስተባበር ስራ መሰራቱ እና ልዩ ልዩ የተግባቦት መንገዶችን ተጠቅሞ መልዕክት የማስተላለፍ ሥራ፣ 250 በዜና መልክ የተሠሩ መረጃዎችን ዲጂታል ሳይኔጆችን እና ቪዲዮ ውሎችን በመጠቀም ለተቋሙ አመራሮችና ሠራተኞች ተደራሽ የማድረግ የወረቀት አልባ አሠራርን ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዶ 302 ማስታወቂያዎች ተደራሽ የማድረግና 83 ባነሮችን በማሳተም መልዕክቶች እንዲተላለፉ የተደረገና 7 የንግግር ጽሁፎችን የማዘጋጀት፣ 5 ጋዜጣዊ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ማለትም የ2015 በጀት ዓመት የፌደራል ግብር ከፋዮች እውቅና እና ሽልማት መርሀ ግብር በስኬት እንዲጠናቀቅ፣ የአድዋ ድል በአል በደማቅ ሁኔታ እንዲከበር ፣ የገቢው ዘርፍን የ2016 በጀት ዓመት የአራት፣ የስድስትና የዘጠኝ ወራት ዕቅድ

አፈጻጸምን፣በገቢው ዘርፍ እየተሰሩ ያሉ የሪፎርም ሥራዎችን እና የንቅናቄ ማጠቃለያና ማስጀመሪያን አስመልክቶ ጋዜጣዊ መግለጫ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

## 2.5 ለተጠሪ ተቋማት እና ለክልሎች የሚደረግ ድጋፍና ክትትል ማሻሻል አፈጻጸም

በበጀት ዓመቱ የተጠሪ ተቋማት ዕቅድ ከዘርፍ ዕቅድ ጋር ማናበብና ማጣጣም፣ የየሩብ ዓመቱን የተጠሪ ተቋማት ሪፖርት መገምገም፣ የክልሎችን ዕቅድ ከዘርፍ ዕቅድ ጋር ማናበብና ማጣጣም፣ ከክልሎች ጋር የዘርፍ አፈጻጸም በጋራ መገምገም እና ለክልሎች ወቅታዊ የአቅም ግንባታ ድጋፍ ስራዎችን በመስራት የዘርፉ ዕቅድ ከተጠሪ ተቋማት ዕቅድ ጋር ተጣጥሞ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

### ➲ ከክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ገቢ ተቋማት ከድጋፍ አንጻር የተሰሩ ስራዎች

#### ❖ ሥልጠናዎች

በበጀት ዓመቱ በ15 የስልጠና ርዕሶች ላይ ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ባለሙያዎች እና የሥራ ኃላፊዎች በዙምና በአካል በመገኘት በኢፋይሊንግ፣ በሲግታስና ቁርጥ ግብር፣ ያላሳወቁ ግብር ከፋዮች መለያ፣ በታክስ ከፋዮች ምዝገባና ስረዛ ሞጁል፣ በብሄራዊ መታወቂያ ሥርዓትና በታክስ አስተዳደር፣ በታክስ ህጎች፣መመሪያዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና የአሰራር ማንዋሎች፣ በደንበኞች አያያዝና ድጋፍ፣ በአመራር ሰጪነት ክህሎት፣ በIFRS፣ በጋራ ገቢ፣ በሦስተኛ ወገን፣ በታክስ ኦዲት ፣ በሽያጭ መመዝገቢያ ቁጥጥርና መረጃ አስተዳደር፣ በታክስ ተመላሽ፣ በዲጂታል መታወቂያና በመሳሰሉት ርዕሶች ዙሪያ ለ1,427 ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ1,305 ሰልጣኞች ስልጠናውን የወሰዱ ሲሆን የዕቅዱን 91.45 በመቶ ተከናውኗል፡፡

ሰንጠረዥ 6 በ2016 በጀት ዓመት ስልጠና የወሰዱ ክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች

| ተ.ቁ. | ክልል/ከተማ አስተዳደር | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ኦሮሚያ | 298 | 113.1 | 113.1 |
| 2 | አማራ | 132 | 79.55 | 79.55 |
| 3 | ደቡብ ኢትዮጵያ | 245 | 96.73 | 96.73 |
| 4 | ሲዳማ | 104 | 88.46 | 88.46 |
| 5 | አፋር | 27 | 37.04 | 37.04 |
| 6 | ሀረሪ | 35 | 37.14 | 37.14 |
| 7 | ጋምቤላ | 33 | 51.52 | 51.52 |
| 8 | ቤኒሻንጉል | 32 | 21.88 | 21.88 |
| 9 | ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | 105 | 99.05 | 99.05 |
| 10 | ሶማሌ | 51 | 58.82 | 58.82 |
| 11 | ደቡብ ምዕራብ | 141 | 85.11 | 85.11 |
| 12 | አዲስ አበባ | 141 | 121.3 | 121.3 |
| 13 | ድሬዳዋ | 30 | 56.67 | 56.67 |
| 14 | ትግራይ | 53 | 84.91 | 84.91 |
| ድምር | | **1427** | **1305** | **91.45** |

### ➲ የተሰጡ የመረጃ ቴክኖሎጂ አገልግሎት ድጋፎች

- ❖ የኦሮሚያ እና የሀረሪ ገቢዎች ቢሮዎች ከደረጃ ``ሐ`` ግብር ከፋዮች የቁርጥ ግብር በሲግታስ ሲስተም አማካኝነት ውሳኔ ወጥቶ ግብርን በኢ-ታክስ በቴሌ ብር በኩል እንዲከፍሉ ተደርጓል፤ እንዲሁም ሲዳማ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ፣ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ እና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች ስልጠና እና የቴክኒክ ድጋፍ ተሰጥቷቸው ወደ ሲስተም ገብተዋል፤
- ❖ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ፣ የኦሮሚያ ገቢዎች ቢሮ እና የአማራ ገቢዎች ቢሮ የኢ-ታክስ ስርዓት እንዲገቡ ተደርጓል፤
- ❖ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ሲግታስ አገልግሎት እና የአክሳስ ሰኩሪት ጋር ተያይዘው ለተነሱ ጉዳዮች እልባት እንዲሰጣቸው ተደርጓል፤
- ❖ ለሀረሪ፣ ለሶማሌ፣ ለኦሮሚያ፣ አማራ፣ ለማዕከላዊ ኢትዮጵያ፣ትግራይ፣ ጋምቤላ እና ለደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት የታክስ ማእከል እንዲከፈትላቸው ተደርጓል፤
- ❖ ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ገቢዎች ቢሮ ለሲግታስ ማስፋፋት የሚያስፈልግ በጀትና ማቴሪያ ግምት፣ ለደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት ገቢዎች እና ኦሮሚያ ገቢዎች ቢሮ በሲስተም ላይ የመዋቅር ማስተካከያ ድጋፍ ተደርጓል፤
- ❖ ለትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢዎች ልማት ባለሥልጣን ለ 8 ባለሙያዎች user Name በሲግታስ ዳታ ቤዝ እንዲከፈትላቸው ተደርጓል።

### የቋሚ ቁሳቁስ እና ሌሎች ድጋፎች

- ❖ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተደራጅተው ለቀረቡ የድጋፍ 10 ጉዳዮች/ የመመሪያዎች ግልፅነት፣የኢ-ታክስ፣ የሲግታስ አግልግሎት፣ ቅንጅት… ወዘተ/ ምላሽ እንዲያገኙ ተደርጓል፣
- ❖ ከጋራ ገቢ ክፍፍል ግልፅነት ዙሪያ በሲዳማ፣ ከአማራ፣ ከኦሮሚያ፣ ከደቡብ ምዕራብ፣ ከቤንሻንጉል ለቀረቡ ጥያቄዎች አስፈላጊውን የመረጃ ማጥራት ስራዎች ተሰርተው ምላሽ እንዲሰጣቸው ተደርጓል፣
- ❖ ከፌዴራል፣ ከአዲስ አበባ እና ከሌሎች ክልሎች የተለያዩ የስራ ላይ ልምድ እና ተሞክሮዎች ለመውስድ ለተንቀሳቀሱ ክልሎች ልምድ እና ተሞክሮ እንዲያገኙ ድጋፍ ተደርጓል፣
- ❖ ሀገር አቀፍ የታማኝ ግብር ከፋዮች የምስጋና እና የዕውቅና መርሐ ግብርን ለክልልና ከተማ አስተዳደር ፕሬዝዳንቶች እና ቢሮ ሀላፊዎች እንዲገኙና ልምድ እንዲወስዱ ተደርጓል። እንዲሁም በራሳቸው መርሐ ግብሩን ሲያዘጋጁ ደግሞ በታማኝ ታክስ ከፋዮች ልየታ እና በፕሮግራም ዝግጅት ላይ ቴክኒካል ድጋፍ ተደርጓል፣
- ❖ ትግራይ ክልል ገቢዎች ቢሮ ወደ መደበኛ ስራ እንዲገባ በስልጠና እና በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ድጋፍ እንዲያገኝ ተደርጓል፣

- ❖ ለትግራይ፣አፋር፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ እና ቤንሻጉል ጉምዝ የወንበር፣ የጠረጴዛ፣ የሼልፍ እና ሌሎች ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፤
- ❖ ለአፋር ክልል ገቢዎች ቢሮ በአደረጃጀቱ፣ በሠራተኞች ድልድል፣ በታክስ ደረሰኝ አጠቃቀም እና አስተዳደር ረቂቅ መመሪያዎች እንዲሁም በኤክሳይዝ ታክስ ረቂቅ አዋጅ ላይ በአካል በመገኘት ድጋፍ ተደርጓል፣
- ❖ ለሁሉም ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች የመረጃ ጥራት ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችላቸው data quality tool ቴምፕሌት ተግባራዊ እንዲያደርጉ ተልኮላቸዋል፣
- ❖ የክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች የ1ኛ ሩብ እና የግማሽ ዓመት የገቢ እቅድ አፈፃፀም በዙም በመገምገም ቴክኒካል ድጋፍና ልምድ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

## ➲ የታክስ ስርዓትን ከማጣጣም አንጻር የተሰሩ ስራዎች

- ❖ የክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች የገቢ አፈፃፀም ዳሰሳና በአካል ምልከታ መሠረት የታክስ ፖሊሲ እና የታክስ አስተዳደር ክፍተቶች በተለይ የጫት ቀረጥ፣ የአካባቢ ብክነት ታክስ፣ ቅድመ አወሳሰን መመሪያ፣ ቅድመ ሻት አሰባሰብ እቅድ፣ ከአንድ ክልል በላይ ስራ ላይ ከተሰማሩ ግለሰብ ታክስ ከፋዮች የሚሰበሰብ ሻት ተልይተዋል፤ እንዲፈቱም ክትትል እየተደረገ ይገኛል፤
- ❖ በክልሎች እና ከተሞች ለሚቀርቡ የህጎችና አሰራር ክፍተት ጥያቄዎች ምላሽ ከመስጠት አንፃር ከጋራ ገቢዎች ክፍፍልና ትልልፍ ጋር የተያያዙ / ሲዳማ፣ቤንሻንጉል፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ኦሮሚያ፣ አማራ/፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቅያ ጊዜ የሶስት ወር፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከአንድ ክልል በላይ ጉዳይ፣ የሜትር ታክስ፣ የአክሲዮን ማህበራት፣ የአስጎብኝ ድርጅቶች፣ ወዘተ ምላሽ እንዲያገኙ ተደርጓል፤
- ❖ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እና በሌሎች አካላት የወጡና በወጥነት መተግበር የሚገባቸው 25 መመሪያዎችና ሰርኩላሮች ተጣጥመው እንዲፈፀሙ ለክልሎች በማስተላለፍ ተፈፃሚነታቸውን በአካል ምልከታ ክትትል ተደርጓል፤
- ❖ በአካል በክልሎች በመገኘት ምልከታ በማድረግ በታክስ አስተዳደርና ገቢ አሰባሰብ ዙሪያ በሚታዩ ኦፐሬሽልና ቴክኒካል ጉዳዮች ድጋፍ ከመስጠት አንፃር በሲዳማ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ፣ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ፣በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እና በጋምቤላ የመስክ ምልከታ በማድረግ የአቅም ግንባታ፣ ቴክኒካልና ኦፕሬሽናል ድጋፍ ተደርጓል፤
- ❖ የፌዴራል፣ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች የገቢ ተቋማት እና የፋይናንስና ገቢ ዘርፍ ተቋማት የጋራ ውይይት መደረኮች በተለያዩ ጥናቶች፣ ሪፖርቶችና አሰራሮች ዙሪያ ተደርጓል፤

- ❖ በሚኒስቴሩ መ/ቤቱ የተዘረጉ የታክስ መረጃ ቴክኖሎጂዎችን ወደ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች የገቢ ተቋማት እንዲስፋፉ ማስተዋወቅ፣ ማሰልጠን እና ሁኔታዎችን ከማመቻቸት አንፃር የሲዳማ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ፣ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ እና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች የገቢ ተቋማት ወደ ቀርጥ ግብር በኢ-ፔይመንት እንዲሰባስቡ የሚያስችላቸው ስልጠና በመስጠት ወደስርዓቱ ገብተዋል፤
- ❖ በታክስ ህጎች እና በጋራ ገቢ አስተዳደር አፈፃፀም ዙሪያ የወርክሾፕ መድረኮች በማዘጋጀት ውይይት ከማድረግ አንፃር የመርከቶና አከባቢዋ የደረሰኝ ጥናት፣ የመሬት መጠቀሚያ ክፍያና የግብርና ገቢ ግብር ረቂቅ አዋጅ፣ በፋይዳ ስርኣት ዙሪያ ውይይት ተደርጓል፤
- ❖ የተዘረገው የክልሎች እና የፌዴራል ቅ/ፅ/ቤቶች የስምምነቱ ተግባራዊ እንዲሆንና በመካከላቸው ያለው መልካም የስራ ግንኙነት ስርዓት አፈፃፀም፣ የመረጃ ቅብብሎሽ፣ የፋይዳ አተገባበር ዙሪያ በዙም በመገምገም ምክረ-ሀሳብ ተሰጥቷል፣
- ❖ የመግባቢያ ሰነድ በገቢዎች ሚኒስቴር በሚኒስትር እና በቢሮዎች ኃላፊዎች ደረጃ እንዲሆኑ ተሻሽሎ ተዘጋጅቶ ግብዓት የተሰበሰበት ይገኛል፤

❖ ኦሮሚያ፣ሶማሌ፣ደቡብ ኢትዮጵያ እና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች የግብርና እና የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ አዋጅ እንዲያወጡ ተደርጓል።

❖ በፌዴራል ደረጃ ለማልማት በሂደት ላይ ባለው የታክስ ስርዓት የማዘመን ስራዎች፤ በኤሌክትሮኒክስ ኢንቮይስ፣በዳታዌርሀወስ እና / E-invoice, Data ware house, Business Intelligent/ ከክልሎች ጋር ፍላጎት እንዲጣጣም ተደርጓል፣

❖ የታክስ ከፋዮች ምዝገባ ባዮሜትሪክ መረጃ ከፋይዳ ሲስተም በኩል እንዲጣጣም ተደርጓል፣

❖ በአዲስ አበባና ዙሪያው የሚስተዋለውን ከደረሠኝ ጋር የተያያዙ ችግሮችን በተመለከተ ግምገማ አድርጎ የመፍትሄ እርምጃዎችን የሚያቀርብ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ ከኦሮሚያ እና ከፌዴራል ገቢ ተቋማት የተውጣጣ የባለሙያዎች ቡድን ሥራውን አጠናቅቆ ሰነዱ ለክልሎችና ከተማ አስተዳሮች የጋራ መድረክ ላይ ቀርቧል።

❖ የአማራ ክልል አሁናዊ የገቢ አሰባሰብ በተመለከተ የአጭር የዳሰሳ ጥናት ተዘጋጅቶ ቀርቧል፣

❖ በመርካቶና በአካባቢው የደረሰኝ አስተዳደር ችግሮችን በሚመለከት ከፌዴራል፣ ከአዲስ አበባ እና ኦሮሚያ በጋራ በተቋቋመ የባለሙያ ቡድን አማካኝነት ተጠንቶ የቀረበው ጥናት ላይ የተመለከቱ ምክረ-ሀሳቦችን ተግባራዊ የሚያደርግ የጋራ አቢይ እና ቴክኒካል ኮሚቴዎች እንዲቋቋሙ ተደርጓል፣

❖ ህገ-መንግስቱን በተገቢው ሁኔታ ካለመረዳት የአንዳንድ ክልሎች የታችኛው እርከን ከፌዴራል መንግስት ታክስ ከፋዮች ግብር/ታክስ ለማስከፈል ጥረት ሲያደርጉ በተለያዩ ጊዜ ማብራሪያዎች ተሰጥቷል፣

## 2.6 የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ክትትል ሥራዎች አፈጻጸም

ለ6,153 ሠራተኞች በሥነ-ምግባራዊ አመራር፣ በመልካም ሥነ ምግባርና የሞራል እሴት ግንባታ፣ በሙስና ጽንሰ ሀሳብ፣ በሙስና ምንነት፣ መንስኤዎች፣ በንግድ ሥነ-ምግባር፣ በሙስና ወንጀሎች 881/2007፣ በሥነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 136/2010 እና በሠራተኞች አስተዳደር ደንብ 155/2000፣ በንብረት እና በዓመት እረፍት አጠቃቀም፣ በመጥፎና መልካም ሥነ-ምግባር መገለጫዎች፣ በሥነ-ምግባር ደንብ ምንነትና ጥቅም፣ በመሠረታዊ የሥነ-ምግባር መርሆዎች፣ በሙያ ሥነ-ምግባር፣ በንግድ ሥነ-ምግባር እና በጥቆማ አቀራረብ ወዘተ ርዕሶች ዙሪያ ለዋናው መ/ቤትና ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

በዋናው መ/ቤት እና በቅ/ጽ/ቤት ለሚገኙ ለሁሉም አዲስ እና ነባር በጠቅላላው ለ 32 (16 ወ፣ 16 ሴ) የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል አመራርና ባለሙያዎች ለአራት ተከታታይ ቀናት ስለክፍሉ አጠቃላይ ሥራዎች የክህሎት ማጎልበቻ ስልጠና በክፍሉ አቅም ለመስጠት ተችሏል፡፡

ለ641 ከፌዴራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጋር በመተባበር ለዋናው መ/ቤትና በአዲስ አባባ ውስጥ ለሚገኙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ቡድንና ከዚያ በላይ ላሉ አመራሮች ሥነ-ምግባራዊ ሞራል በሚል ርዕስ ዙሪያ ለሁለት ቀናት ሥልጠና የተሰጠ ሲሆን በአጠቃላይ 6,794 ሠራተኞችና ለግብር ከፋዮች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

አለም ዓቀፍ የፀረ ሙስና ቀንን ሚኒስትር መ/ቤቱ ከጉምሩክ ኮሚሽን ጋር በመቀናጀት ለሚኒስቴሩና የኮሚሽኑ ከፍተኛ አመራሮች እና ሠራተኞች በአጠቃላይ 333 (ወ ፣ 207፣ ሴ 126) በዓለም ለ20ኛ ጊዜ በሀገራችን ደግሞ ለ19ኛ ጊዜ "ሙስና የጋራ ጠላታችን ነው፤ በሕብረት እንታገል!" በሚል መሪ ቃል ለዉይይት መነሻ የሚሆን ፓወር ፖይንት በፀረ ሙስና ኮሚሽን ቀርቦ ውይይት በማድረግ በዓሉ በደመቀ ሁኔታ የተከበረ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ሁሉም የገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በአጠቃላይ 4,575 ሠራተኞች በተገኙበት በዓሉን በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲያከብሩ ተደርጓል፡፡

የሥነ-ምግባርና የሙስና መከላከል ብሮሸሮች እና ፖስተሮች አዘጋጅቶ ለሰራተኞች እና ለግብር ከፋዮች ከማሰራጨት አንጻር በበጀት ዓመቱ በተለያዩ 5 ዋና ዋና አርዕስቶች የተዘጋጁ ብሮሸሮች ለ8,145 የተቋሙ አመራርና ሠራተኞች እንዲሁም ለተለያዩ ግብር ከፋዮች በተለያዩ ርዕሶች ማለትም በገቢው ዘርፍ መልካም ሥነ ምግባር የተላበሰ አገልግሎት አሰጣጥ፣ በግዥ ሂደት ተሳትፎ ያላቸው ሠራተኞች የሚጠበቅባቸው ሥነ ምግባር፣ የሥራ ላይ ሥነ-ምግባር፣ በሥነ-ምግባር ደንቡ ላይ በተደነገጉ ክልከላዎችና የጥቅም ግጭት፣ በሙስና ጽንሰ ሀሳብ፣ በሀብት ማሳወቅና ምዝገባ፣ በተገልጋዮች እና በሠራተኞች መብትና ግዴታዎች እና በጥቆማ አቀራረብ ዙሪያ ብሮሸሮችን በማዘጋጀት እንዲሰራጩ ተደርጓል፡፡

ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል ተገልጋዮች እና ሠራተኞች ጥቆማዎችን ማቅረብ የሚችሉበትን የጥቆማ መስጫ ሳጥኖች፣ የጥቆማ ማቅረቢያ ቅጻ ቅጾች፣ የቢሮ ስልኮች፣ የቴሌግራም ገጾች፣ ኢሜይል፣ ኤሌክትሮኒክ የድምጽ አስተያየት/ጥቆማ መስጫ መሳሪያ/ሳጥን ግልጽና አመቺ በሆኑ ቦታዎች ላይ የማስቀመጥና የማስተዋወቅ ሥራ ተሰርቷል፡፡

በበጀት ዓመቱ 430 የመጀመሪያ ሀብት ምዝገባ፣ 660 ሰራተኞች የዕድሳት ሀብት ምዝገባ ሲያደርጉ 71 ሠራተኞች ደግሞ የአገልግሎት ማቋረጥ ሀብት ማሳወቅና ምዝገባ እንዲያከናውኑ በማድረግ የክሊራንስ አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ በውስጥ እና በውጭ የኦዲት ግኝቶች ላይ በተደረገ ክትትል እርምጃ የተወሰደባቸው በስጋት ደረጃቸውና ሊያስከትሉት በሚችሉት ጉዳት በመለየትና ቅደም ተከተል

በመስጠት ትኩረት ተሰጥቶ በግኝቶች ላይ ክትትል ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም 90 ሠራተኞች የሥነ-ምግባር ሁኔታ ተጣርቶ ለሰው ሀብት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት ተላልፏል፡፡

በዋና መ/ቤት እና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በተለያዩ የሥራ ክፍሎች የሚስተዋሉ የህግና የአሠራር ክፍተቶችን ማለትም በመዝገብ ቤት አሰራር ዙሪያ፣ በባለልዩ መብት ተመላሽ በመዝገብ ቤት የፕሮቶኮል መዝገብ ላይ ቁጥር ሳይሰጠው በባዶ ተመላሽ የሚጠየቅበትን አግባብ በተመለከተ፣ በግዥ አፈጻጸም አሰራር ላይ፣ በኤሌክትሮኒክስ ክፍያ አፈፃፀም ላይ በተስተዋሉ ክፍተቶች ላይ፣ በዓመት እረፍት ፈቃድ አሰጣጥ አሰራር ላይ ፣ የሠራተኞች የሥነ-ምግባር ወቅታዊ ሁኔታን አስመልክቶ፣ በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የቁጥጥር ስልትና የሕግ ተገዥነት የአሰራር ሥርዓትን በዳሰሳ ጥናት በመለየት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ሲቀርቡ በገቢው ዘርፍ ላይ የተደረገውን የሙስና ስጋት የዳሰሳ ጥናት ግኝቶች ላይ፣ በታክስ ኦዲት አሰራሮች ላይ የስጋት ተጋላጭነት፣ የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት የገቢ አሰባሰብና ክሊራንስ አሰጣጥ አሰራርን በተመለከተ፤ በታክስ ከፋዮች መረጃ ማቅረቢያ ጥራት በታክስ መግለጫ ላይ ያለው ተጽዕኖ፣ በሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሉ በኩል የተሰጡ የሥነ-ምግባር ስልጠናዎች በሰራተኛው ላይ ያመጡትን ለውጥ፣ በታክስ ኦዲት የሥራ ሂደት አሰራር ላይ፣ በአንድ ቅ/ጽ/ቤት የግብር ከፋዮች ፋይል ትውስትና አመላለስ ስርዓትን በተመለከተ እና የተቋሙ ሰራተኞች ሥነ-ምግባር ደንብ ውጤታማነት ላይ ጥናት ተደርጎ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ለማሳወቅ መረጃዎችን የማሰባሰብ፣ የመተንተን እና የማጠናቀር ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ ውስጥ ተጠንተው ከተጠናቀቁ ጥናቶች መካከል አስሩ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው የሥራ ክፍል በማስተላለፍ አፈፃፀሙን የመከታተል ሥራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

የሥነ-ምግባር ማስገንዘቢያና የሙስና መከላከል መልዕክቶችን በማዘጋጀት በማህበራዊ ሚዲያዎች 799 መልዕክቶችን የተሰራጨ ሲሆን ለአብነትም መብቶን በገንዘብ አይግዙ፣ የስነ-ምግባር መርሆች፣ መልካም ሥነ-ምግባር የህይወታችን መመሪያ ይሁን፣ የንግድ ሥነ-ምግባር፣ በሞራል ዕሴቶች፣ በሙስና ወንጀሎች 881/2007፣ በሀብት ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 668/2008፣ በፀረ ሙስና ትግል፣ በመልካም ሥራ፣ የሙስና የመልካም አስተዳደር እና የኢኮኖሚ እድገት ፀር መሆኑን፣ በግዥ ሂደት ከሚሳተፉ ባለሙያዎች የሚጠበቅ ሥነ-ምግባር ለሠራተኛ የተከለከሉ ተግባራት፣ የሥነ-ምግባር ጥፋቶች፣ የሥራ ሥነ-ምግባር፣ የጥቆማ አቀራረብ፣ የጥቅም ግጭት፣ በመልካም ሥነ-ምግባር ማገልገል ድርብ ክብር መሆኑን፣ የሞራል ዕሴቶች፣ የፀረ-ሙስና ትግል ወዘተ በሚል ርዕሶች የተዘጋጁ መልዕክቶች በማህበራዊ ሚዲያዎች (በቴሌግራምና በሬዲዮ) እንዲሰራጩ ተደርጓል፡፡

የሙስናና ብልሹ አሠራር ጥቆማዎችን በማጣራት እና የክትትል ሥራዎች በመስራት የተወሰዱ የዲሲፕሊን ዕርምጃዎችን በተመለከተ 18 ሠራተኞች የተለያየ ጥፋት ፈጽመዉ በመገኘታቸዉ ከሥራ እንዲሰናበቱ ፤6 ሠራተኞች በደረጃና ደሞዝ እንዲቀጡ ፤14 ሠራተኞች በደሞዝ እንዲቀጡ፣ 15 ሠራተኞች የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጣቸው፣15 ሠራተኞች የቃል ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው፤3 ሠራተኞች በፈፀሙት ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት የዲስፕሊን ክስ የተመሰረተባቸው እና 14 ሠራተኞች ጥቆማ ቀርቦባቸው በሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሉ በኩል የማጣራት ሥራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

በዋናው መ/ቤትና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የወንጀል ጉዳዮች ሲያጋጥሙ የመመርመር ስልጣን ላላቸው አካላት ከማስተላለፍ አኳያ 21 ጉዳዮች ተጨማሪ ምርመራ ተደርጎባቸው ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ለማድረግ ለፌደራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ቢሮ የማስተላለፍ ስራ ተሰርቷል፡፡

## የጉምሩክ ኮሚሽን የሥነ-ምግባር እና ፀረ ሙስና የክትትል ሥራዎች አፈጻጸም፡-

በአስራ ሁለት ወራት 20 ለብልሹ አሰራር የተጋለጡ አሰራሮች በጥናት በመለየት የማሻሻያ ሀሳብ ለማቅረብ ታቅዶ 26 የአሰራር ክፍተቶች ላይ ጥናት በመከናወኑ አፈፃፀሙ 130 በመቶ ሆኗል፡፡ ለብልሹ አሰራር ክፍተት ይፈጥራሉ ተብሎ በጥናት ከተለዩ 107 የአሰራር ክፍተቶች ላይ ክትትል በማድረግ 66 (61.68%) ክፍተቶች ላይ ሙሉ በሙሉ እርምጃ ተወስዷል፤ይህም በዕቅድ ከተያዘው 90 በመቶ አኳያ አፈጻጸሙ 68.53 በመቶ ሊሆን ችሏል፡፡ እንዲሁም ከተለያዩ አካላት የቀረቡ ጥቆማዎችን መሠረት በማድረግ በስታንዳርዱ መሰረት በማጣራት እና አስፈላጊውን እርምጃ በመውሰድ ተቋሙ ሊያጣ የነበረውን ብር 8,173,024.49 ሙስና ቀድሞ ማምከን ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በዋና መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች 26 ስጋቶች ላይ የአሰራር ዳሰሳ ጥናት የተደረገ ሲሆን 5 ስጋቶች ላይ ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ጋር በጋራ በመገምገም ስጋቶቹ እንዲፈቱ ተደርጓል፡፡

**ሰንጠረዥ 3፡- የ2016 በጀት ዓመት የ12 ወራት የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድ አፈጻጸም**

| ተ.ቁ | የዲሲፕሊን እርምጃ ዓይነቶች | እርምጃ የተወሰደባቸዉ | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር | |
| 1 | ከስራ የተሰናበቱ | 55 | 9 | 64 | • በከባድ ዲሲፕሊን ጥፋት በአንቀጽ 30/1/ሠ መሠረት 10 ወንድ፣ 1 ሴት ሠራተኛ፣<br>• ተደጋጋሚ ጥፋት በአንቀጽ 32/2 መሰረት 4 ወንድ፣ 3 ሴት ሠራተኛ፣<br>• በሙከራ ቅጥር ከባድ የስነ ምግባር ችግር በአንቀፅ 14/3 ወንድ 18፣<br>• በእስራት ምክንያት ስንብት በአንቀጽ 41 መሰረት 3 ወንድ ሠራተኛ እና<br>• በሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ 1064/2010 አንቀጽ 94/1 ወንድ 20 ሴት 5፤<br>• በአጠቃላይ 64 ሰራተኞች ከስራ ተሰናብተዋል፡፡ |
| 2 | ከባድ የዲሲፒሊን ቅጣት | 82 | 22 | 104 | • እስከ 2 ዓመት ከደረጃና ደመወዝ ዝቅ የተደረጉ 14(10 ወንድ እና 4 ሴት) እና እስከ 4 ወር በሚደርስ የደመወዝ መቀጮ 90 (72 ወንድ እና 18 ሴት) ሠራተኞች፤<br>• በአጠቃላይ 104 ሠራተኞች በከባድ ዲሲፒሊን ተቀጥተዋል፡፡ |
| 3 | ቀላል የዲሲፒሊን ቅጣት | 209 | 67 | 276 | • የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ 145 (115 ወንድ እና 30 ሴት) ሠራተኞች እና የቃል ማስጠንቀቂ 131(94 ወንድ እና 37 ሴት) ሠራተኞች፤<br>• በአጠቃላይ 276 ሠራተኞች በቀላል ዲሲፒሊን ተቀጥተዋል፡፡ |
| | ጠቅላላ ድምር | 346 | 98 | 444 | |

ከላይ በሰንጠረዥ 3 ላይ እንደተመለከተዉ በዋና መ/ቤትና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በቀረቡ ጥቆማዎችና መረጃዎችን መሰረት በማድረግ በስነ ምግባር ችግር ምክንያት ከስራ የተሰናበቱ 64፣ በከባድ ዲሲፒሊን የተቀጡ 104 እና ቀላል ዲሲፒሊን እርምጃ የተወሰደባቸዉ 276 ሰራተኞች ሲሆኑ በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ 444 ሰራተኞችና አመራሮች ላይ የዲሲፒሊን እርምጃ ተወስዷል፡፡

በበጀት ዓመቱ በኮሚሽ ደረጃ የሀብት ምዝገባ 95 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ የመጀመሪያ የሀብት ምዝገባ እና ዕድሳት ያከናወኑ 1,909 አመራሮችና ሰራተኞች ሲሆኑ እስካሁን ድረስ መመዝገብ ካለባቸው አመራርና ፈጻሚዎች 9,081 ውስጥ 7394 (81.42%) የመጀመሪያ ማኑዋልና የዲጂታል ሀብት ምዝገባ በማከናወን የዕቅድ አፈጻጸሙን 85.70 በመቶ ማድረስ ችሏል፡፡

ሰንጠረዥ 4፡- የአስራ ሁለት ወራት የሀብት ምዝገባ አፈጻጸም መረጃ

| ተ.ቁ | የሀብት ምዝገባ አይነት | ሀብት ያስመዘገቡ ሠራተኞች ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር |
| 1 | የመጀመሪያ ማኑዋል ሀብት ምዝገባ | 695 | 343 | 1,038 |
| 2 | የዕድሳት ማኑዋል ሀብት ምዝገባ | 829 | 403 | 1,232 |
| 3 | የአገልግሎት ማቋረጥ ማኑዋል ሀብት ምዝገባ | 449 | 457 | 906 |
| 4 | የኮንትራት ማቋረጥ ማኑዋል ሀብት ምዝገባ | 29 | 16 | 45 |
| ንዑስ ድምር | | 1572 | 772 | 2,344 |
| እስካሁን ድረስ ሀብት ያስመዘገቡ ሠራተኞች | | 4167 | 3227 | 7394 |

## 2.8. የሴቶችና ማህበራዊ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማሻሻል አፈጻጸም

የሴት ሰራተኞችን የመፈጸም፣ የመወሰንና ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ በ2016 በጀት ዓመት በበጀት ዓመቱ በዋናው መ/ቤትና በከፍተኛ፣ መካከለኛ ቁጥር 1 እና 2፣ በምስራቅ፣ ሰሜን ምዕራብ ፣ መቀሌ፣ በኮምቦልቻና በጅማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ለሚገኙ 1,683 ሴት አመራሮችና ሠራተኞች፣ ለ527 ወጣት ሰራተኞች በድምሩ ለ2,210 ሰራተኞች የተሻለ በራስ መተማመን ያለው ስብዕና ግንባታ፣ በአመራር ክህሎት፣ በስሜት ብልህነት፣ በአስተዳደር ክህሎት፣በአስተሳሰብ ለውጥ፣ በህይወት ክህሎት፣ በደንበኞች አያያዝ ዙሪያ፣ በአካቶ ትግበራ፣በማህጸን በር ካንሰር ቅድመ ምርመራ ግንዛቤ ማስጨበጫ፣ በታክስ ህጎችና ስለታክስ ጥቅምነት ዙሪያ በተለያዩ ጊዜያት ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም በመካከለኛቁጥር 1 ቅ/ጽ/ቤት ለ120 ሴት ግብር ከፋይ ሴት ስራአስኪያጆች እና ሂሳብ ኃላፊዎች በታክስ ህጎች ላይ ስልጠና ተሰቷል፡፡

ለ14 በዝቅተኛ የስራ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሴት ሰራተኞች Level 1 COC ለመፈተን እና ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያደርግ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

የሥራ ክፍሎች የሥርዓተ ጾታ፣ የህጻናት፣ የአካል ጉዳተኞች እና ወጣቶች ጉዳዮች የዕቅዳቸው አካል አድርገው እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡ በቅጥርና በደረጃ ዕድገት ወቅት የሴቶች እና አካል ጉዳተኞች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ በቅ/ጽ/ቤቶችም አገልግሎት ጠይቀው ለሚመጡ አካል ጉዳተኞች ቅድሚያ የሚያገኙበት ሁኔታ ተመቻችቷል፡፡

በዋናው መ/ቤት በሚገኘው የሴቶች ፎረም አማካኝነት 50 ተማሪዎችን የማስተማር ስራ እየተሰራ ነው፡፡

በዋናው መ/ቤት ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የተደራጁ ወጣቶችና ሴቶችን በመደገፍ ለሠራተኞች የመሰረታዊ ፍጆታ ስኳር፣ ፓስታ፣ ዘይት እና ዱቄት የማቅረብ እንዲሁም ለሰራተኞች የኑሮ ውድነትን ለመደጎም ከፐርፐዝ ብላክ ጋር በመነጋገር በዝቅተኛ ዋጋ አስቤዛ በማስመጣት የማከፋፈል ሥራ ተሰርቷል፡፡

በተጨማሪም አነስተኛ ገቢ ያላቸውን ሰራተኞች ተጨማሪ የገቢ ምንጭ የሚያገኙበትን ሁኔታ ለማመቻቸት በአዲስ መልክ 15 ሴቶች በሻይ ቡና አቅርቦት እንዲደራጁ ተደርጓል፡፡

በሀገር አቀፍ ስፖርት ለሁሉም ከሁሉም መ/ቤቱ ከፌዴራል መስርያ ቤቶች ጋር ለሚደረገዉ ውድድር በእግር ኳስ አራተኛ ደረጃ፣ በጠረጴዛ ቴኒስ በሴቶችና በወንዶች አንደኛ ደረጃነትን በመያዝ የወርቅ ሜዳልያ የተገኘ ሲሆን በቼዝ ጨዋታ ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ ተጠናቋል ፡፡ በተጨማሪም የአገርህን እወቅ ክበብ አባላት ጋር በውስጥ የረቂቅ ደንብ ዙሪያ ውይይት በማድረግ ደንቡ እንዲጸድቅ ተደርጎ ወደ ሥራ ተግብቷል፡፡

በተቋሙ የሥርዓተ-ጾታ አተገባበርን በተመለከተ ደረጃ ለመስጠት ኮሚቴ በማዋቀር አስር ቀን አዳማ በመገኘት ሥራዎችን በማስገምገም እና ደረጃ የማሰጠት ስራ ተከናውኗል፡፡

በተቋም ደረጃ አለማቀፍ የሴቶች ቀን (ማርች8) መሪ ቃሉን ለሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በመላክ በሥልጠና፣ በሴቶች እሩጫ እና የበጎ አድራጎት ሥራዎችን በመስራት በደማቅ ሁኔታ ተከብራል፡፡

**ከህጻናት ማቆያ እና ሌሎች ተያያዥ ስራዎች ጋር በተያያዘ የተከናወኑ ሥራዎችን በተመለከተ፡-** በዋናው መ/ቤት እና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የህጻናት ማቆያ ላይ አገልግሎት የሚያገኙ በ10 የህጻናት ማቆያ ማዕከል ውስጥ 285 ህጻናት አገልግሎት እያገኙ ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በባህር ዳር ከተማ ካሉት የህፃናት መዋያ ማዕከል የተሻለ አደረጃጀት ያላቸውን ተቋማት የአብክመ ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ሱፐርቪዥን በማድረግ ሽልማት በማዘጋጀት ሰኔ 8/2016 ዓ.ም የአፍሪካ ህፃናትን ቀን አስመልክቶ በተዘጋጀው ፕሮግራም የዋንጫና ሰርተፊኬት ሽልማት ተሸላሚ ተሆኗል፡፡

በተጨማሪም ከሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር ዋናው መ/ቤትና ቅ/ጽ/ቤት ለሚገኙ ሴቶችና ህጻናት ላይ ለሚሰሩ 4 ባለሙያዎች ለ6 ወር የሱፐርቫይዘር ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጎ የማስመረቅ፣14 የህጻናት ተንከባካቢ ባለሙያዎች ለ6 ወር ቅዳሜ ቅዳሜ ስልጠና እንዲወስዱ የማድረግ፤ PFC እና ከሴቶችና ማህበራዊ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ለ56 ወላጆች በህፃናት አመጋገብ እና አስተዳደግ ዙሪያ ስልጠና የመስጠት እና የዋናው መ/ቤትና የቅርንጫፍ ጽ/ቤት የህጻናት ማቆያ ሞዴል ተደርጎ በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ተመርጦ አስር የቴክኒክ ቡድን ባለሙያዎች ተልከው ከመጋቢት 2016ዓ.ም እስከ ታህሳስ 2017 ዓ.ም ድረስ ስልጠናና የማማከር አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡

በኮሚሽኑ በበጀት ዓመቱ 202 ሰራተኞች የህጻናት ማቆያ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል ታቅዶ 272 ሰራተኞች የህጻናት ማቆያ ተጠቃሚ በመሆናቸው የዕቅድ አፈፃፀም 134.65 በመቶ ሊሆን ችሏል፡፡ የህጻናት ማቆያ ከጅግጅጋ እና ከሰመራ ቅ/ጽ/ቤቶች በስተቀር በዋና መ/ቤትና በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

በኮሚሽኑ ካሉ ጠቅላላ 9,081 ሠራተኞች መካከል 3,858 ወይም 42.48% በሴት ሠራተኞች የተሸፈነ ነው፡፡ በኮሚሽን ደረጃ ሴቶችን በማብቃት ወደ አመራርነት ከማምጣት አንፃር የሴቶችን ሽፋን 32 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ 22 በመቶ በሴት አመራሮች በመሸፈኑ የዕቅድ አፈፃፀሙ 68.75 በመቶ ሊሆን ችሏል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለአመራር ብቁ ናቸው ተብሎ የሚታሰቡ የ115 ሴት ሠራተኞች መረጃ የማሰባሰብ ስራ ተሠርቷል፡፡

የሴት ሰራተኞች አቅም ለማጎልበት በበጀት ዓመቱ አጠቃላይ ሥልጠና ከሚወስዱ ሰራተኞች ዉስጥ የሴት ሰራተኞች ድርሻ 44 በመቶ እንዲሆን ታቅዶ እስካሁን በአጠቃላይ ስልጠና ከወሰዱ 6,106 ሰልጣኞች ዉስጥ 2,779 (45.51%) ሴቶች በመሆናቸዉ የሴት ሰራተኞችን አቅም የማጎልበት ዕቅድ አፈፃፀም 103.43 በመቶ ሊሆን ችሏል፡፡ በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ 95 በመቶ ለአካል ጉዳተኛ ሰራተኞች እና ተገልጋዮች ምቹ የስራ ሁኔታና ቦታ ለመፍጠር የታቀደ ሲሆን እስካሁን ለ50 በመቶ ምቹ የስራ ሁኔታ እና ቦታ በመፈጠሩ የዕቅድ አፈፃፀም 52.63 በመቶ ሊሆን ችሏል፡፡

በዋና መስሪያ ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው 57 ሴት ሰራተኞች ተደራጅተዉ ገቢያቸዉን እያሳደጉ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ለ10 ሰራተኞች በገቢ ማስገኛ ስራዎች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በተጨማሪም ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው 50 (38 ሴትና 12 ወንዶች) ሠራተኞች ሙሉ ወጪያቸውን በመሸፈን ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ አስፈላጊው እየተደረገ ይገኛል፡፡

## 2.9. የበጎ አድራጎት እና የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎች አፈጻጸም

- ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 5 ድረስ ላሉ ሰራተኞች የአዲስ ዓመት በዓል ምክንያት በማድረግ ለ1,646 የተቋሙ ሠራተኞች በ9,002,818.54 ብር ተገዝቶ ለእያንዳንዳቸው የ50 ኪሎ ጤፍ ድጋፍ በተቋሙ በኩል ተደርጓል፡፡
- ለዋናው መ/ቤት 149 ሠራተኞች የትምህርት መሳሪያ ዋጋ በመጨመሩ ምክንያት ሰራተኞቹ መቸገራቸውን ገልጸው እንዲቀርብላቸው በጠየቁት መሰረት 4428 ደብተሮችን ከአስመጪዎች በማምጣት በዝቅተኛ ዋጋ በማከፋፈል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡
- በዋና መ/ቤት በቫይረሱ ለተያዙ ድጋፍና እንክብካቤ ለሚደረግላቸው 16 ሰራተኞችና ቤተሰቦቻቸው፣ ከቦሌ ክ/ከተማ ተቋሙ ለተቀበላቸው 8 ህጻናት፣ በአጠቃላይ ለ24 ተረጂዎች የተደረገ የድጋፍ ገንዘብ ክፍያ ብር 189,800 ከኤድስ ፈንድ ወጭ ሆኖ ተከፍሏል፡፡
- ከ12 ቅ/ጽ/ቤቶች ውስጥ ለተረጂዎች የተደረገ ድጋፍ 961,000 በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ ለ83 ህጻናት እና ለ29 ሠራተኞች በድምሩ ለ112 ተረጂዎች 1,150,800 በቋሚ ድጋፍ ወጪ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በጊዜያዊነት ለአረጋዊያንና የአዕምሮ ህመምተኞች፣ለኤች አይቪ ህመምተኞች፣ለአዲስ ዓመትና ለተማሪዎች የት/ቤት ቁሳቁስ ግዥ፣ የማህበራዊ ችግር ላጋጠማቸውው ሠራተኛ ብር 399,136 ወጪ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም አነስተኛ ገቢ ላላቸው ሰራተኞች ብድር 45,000 ተሰጥቷል፡፡
- በተቋም ደረጃ በፈቃደኝነት ከደም ባንክ ጋር በመነጋገር 267 ሰራተኞች ደም እንዲለግሱ ተደርጓል፡፡በተጨማሪም ከሰራተኞች ላይ ከሚቆረጠው በኤች አይቪ ፈንድ 77 ህጻናት እንዲማሩ እየተደረገ ይገኛል፡፡
- ከሰራተኛ 0.5% የተቆረጠውን ወደ የኤች.አይ.ቪ እንዲገባ ከማድረግ አኳያከ13 ቅ/ፅ/ቤቶች ከሰራተኞች ደመወዝ ብር 1,824,869.25 እና ከዋና መ/ቤት ብር 366,011.3 በድምሩ ብር 2,190,880..55 ገቢ መሆኑን ክትትል ተደርጓል፤ በተጨማሪም በኦዲት ግኝት ያለ አግባብ የወጣ ብር 29,700 ተመላሽ ሆኗል፡፡
- የሰራተኞች የስኳር እና የደም ግፊት መጠን ልኬት በማከናወን የልኬት መጠናቸው ከፍ ብሎ ለታየ የምክር አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡በተጨማሪም ለ15 ሰራተኞች የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ/የደም መፍሰስን ማቆም ቁስል ማሸግ/ ተግባራት ተከናውኗል፡፡
- የመካከለኛ ቂጥር 1 ቅ/ጽ/ቤት ሠራተኞች ለመቄዶኒያ የአረጋዊያን መረጃ ማዕከል በፈቀዳቸው ቀጣይነት ባለው መልኩ ከወር ደመወዛቸው ተቆራጭ በማድረግ 45,239.05 በመሰብሰብ ገቢ

ሲያደርጉ የኮንቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት ሠራተኞች ደግሞ ሶፍት፣ ሳሙናና አልባሳት ግምታቸው ብር 17,750 /አስራ ሰባት ሺ ሰባት መቶ ሀምሳ / የሚሆን ድጋፍ አድርገዋል፡፡ በተጨማሪም በተለያዩ ችግር ውስጥ ላሉ ትምህርት ቤቶች ለህጻናት ትምህርት መማሪያ ደብተርና እስኪሪብቶ ግምቱ ብር 17,835 /አስራ ሰባት ሺ ስምንት መቶ ሰላሳ አምስት/ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

- ጅማ ቅ/ጽ/ቤት ለሰራኞች የንጽህና መጠበቂያ፣ አልባሳት፣ የምግብ ፍጆታ እቃዎች ግምቱ 102,291.50/ አንድ መቶ ሁለት ሺ ሁለት መቶ ዘጠና አንድ ከሀምሳ ሳንቲም/ ብር የሚሆን ለሚሽን ኦፍ ቻርቲ የበጎ አድራጎት ድርጅት ድጋፍ የተደረገና ማህበራዊ ኃላፊነት ከመወጣጥ አኳያ ደግሞ ሁለት ሰራተኞች ባጋጠማቸው ማህበራዊ ችግር ምክንያት በአመራርና ሰራተኞች 191,730 /መቶ ዘጠና አንድ ሺ ሰባት መቶ ሰላሳብር / ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- መካከለኛ ቁጥር 1 ቅ/ጽ/ቤት ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀንን በማስመልከት ለጌርጌሴኖን የአዕምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል ከሰራተኞች የተለያዩ አልባሳት፣ የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችንና በጥሬ ገንዘብ በአጠቃላይ ከአንድ መቶ ሺህ(100,000) ብር በላይ የሚገመት ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም በምስራቅ አነስተኛ ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት ለሜሪጆይ ኢትዮጵያ ግምታቸው 38,500/ሰላሳ ስምንት ሺ አምስት ብር/ የአይነት ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- በገቢዎች ሚኒስቴር እና ጉምሩክ ኮሚሽን በጋራ በ2016 በጀት ዓመት የአረንጓዴ አሻራ ተግባራትን በማካሄድ 25,000 ችግኞችን ለመትከል የታቀደ ሲሆን 33,330 ችግኞች በመተከላቸው የዕቅድ አፈጻጸሙ 133.32 በመቶ ሊሆን ችሏል፡፡ ይህም ከገቢዎች ሚኒስቴር ጋር በጋራ በመሆን በወልመራ ወረዳ የኮሚሽኑ አመራሮችና ፈጻሚዎችን በመተባበር የችግኝ ተከላ ስራ የተሰራ ሲሆን ችግኞቹም እንዲፀድቁ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በቅንጅት እየተሰራ ይገኛል፡
- በኮሚሽኑ በጀት ዓመቱ ስድስት የአቅመ ደካማ ማህበረሰቦች የመኖሪያ ቤቶችን ለመገንባት/ለማደስ ታቅዶ 11 መኖሪያ ቤቶች ተገንብተው ለአቅመ ደካሞች የተላለፉ በመሆኑ የዕቅድ ክንውኑ 183.33 በመቶ ሊሆን ችሏል፡፡ ለዚህ ተግባር የሚውል 6 ሚሊዮን ብር የታቀደ ሲሆን ብር 6.5 ወጪ በማድረግ የዕቅድ አፈፃፀም 108.33 በመቶ ሊሆን ችሏል፡፡
- በበጀት ዓመቱ ለ1000 የአቅመ ደካማ ቤተሰብ ተማሪዎችን ለመደገፍ ታቅዶ የተለያዩ የትምህርት ቁሳቁሶች በመግዛት ለ4000 ተማሪዎች ድጋፍ የተደረገ ሲሆን ለይህ ተግባር 3,000,000.00 ብር የሚተመን ገንዘብ ለማውጣት ታቅዶ ብር 2,600,528.00 ወጪ በመደረጉ የእቅድ አፈፃፀሙ 86.67 በመቶ ሊሆን ችሏል፡፡
- ለተለያዩ ማህበራዊ ቀውሶች 1,339.49 ሚሊዮን ብር ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ብር 1,135.48 ሚሊዮን ብር ድጋፍ በመደረጉ አፈፃፀሙ 84.77 በመቶ ሊሆን ችሏል፡፡ ይህም በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግር ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች አገልግሎት እና ለተለያዩ መንግስት ተቋማት የሚውሉ ምግብ ነክ፣ የተለያዩ አልባሳት እና ጫማዎች፣ ብርድ ልብስ፣ የቤት ክዳን ቆርቆሮ እና ሌሎች ቁሳቁሶችን በማሰባሰብ እና በማደራጀት ለተለያዩ 35 ተቋማት (ብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት፣ ለከተማ አስተዳደሮች፣ ለተለያዩ በጎ አድራጎት ማህበራት፣ ለእምነት ተቋማት እና ለመንግስት ተቋማት) ድጋፍ ለማድረግ ተችሏል፡፡

ሰንጠረዥ 6፡- በኮንትሮባንድ ተይዘው ለተቸገሩ ህብረተሰብ የተደረገ ድጋፍ መረጃ

| ድጋፍ የተደረገላቸው አካላት | የተደረገ ድጋፍ ገንዘብ መጠን | የክፍፍል ድርሻ (%) |
|---|---|---|
| ለክልሎች | 794,672,668.15 | 70 |

| | | |
|---|---|---|
| ለመንግስት ተቋም | 124,998,767.00 | 11 |
| ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች | 152,795,472.60 | 13 |
| ለከተማ አስተዳደሮች | 52,976,510.00 | 5 |
| ኃይማኖት ተቋማት | 10,033,675.00 | 1 |
| ድምር | 1,135,477,092.75 | 100.00 |

በኮሚሽኑ በጀት ዓመቱ የደም ልገሳ ፕሮግራም በማዘጋጀት አጠቃላይ ካሉት ሰራተኞች 2.37 በመቶ ደም ልገሳ እንዲያደርጉ ታቅዶ 150 ሰራተኞች(1.65 በመቶ) በበጎ ፈቃድ ደም እንዲለግሱ በመደረጉ የዕቅድ አፈፃፀም 69.62 በመቶ ሊሆን ችሏል፡፡ በኤች.አይ. ቪ ኤድስ ለተያዙና በዚህ ምክንያት ወላጆቻቸዉን ያጡ ህጻናትን ጨምሮ ለ150 ሰዎች ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ለ107 ሴትና ለ89 ወንድ በድምሩ ለ204 ህፃናት ድጋፍ በመደረጉ አፈፃፀም 136 በመቶ ሊሆን ችሏል፡

# ክፍል ሦስት

## 3 በቁልፍ የውጤት አመልካቾች (KPIs) ላይ የተመሰረተ የልማት ዕቅድ አፈጻጸም

### 3.1 ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ተደራሽ የታክስና ጉምሩክ አስተዳደር ሥራዎች አፈጻጸም

### 3.1.1 የገቢ አሰባሰብ የህግ ማዕቀፎችና አሰራሮችን የማሻሻል ሥራዎች አፈጻጸም

#### ➲ የአሰራር ሥርዓት ማሻሻያ ሥራዎች አፈጻጸም

በተቋሙ በበጀት ዓመቱ 10 የአሠራር ሥርዓቶችን ለመቅረፅ/ ማሻሻያ ለማቅረብ ታቅዶ 6 የአሠራር ሥርዓቶችን መቅርጽ የተቻለ ሲሆን እነሱም የገቢ ማበረታቻ ሥርዓት ማንዋል፤ የታክስ ስሌት ማንዋል፣ የግምት አወሳሰን ማንዋል፤ የኤክሳይዝ ታክስ አፈፃፀም ማንዋል፤ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች አምራች ድርጅቶች በእጅ ያሉ ጥሬ ዕቃዎች እንቅስቃሴ መከታተያ ቅፅ እና ድርጅት ማሸግ፣ማገድና መሰረዝ አሠራር ማንዋል ተቀርጸው ለሥራ ዝግጁ ሆነዋል፡፡ በተጨማሪም በታክስ አስተዳደር ወጥ አሠራር እንዲኖር ለማስቻል ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ለክልል ታክስ ባለሥልጣናት የተላለፉ አሠራርና ማብራሪያዎችን በተመለከተ ከገንዘብ ሚኒስቴር ተወስነው የተላኩ የታክስ ጉዳዮች መመሪያዎችና የአፈፃፀም ሥርዓት 53 ጉዳዮች ፣ለግብር አወሳሰንና አሰባሰብ፣ ለተመላሽ አፈፃፀም የሚረዱ 44 የተለያዩ የአሠራር ሥርዓቶች ተዘጋጅተው ለአፈፃፀም ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የተላለፉ እና ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና ከግብር ከፋዮች ወይም ከመ/ቤቶች 110 የማብራሪያ ጥያቄዎች ቀርበው ከታክስ ሕግና ከመመሪያዎች አንፃር ታይቶ ማብራሪያ የተሰጣቸው ናቸው፡፡

#### ➲ የተከናወኑ የጥናት ሥራዎች አፈጻጸም

በበጀት ዓመቱ ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ተደራሽ የታክስና ጉምሩክ አስተዳደር ሥርዓትን ለመገንባት የሚያስችሉ የታክስ አስተዳደር አፈጻጸም ክፍተቶችን በመለየት ለማረምና አሰራሮችን ለማሻሻል የሚያስችሉ ከታች የቀረቡት ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡

- **የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አፈታት አፈጻጸም ግምገማ ጥናት ማካሄድ፦** በአሰራር ላይ ያሉ ችግሮችን መለየት፤ የተገኙ ውጤቶችን መዳሰስ እና ለችግሮች አማራጭ የመፍትሔ ሃሳቦችን ማቅረብ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የጥናት ስራው ተጠናቆ ረቂቅ ሰነዱ ለአስተያየት ቀርቦ በተሰጡ አስተያየቶች ሰነዱን በማዳበር የመጨረሻ የጥናት ሰነድ ተዘጋጅቶ በታክስ ውሳኔ ቅሬታ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት በግብዓትነት እንዲያገለግል ለሚኒስትር ጽ/ቤት፣ ለታክስ ኦፕሬሽን ዘርፍ፣ ለታክስ ሥርዓት ዘርፍና ሌሎች ለሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ቀርቧል፡፡
- **የታክስ ከፋዮች አገልግሎት አሰጣጥ እርካታ ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፡-** ተቋሙ በተቀመጠው የአገልግሎት ስታንዳርድ /ቻርተር/ መሰረት አገልግሎት እየተሰጠ ስለመሆኑ ለመፈተሽ ተገልጋዮች ያላቸውን የእርካታ ደረጃ ለማወቅ እና በተገልጋዮች የሚነሱ ችግሮችን በመለየት የተገልጋዮች እርካታን ለማሳደግ የሚያስችል ምክረ ሃሳብ ለማቅረብ ከሁሉም ቅጽ/ቤቶች በናሙና ከተመረጡ ታክስ ከፋዮች መረጃዎችን በመሰብሰብ

በመተንተን የጥናት ሰነድ ተዘጋጅቶ ውጤቱ የሚያሳየው በስታንዳርዱ መሠረት አገልግሎት ከመስጠት አንጻር በአማካይ አፈጻጸሙ በ2015 ከነበረበት 86.1% በ2016 ወደ 87% እና የተገልጋዮችን እርካታ ደግሞ በ2015 ከነበረበት 81.8% በ2016 ወደ 83.5% ከፍ ያለመሆኑ ጥናቱ አመላክቷል፡፡ ነገር ግን ምንም እንኳ አገልግሎት በስታንዳርዱ ከመስጠትና የተገልጋዩን ዕርካታ ከማሳደግ አንጻር አፈጻጸሙ እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም አሁንም በተለይ በክሊራንስ አገልግሎት፣ በታክስ ተመላሽ አገልግሎት፣ በታክስ ውሳኔ ቅሬታ አፈታት እና በኦዲት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ከአማካዩ ማለትም ከ(83.5%) በታች ዕርካታ የተመዘገበባቸው በመሆኑ ተቋሙ በቀጣይ ትኩረት ሰጥቶ እነዚህን አገልግሎቶች የበለጠ ማሻሻል የሚያስችሉ ተከታታይ ዕርምጃዎችን መውሰድ የሚጠበቅበት መሆኑን የዳሰሳ ጥናቱ አመላክቷል፡፡

- **የባለፉት 10 አመታት የተወሰዱ የታክስና የጉምሩክ አስተዳደር ማሻሻያዎች ዙሪያ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፡-** የባለፉት 10 አመታት የተወሰዱ የታክስና ጉምሩክ አስተዳደር የማሻሻያ እርምጃዎች ዙሪያ የዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ መረጃዎች ከገቢዎች ሚኒስቴርና ከጉምሩክ ኮሚሽን ተሰብስበው የትንተና ስራውን በመስራት ረቂቅ የጥናት ሰነዱ ለአስተያየት ቀርቦ በተሰጠው አስተያየት መሠረት ሰነዱን በማዳበር የጥናት ውጤቱን በቀጣይ ለሚደረጉ ማሻሻያዎች በግብዓነት እንዲረዳ ሰነዱን ለሚመለከታቸው ሁሉ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡
- **የተተውና በጉምሩክ የተወረሱ ዕቃዎች አስተዳደር ዳሰሳ ጥናት፡-** የተተውና በጉምሩክ የተወረሱ ዕቃዎች አስተዳደር ሥርዓት አፈጻጸም በመገምገም ጠንካራና ደካማ ጎኖች በመለየት በቀጣይ የተለዩ ችግሮችን ለማሻሻል የሚያስችል ምክረ ሃሳብ በማቅረብ መረጃዎችን ከጉምሩክ ዋናው መ/ቤት እና ከቅ/ጽ/ቤቶች በመሰብሰብና በመተንተን ረቂቅ የጥናት ሰነድ ተዘጋጅቶ ለአስተያየት ቀርቧል፡፡
- **የጉምሩክ ቀረጥ ነጻ መብት ክትትል አፈጻጸም ግምገማ ጥናት፡-** በመንግስት የተሰጡ የጉምሩክ ነጻ መብቶች አጠቃቀም ክትትል ዙሪያ ዳሰሳ በማካሄድ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል አማራጭ የመፍትሔ ሃሳብ ለማቅረብ መረጃዎችን ከጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶችና ከተጠቃሚዎች መረጃዎችን በመሰብሰብ ትንተና በማካሄድ የጥናት ሰነድ ተዘጋጅቶ ለቀጣይ አፈጻጸም በግብዓትነት እንዲያገለግል ለጉምሩክ ኮሚሽንና ሌሎች ለሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች እንዲደርስ ተደርጓል፡፡
- **የሠረተኞች ስልጠና ውጤታማነት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፡-** በታክስና ጉምሩክ የስልጠና ማዕከል የሚሰጡ ስልጠናዎች ምን ያህል ውጤታማ ናቸው የሚለውን መገምገምና ከስልጠና አሰጣጥ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ችግሮችን በመለየት መረጃዎችን ከገቢዎች ሚኒስቴርና ከጉምሩክ ዋና መ/ቤት እና ከሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች በማሰባሰብ መረጃዎችን በመተንተን የጥናት ሰነድ ተዘጋጅቶ በቀጣይ የስልጠና ውጤታማነት ለማሻሻል በግብዓትነት እንዲያገለግል ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ሁሉ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡
- **የተመረጡ ግብር ከፋዮች አገልግሎት ቡድን አጭር ዳሰሳ ጥናት፡-** ከዋናው መ/ቤት፣ ከከ/ግ/ከ ቅጽ/ቤት፣ ከመካከለኛ ግ/ከ/ቅ/ጽቤት፣ ከተመረጡ ግብር ከፋዮች ታክስ አስተዳደሮች መረጃዎችን በመሰብሰብና በመተንተን ረቂቅ የጥናት ሰነድ ተዘጋጅቶ ለውይይት ቀርቦ በተሰጠው አስተያየት መሠረት ሰነዱ ዳብሮ የተዘጋጀው የጥናት ሰነድ ለቀጣይ አፈጻጸም በግብዓትነት እንዲያገለግል ለሚመለከተው አካል ቀርቧል፡፡
- **የህብረት ሥራ ማህበራት የታክስ አስተዳደር አፈጻጸም ዳሰሳ ጥናት፡-** የዚህ ጥናት ዋና ዓለማ የህግ ሰውነት የተሰጣቸው የህብረት ሥራ ማህበራት በህብረት ሥራ ማህበራት ማቋቋሚያ አዋጅ ነጻ ከተደረገው የንግድ ትርፍ ገቢ ግብር ውጪ ያሉ ታክሶችን አስተዳደር በሚመለከት ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ በመዳሰስ ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት የሚፈቱበትን አማራጭ የመፍትሔ ሃሳብ ለማቅረብ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ጥናቱን ለማካሄድ መረጃዎች ከፌዴራልና ከክልል የህብረት ሥራ ኮሚሽኖች፣ ከክልል/ከተማ አስተዳደር በተለያዩ ክልሎች ከሚገኙ የገቢዎች ሚኒስትር ቅ/ጽ/ቤቶች እና ከተመረጡ የህብረት ሥራ ማህበራት መረጃዎችን በመሰብስብና በመተንተን ረቂቅ የጥናት ሰነድ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትር ጽ/ቤት ቀርቧል፡፡
- **የዲጂታል ግብይት ታክስ አስተዳደር፡-** እያደገ ከመጣው የኤሌክትሮኒክስ ንግድ በሀገራችን ታክስ ለመሰብሰብ ያሉ መልካም እድሎችና ተግዳሮቶችን ገምግመም የመፍትሔ ሃሳብ ለማቅረብ መረጃዎችን

ከሚመለከታቸው ተቋማት (ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ ገንዘብ ሚኒስቴር እና ብሄራዊ ባንክ) እና ገቢዎች ሚኒስቴር መረጃዎችን በመሰብሰብ የጥናት ሰነድ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ሁሉ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

- **የታክስ ተመላሽ ስርዓት አተገባበር ዳሰሳ ጥናት:-** የተ.እ.ታ ተመላሽ ስርዓት አፈጻጸም በመገምገም ከተመላሽ ስርዓት ጋር ተያይዞ ያሉ ችግሮችን በመለየት ለቀጣይ መፍተሔ አቅጣጫዎችን ለሚመለከታቸው መረጃዎች ከዋናው መ/ቤት፣ ከቅ/ጽ/ቤቶች እና ከታክስ ከፋዮች በመሰብስብ የትንተና ሥራ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

**በጉምሩክ ኮሚሽን በኩል የጥናት ስራዎች አፈፃፀምን በተመለከተ:-**

- ከማህበራዊ ልማት ቀረጥ አተገባባር ጋር በተያያዘ የጥናት ስራ ተከናውኖ የውሳኔ ሀሳብ ቀርቧል፡፡ ተቀባይነት ያለው የስሪት ሀገር መግለጫ (Origin Marking) በገቢ እቃዎች ላይ በማይገኝበት ጊዜ መደረግ ስላለበት የስሪት ሀገር አወሳሰን ጥናት በማድረግ አሰራር ተዘጋጅቶ ለቅ/ጽ/ቤቶች ተልኳል፡፡ በኮስሞቲክስ እቃዎች አስመጪዎች ማህበር በተወሰኑ እቃዎች ታሪፍ አመዳደብ ላይ ያቀረቡትን ቅሬታ መሰረት በማድረግ ጥናት በማድረግ አስፈላጊው ሰነድ ተዘጋጅቶ ለዓለም የጉምሩክ ድርጅት የታሪፍ አመዳደብ ተልኳል፡፡
- እንዲሁም የጉምሩክ ዕቃ ፍተሻ አሠራር ላይ እና በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ገብተው የሚወጡ ዕቃዎች የጉምሩክ አሠራር ስርዓትን በተመለከተ እየገጠሙ ያሉ ችግሮችን በመለየትና የመፍትሄ ሃሳብ ለማቅረብ ጥናቶች ተከናውነዋል፡፡
- ከተሽከርካሪ መለዋወጫ ጋር ተያይዞ በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን በተመለከተ ጥናት በማድረግ የመፍትሄ ሀሳብ ቀርቧል ፡፡
- የቦንድድ ግብዓት አቅራቢ በሆኑ አራት ድርጅቶች ላይ የተሰጣቸውን መብት በአግባቡ እየተጠቀሙ መሆናቸውንና አለመሆናቸውን ጥናት ተከናውኗል፡፡
- እንዲሁም በአምራች ኢንዱስትሪዎች ዙሪያ በተረፈ ምርት ምንነትና አወጋገድ ላይ ጥናቶች ተከናውነዋል፡፡
- በተጨማሪም የADVANCE RULING የዋጋ አሰራርን በተመለከተ የአለም አቀፍ ልምዶችን በማካተት የጥናት ስራው ተጀምሯል፡፡
- 38 አይተሞች ላይ በተለይ ደግሞ ተሽከርካሪ ላይ ክልከላዉ ከመደረጉ በፊት እና በኋላ ያለዉን ልዩነት እና ከገቢ ጋር ያላቸዉን ተጽዕኖ ለማሳየት በሚያስችል ደረጃ አስፈላጊ የሆኑ ጥናቶች ተከናውነዋል፡፡ የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ተጠቃሚዎች የህግ ተገዥነት ደረጃቸውን በጥናት ለመለየት የመረጃ ትንተና ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡
- የስጋት ሥራ አመራርን ለማሻሻል የሚያስችል የውጤታማነት ጥናት በመካሄድ ረቂቅ ሪፖርት ተዘጋጅቷል፤ የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ተጠቃሚዎች የህግ ተገዥነት ደረጃቸውን በጥናት የመለየትና የመተንተን ስራ እየተሰራ ይገኛል፤ከዚሁ ጋር ተያይዞ የወጪ ንግድ ማበረታቻ ስርዓት ተጠቃሚዎች ከ6ቱ ዓይነት ስርዓቶች ለምን የቫውቸር ስርዓትን በብዛት(90%) እንደሚጠቀሙ ጥናቱ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ የዕቃዎች ቆይታ ጊዜ ጥናት (TRS)ተከናውኗል፤ በዚህም ደንበኞች ለኮሚሽኑ የሚያቀርቧቸው ሰነዶች በአማካይ 11 ቀናት ያህል ቆይተው የሚስተናገዱ መሆኑን የጥናቱ ግኝት ያሳያል፡ ፡ በንግድ ማጭበርበር ስራ የተሳተፉ አካላት የመለየትና የንግድ ማጭበርበር የሚከሰትባቸው የስራ ዘርፎች በጥናት የመለየት ስራ ተሰርቷል፣ በሀሰተኛ የባላድርሻ አካላትን የድጋፍ ደብዳቤ በማዘጋጀት አለግባብ በአካል ጉዳተኛ ስም ተሽከርካሪዎችን ወደ አገር ውስጥ በማስገባት የሚያጭበረብሩ አካላት በጥናት የመለየት ስራ ተሰርቷል፡፡ በኮንስትራክሽን የስራ ዘርፍ የሚስተዋሉ ከቀረጥ ነፃ መብት አላግባብ በመገልገል የሚስተዋሉ ችግሮችን የመለየት ስራ ተሰርቷል፡፡

- ከንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚ/ር፣ ከኦሮሚያ ንግድ ቢሮ እና ከሱማሌ ክልል ንግድና ትራነስፖርት ቢሮ ጋር በመቀናጀት በሶማሌ ክልል የሀገር ውስጥ የጫት ኮታን በተመለከተ ጥናት ተደርጎ የመጠን ማስተካከያ ተደርጓል፡፡አንላይን ክፍያ አገልገሎት ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ እና ያሉት ክፍተቶች እና የህግ ማዕቀፎችን በመለየት ጥናት በማድረግ የውሳኔ ሐሳብ ቀርቧል፡፡
- የTelex relaze and See way bill ላይ እና በአንድ የባንክ ፈቃድ ከሁለት በላይ የማስጫኛ ሠነድ ጋር ተያይዞ ዳሰሳዊ ጥናቶች ተከናውነዋል፡፡
- በስካኒንንግ ማሽን አጠቃቀም ዙሪያ ያስገኙት ውጤትና የተስተዋሉ ችግሮችን የተመለከተ ዳሰሳ ጥናት ላይ አስተያየጥ እየተሰጠበት ይገኛል፡፡
- እሴት የማይጨምሩ የስራ ፍሰቶችን ለማሻሻል ለተቋማዊ አቅም ዘርፍ ተጠንቶ ቀርቧል፡፡

## 3.1.2 የታክስ መረጃ አስተዳደር ውጤታማነት ማረጋገጥ ስራዎች አፈጻጸም

### ➲ የታክስ መረጃና የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አስተዳደር አፈጻጸም

- ለ 1,094 ወጭ መጋራት መረጃ ፈላጊዎች ምላሽ ተሰጥቷል፡፡
- በመመሪያ ቁጥር 143/2011 መሰረት 3,949 ታክስ ከፋዮች መሰረታዊ የምዝገባ መረጃቸው ወቅታዊ ተደርጓል፡፡
- 7,595 ታክስ ከፋዮች የተሟላና ጥራቱን የጠበቀ የምዝገባ መረጃ እንዲኖራቸው ተደርጓል፡፡
- 4,720 ግብር ከፋዮች የግ/ከ/መ/ቁ አውጥተው የንግድ ፈቃድ በማምጣት የታክስ አካውንት ባለማስከፈታቸው ተሰርዘዋል፡፡
- የቢዝነስ አመቺነትን ከመፍጠር አንፃር የተሸጡ የሽ/መ/መሳሪያዎች በሙሉ በ3 ቀናት ውስጥ መተከል ያለባቸው ሲሆን በበጀት አመቱ ከተሸጡ 10,342 ማሽኖች ውስጥ 10,328 መሳሪያዎች በሙሉ100% በ3 ቀናት ሊተከሉ ችለዋል፣
- አመታዊ እድሳት ፈልገው ከገቡ 77,236 ማሽኖች ውስጥ 77,011 (100%) በ48 ሰዓት ታድሰዋል፡፡
- የጥገና አገልግሎት ፈልገው ከገቡ 35,764 ማሽኖች ውስጥ 35,656 (100%) በ48 ሰዓት ተጠግነው ወጥተዋል፡፡
- አምባሰል 1716፣ ሀሮን 2400፣ ስኬት 600፣ ወንዶ ንግድና ኢንቨስትመንት ኩባንያ 940፣ አይፖስ ኢንተርናሽናል ኃ/የተ የግል ማህበር 500፣ ዲያንካ 220፣ ፔትራም ኃ/የተ የግል ማህበር 300፣ ኢታ ሶሉሽን 18 በአጠቃላይ ያስመጧቸው 6,694 የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ሲስተም ላይ ተመዝግበው እና መለያ ቁጥር ተሰጥቷቸው ለሽያጭ እንዲቀረቡ ተደርጓል፡፡
- ለ3 የሽ/መ/መ እና ሶፍትዌር እውቅና ተሰጥቷል፣
- ሐሮን ኮምፒውተር ኃላ.የተ.የግ.ማህበር ዤአሜን ዳታ ሜጋ ቴክኖሎጂ ካፓኒ ሊሚትድ ከተባለ አምራች ድርጅት ያስመጣውን አዲስ ሞዴል በአ.አ ዩንቨርስቲ የፍተሻ ስራ ተጠናቆ እውቅና እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡
- ለ3 የኦሮሚያ ባለሙያዎች የሽያጭ መ/መሳሪያ መረጃ መመዝገቢያ እና ለ5 የአዲስ አበባ ከተማ ገቢዎች ሰራተኞች የጠፋ ማሽን መመዝገቢያ መጠቀሚያ ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡
- ለ7 የሀሮን፣ ለ1 የስኬት ቴክኖሎጂስ ለ1 የአምባሰል ቴክኒሺያን፣ ለ3 የወንዶ፣ ለ3 የቢፍቱ፣ ለ3 የአይፖስ እንዲሁም ለ1 ኢታ፣ ለ1 ጁፒተር አቅራቢዎች በጠቅላላው ቴክኒሺያኖች ለ18 የተመዘገበ የSeal ቁጥር ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡

➢ ከቢፍቱ አዱኛ እና ከአምባሰል ትሬዲንግ የሽያጭ የፌዴራል እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግብር ከፋዮች ገዝተው ያልወሰዷቸውን 69 ማሽኖች፣ ለጥገና፣ ለዓመታዊ እድሳት የገቡ 112 ማሽኖች እና በአደራ ለ3 ወር እንዲቀመጡ ተፈቅዶ ከ3 ወር በላይ የሆናቸው 52 ማሽኖች

እንዲወሰዱ ለማድረግ መረጃቸውን የመሰብሰብ እና አደራጅቶ ለታክስ ማዕከላት በመላክ እንዲያስወስዱ የክትትል ስራ ተሰርቷል፡፡

- በጁፒተር 33 እና በወንዶ 85 በጠቅላላው 118 ግብር ከፋዮች የገዟቸው፣ በጥገና፣ በዓመታዊ ምርመራ ለ3 ወር በአደራ እንዲቀመጡ ተደርገው ግብር ከፋዮች ሊወስዷቸው ባለመፈለጋቸው አገልግሎት ማዕክል የነበሩ ቅርንጫፎች፣ አዲስ አበባ ገቢዎችና ኦሮሚያ ገቢዎች እንዲያስነሱ በደብዳቤ የማሳሰብ ስራ ተሰርቷል፡፡
- በአደራ ከተቀመጡት ከ3 ወር በላይ ከሆናቸው 930 ማሽኖች ውስጥ 470 ወደ ስራ ሲመለሱ 319 ማሽኖች የተወገዱ ሲሆን 28ቱ ባለቤቶቹ በመጥፋታቸው አገልግሎት ማዕከል እንዲቀመጡ ሲደረግ 113 ማሽኖች ክትትል የሚፈልጉ ናቸው፡፡
- በአስራ ሁለት ወራት ውስጥ (ከመካከለኛ ቀጥር 2 ውጭ) 46,654 ለማስገባት ታቅዶ 40,778 (87%) የኤፍዲ መረጃዎች ወደ ሲስተም እንዲገባ ተደርጓል፡፡
- በአጠቃላይ ከአስራ ስድስት ዘርፎች 3,902 ወቅታዊ የገበያ ዋጋ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ታቅዶ ከአስራ ስድስት ዘርፎች 3,902 /100%/ ከተመረጡት የገበያ ቦታዎች ተመሳሳይ የተገኘላቸው ከአራት እስከ ስድስት ናሙናዎችን ተመሳሳይ ያልተገኘውን አንድ ናሙና በአካል፣ በስልክና በዌብ የመሰብሰብ ስራ ተሰርቷል፡፡
- በኢትዮጲያ ምርት ገበያ ከሰኔ እስከ ግንቦት ወር 2016 ዓ.ም. ግብይት የተፈጸመበት 460,354,844.95 የብር መጠን የያዘ 27,898 ዝርዝር ዊዝሆልድ መረጃ ወደ መረጃ ቋት የማስገባት ሥራ ተሰርቷል፡፡
- በበጀት ዓመቱ 343 (በድግግሞሽ የተለያየ ክፍያ) የኮንስትራክሽን ዲዛይን የአገልግሎት ክፍያ መረጃ የመሰብሰብ ስራ የተሰራ ሲሆን የ69 የኮንስትራክሽን ድርጅቶች መረጃ በመተንተንና በማጠናቀር ለፌደራል ቅርንጫፎችና ለክልል ገቢዎች የተሰራጭ ሲሆን የአ.አ. ገቢዎች ቢሮ ግብር ከፋይ የሆኑ የ31 የኮንስትራክሽን ድርጅቶች የኮንስትራክሽን ዲዛይን መረጃ በአ.አ. ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ባለስልጣን ለታክስ መረጃና ሽያጭ መመዝገቢያ ስራ ክፍል ተልኳል፡፡
- ከ 44 የመንግስት ዩንቨርሲቲዎች የወጭ መጋራት መረጃ ተሰብስቦ የ39 ዩንቨርሲቲዎች ወደ መረጃ ቋት ገብቷል፡፡
- ከአምራች አከፋፋይ /ሽያጭ/መረጃ ከመሰብሰብ እንጻር ከ 6,655 ድርጅቶች ለመሰብሰብ ታቅዶ ከ6,277 (94%) ድርጅቶች የተሰበሰበ ሲሆን አፈጻጸሙን በመረጃ ለማሳየት 1,587,684 መረጃ ተሰብስቧል፡፡

- ከግብር ከፋዮች የግዢ መረጃ በመሰብሰብ ረገድ ከ31,184 ድርጅቶች ለመሰብሰብ ታቅዶ ከ15,393 ድርጅቶች (49%) 409,405 መረጃ ተሰብስቧል።

- ከመንግስት ባለበጀት መስሪያ ቤት የግዢ መረጃ ከመሰብሰብ አንጻር ከ315 መስሪያ ቤት ለመሰብሰብ ታቅዶ ከ308 መስሪያ ቤት (98%) በመረጃ 18,109 ተሰብስቧል።
- ከNGO ግዢ መረጃ መሰብሰብ በተመለከተ ከ1,721 NGO የግዥ መረጃ ለመሰብሰብ ታቅዶ ከ1365 ወይም የዕቅዱን 79% መሰብሰብ ተችሏል።
- የሶስተኛ ወገን የግዢና ሽያጭ መረጃ በየወሩ እየሰበሰቡ ወደ መረጃ ቋት ማስገባትንና ተደራሽ ማድረግን በሚመለከት በበጀት አመቱ 2,072,955 መረጃ ወደ መረጃ ቋት ለማስገባት ታቅዶ 2,069,179 መረጃ (100%) በውስጥ ኢንኮደሮች ማስገባት የተቻለ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ 5,145,880 መረጃ በመረጃ መረብ /online/ የተሰበሰበ እና በድምሩ 7,215,059 የግዥና ሽያጭ መረጃ ወደ መረጃ ቋት ገብቷል።
- የመረጃ ጥራት ቁጥጥርን በተመለከተ በ 4,300,147 መረጃዎች ላይ ለመስራት ታቅዶ 4,299,284 (100%) ለመስራት የተቻለ ሲሆን በጥራት ቁጥጥር ወቅት ስህተት ከተገኘባቸው 65,110 መረጃዎች ውስጥ (100%) እርማት እና ድግግሞሽ መረጃን የማጥፋት ስራ ተሰርቷል።

የጠፉ ደረሰኞችን በድርጅት 542 በደረሰኝ 601 ለሚመለከታቸው አካልና ለታክስ ማጭበርበር፣ ለታክስ ኦዲት ዳይሬክቶሬት እና ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች የማሳወቅ ስራ ተሰርቷል

ከቅርንጫፎችና ከክልሎች የተላኩ የጠፉ፣ የተቃጠሉና በአድራሻቸው ሊገኙ ያልቻሉ 1796 የሽ/መ/መሳሪያ አገልግሎት እንዳይሰጡ በመስጋት እና ተጨማሪ ሽያጭ እንዳይከናወን END Command ሰረቨር ላይ ተቀምጠዋል።

የጠፉ፣ የተቃጠሉ እና በአድራሻቸው ያልተገኙ ተብለው ሪፖርት የተደረጉ 1367 ማሽኖች ዝርዝር ጥንቃቄ እንዲደረገበት ለሁሉም ቅርንጫፍ እና በታክስ ስርዓት እና ክልሎች ድጋፍ በኩል ክልሎች እንዲደርሳቸው ደበዳቤ ተጽፏል።

ማሽን መግዛት የሚጠበቅባቸውን ግ/ከፋዮች አዲስ ሽ/መ/መ ከማስገዛት አንጻር 1912 ግ/ከፋዮችን ለማስገዛት ታቅዶ 2081 /109 በመቶ/ ብቻ ማስገዛት ተችሏል፣

መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆኑ ድርጅቶች ላይ ክትትል በማድረግ 59 ድርጅት ህግ ባለማክበራቸው እንዲቀጡ የማስተላለፍ ስራ ተሰርቷል፣

የህግ ተገዥነትን ከማስፈን አንፃር በሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ጠንካራ የቁጥጥር ስራ በመስራት በበጀት ዓመቱ በ46,599 ግብር ከፋዮች ላይ የመስክ ቁጥጥር ስራ ለማካሄድ ታቅዶ በ 45,816 (98%) ቁጥጥር የተደረገ ሲሆን በተደረገው የቁጥጥር ስራም በ3517 ግብር ከፋዮች ህግን ተላልፈው በመገኘታቸው ብር 92,713,930 የቅጣት ውሳኔ የወጣ ሲሆን ብር 16,536,027 ተሰብስቧል።

- የደረሰኝ ህትመት ፈቃድ ለጠየቁ 23,379 ግብር ከፋዮች ፈቃድ ተሰጥቷል፣
- የደረሰኝ ማስወገድ አገልግሎት ለጠየቁ 2,573 ግብር ከፋዮች በሙሉ አገልግሎት አግኝተዋል
- የጠፉ ደረሰኞችን በድርጅት 542 በደረሰኝ 601 ለሚመለከታቸው አካልና ለታክስ ማጭበርበር፣

ለታክስ ኦዲት ዳይሬክቶሬት እና ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች የማሳዎቅ ስራ ተሰርቷል፡፡

## በበጀት ዓመቱ ሀሰተኛ ደረሰኝ መረጃ ማጣራት በሀገር ውስጥ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሲታይ፡-

**ከፍተኛ ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት**

- የመረጃ ይጣራልኝ ጥያቄን ከቀረበባቸው ድርጅቶች የ1540 ድርጅቶችን መረጃቸውን በማጣራት 4164 ግብይቶች ብር 213,441,670.39 ሀሰተኛ መሆናቸው ተጣርቶ ለሚመለከታቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተላልፏል፡፡
- የኦዲት ጥያቄ ከቀረበባቸውን ድርጅቶች ላይ የማጥራት ስራ ተሰርቶ 861 ድርጅቶች ሀሰተኛ ተብለው በዋናው መ/ቤት ከተለዩ ድርጅቶች ጋር ግብይት ያላቸው በመሆኑ ያደረጉትን ግዢ የትራንዛክሽን ብዛት 4248 የብር መጠን 171,253,755.03 የያዙ ግዢዎች ሀሰተኛ መሆናቸውን በመለየት ለኦዲት የስራ ክፍሎች ጥንቃቄ እንዲያደርጉ መረጃውን በማጠናቀር ተላልፏል፡፡

**ኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት**

- ደረሰኝ ይጣራልን ተብለው ከቀረቡ ደረሰኞች መካከል 53 ደረሰኝ ሀሰተኛ ሲሆኑ የያዙት የገንዘብ መጠን 19,741,843.05 ብር ነው፡፡

**ምስራቅ አ/አ/አ/ግ/ከ**

- የህገ-ወጥ ደረሰኝ ትንተና ከ 1,033,753 ድርጅቶች የግዥ ዝርዝር መረጃ ውስጥ 124 ድርጅቶች 2005 ግብይት ብር 649,444,672.79 ግኝት ታክስ እንዲወሰን ለሚመለከተው አካል የማስተላፍ ስራ ተሰርቷል፡፡

**ጅማ ቅ/ጽ/ቤት**

- ለታክስ ኦዲት፣ለታክስ ማጭበርበር እና ለአገልግሎት ኦዲት ከ27 መረጃ ብር 19,298,302.48 ለገቢው አስተዋጽኦ አድርጓል::

**ሐዋሳ ቅ/ጽ/ቤት**

- በበጀት ዓመቱ ውስጥ ከ9 ወረዳዎች የ80 ግብር ከፋይ እና ከ18 ድርጅቶች የሶስተኛ ወገን የቡና መረጃ ሰብስቦ ወደ ሚመለከተው ክፍል በማስተላለፍ ብር 22,147,004.83 የግብር ውሳኔ እንዲወሰን የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡

**ምዕራብ ቅ/ጽ/ቤት**

- በቁጥር 3200 ከሆኑ ድርጅቶች መረጃ ካላቸው 868 ድርጅቶች 44ቱ በሰርኩላር ሀሰተኛ ከተባሉት ጋር ግብይት የፈጸሙ ሲሆን ይህም በግብይት መጠን 74 በገንዘብ መጠን 7,280,137.80 ትንተና በመስራት ወደ ገቢ እንዲቀየሩ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ተላልፏል፡፡ እንዲሁም በታክስ መረጃ በኩል ከተለያዩ ክፍለ ከተሞች እና የገቢ ሰብሳቢ ተቋማት ለቀረቡ 40 የመረጃ ይጣራልኝ ጥያቄ ምላሽ ተሰቷል በዚህም 1,112,250.50 ብር የያዙ 24 ሀሰተኛ

ደረሰኞችን ማዳን ተችሏል ። በድምሩ 8,392,388.3 ብር ወደ ገቢ እንዲቀየሩ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ተላልፏል።

**ሰሜን ምዕራብ ቅ/ጽ/ቤት**

- 9 ግብር ከፋዮች ብር 317,352.24 የያዘ ግብይት በሀሰተኛ ደረሰኝ መፈጸማቸው በማረጋገጥ ወደ ገቢ እንዲቀየሩ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ተላልፏል።
- በ12 ወሩ ዉስጥ 314 ከተለያዩ የግብር ማዕከላት በሚመጡ የሀሰተኛ ደረሰኝ ይጣራልኝ ጥያቄ ተጠይቆ ከዚህም ዉስጥ ብር 10,504,354.58 የሀሰተኛ ደረሰኝ መሆኑን ተጣርቶ ምላሽ ተሰቷል።

## የመረጃ ማጥራት ስራዎች አፈጻጸም

በበጀት ዓመቱ 7,595 ታክስ ከፋዮች የተሟላና ጥራቱን የጠበቀ የምዝገባ መረጃ እንዲኖራቸው የተደረገ ሲሆን የ1,036 ታክስ ከፋዮች መረጃን በማጣራት ወደ ዘላቂ ማቆያ እንዲገባ ሲደረግ በሌላ በኩል ደግሞ 277 እንዲወጣ ተደርጓል።

## 3.1.3 የኤሌክትሮኒክ ታክስ (E-Tax) አጠቃቀምን ማሻሻል ስራዎች አፈጻጸም

### ➲ የኤሌክትሮኒክ ማሳወቅ (E-Filling) ስራዎች አፈጻጸም

የግብር ከፋዮች የኤሌክትሮኒክ ታክስ ማሳወቅ ስልጠና በተመለከተ በበጀት ዓመቱ ለ8,041 ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ8,821 (109 በመቶ) ተሰጥቷል። የኤሌክትሮኒክ ታክስ ማሳወቅ በ2016 በጀት ዓመት የስርዓቱ ተጠቃሚዊ ሽፋን 98 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ ካሉን የተጣራ 50,820 ግብር ከፋዮች ውስጥ 48,349 (95.14 በመቶ) መፈጸም ተችሏል።

**ሰንጠረዥ 10 የኢ-ፋይሊንግ ስልጠና እና የይለፍ ቃል አፈጻጸም**

| ተ. ቁ | ቅ/ጽ/ቤት | እስከ አሁን የሰለጠኑ | የ12 ወሩ ስልጠና | | | የይለፍ ቃል አፈጻጸም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | መቶኛ | በ12 ወሩ የይለፍ ቃል የወሰዱ | እስከ አሁን የይለፍ ቃል የወሰዱና እያሳወቁ (እየተጠቀሙ) ያሉ ግብር ከፋዮች |
| 1 | ከፍተኛ | 744 | - | - | | - | 744 |
| 2 | መካከለኛ ቁ.1 | 4,187 | 23 | 26 | 113 | 27 | 4,186 |
| 3 | መካከለኛ ቁ.2 | 4,032 | | 1 | | 1 | 4,032 |
| 4 | ምሥራቅ | 12,763 | 1,938 | 2,489 | 128 | 2,489 | 12,337 |
| 5 | ምዕራብ | 10,537 | 2,584 | 2,335 | 90 | 2,054 | 9,638 |
| 6 | ሰሜን ምዕራብ | 8,770 | 1,500 | 1,963 | 131 | 1,912 | 8,389 |
| 7 | ባህርዳር | 3,005 | 416 | 404 | 97 | 421 | 2,901 |
| 8 | መቀሌ | 64 | 60 | 64 | 106 | 64 | 46 |
| 9 | ሐዋሳ | 2,010 | 228 | 385 | 168 | 385 | 1,891 |
| 10 | አዳማ | 1,416 | 387 | 301 | 77.7 | 331 | 1,379 |
| 11 | ጅማ | 1,493 | 449 | 442 | 98 | 442 | 1,272 |
| 12 | ድሬዳዋ | 534 | 81 | 93 | 115 | 93 | 510 |
| 13 | ኮምቦልቻ | 1,070 | 375 | 318 | 85 | 330 | 1,024 |
| ድምር | | 50,625 | 8,041 | 8,821 | 109 | 8,549 | 48,349 |

ሰንጠረዥ 7 እስከ አሁን ወደ ስርዓቱ የገቡና እያስታወቁ ያሉ

| ተ. ቁ | ቅ/ጽ/ቤት | ጠቅላላ የግብር ከፋይ ብዛት | ወደ ኢ-ፋይሊንግ ስርዓት መግባት የማይችሉ | የኢ-ታክስ ሥልጠና መውሰድ የሚገባው የተጣራ የግብር ከፋይ ብዛት | እስከ አሁን ስልጠና የወሰዱ | ቀሪ ስልጠና መውሰድ የሚገባቸው ዕቅድ | እስከ አሁን ወደ ስርዓቱ የገቡና እያስታወቁ ያሉ | ሽፋን በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ | 744 | | 744 | 744 | | 744 | 100 |
| 2 | መካከለኛ ቁ1 | 4,407 | 220 | 4,187 | 4187 | 0 | 4,186 | 100 |
| 3 | መካከለኛ ቁ2 | 4,041.00 | 12 | 4,029 | 4,029 | 0 | 4,032 | 100 |
| 4 | ምሥራቅ | 14,954 | 2120 | 12,834 | 12,763 | 71 | 12,337 | 96 |
| 5 | ምዕራብ | 12631 | 1990 | 10,641 | 10,537 | 104 | 9,638 | 95 |
| 6 | ሰሜን ምዕራብ | 11229 | 2475 | 8,754 | 8,754 | 0 | 8,389 | 96 |
| 7 | ባህርዳር | 4124 | 1119 | 3,005 | 3,005 | 0 | 2,901 | 97 |
| 8 | መቀለ | 2664 | | | 64 | | 46 | |
| 9 | ሐዋሳ | 2323 | 390 | 1,933 | 1,933 | 0 | 1,891 | 94 |
| 10 | አዳማ | 1761 | 326 | 1,435 | 1,416 | 19 | 1,379 | 94 |
| 11 | ጅማ | 2089 | 467 | 1,622 | 1,493 | 129 | 1,272 | 78 |
| 12 | ድሬዳዋ | 778 | 240 | 538 | 534 | 4 | 510 | 95 |
| 13 | ኮምቦልቻ | 1438 | 340 | 1,098 | 1,070 | 28 | 1,024 | 94 |
| | ድምር | 63,183 | 9,590 | 50,820 | 50,529 | 291 | 48,349 | 95.14 |

**የኤሌክትሮኒክ ክፍያ (E-Payment) አፈጻጸምን በተመለከተ፦** በበጀት ዓመቱ 10,141 ግብር ከፋዮችን ወደ ስርዓቱ ለማስገባት ታቅዶ 6,111 (60.26 በመቶ) ተከናውኗል፡፡ የኢ-ክፍያ ስርዓት ሽፋን በተመለከተ ከክፍያ ጋር አሳውቀው ክፍያ ከከፈሉት 37,637 ግብር ከፋዮች ውስጥ 25,623 (68.08%) በኢ-ፔይመንት ስርዓት የከፈሉ ናቸው፡፡ በኤሌክትሮኒክ የታክስ ክፍያ ሥርዓት የተሰበሰበ የታክስ መጠን ከአጠቃላይ ታክስ ያለውን ድርሻ 35 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ በአገር ውስጥ ታክስ ከተሰበሰበው 321.85 ቢሊየን ብር ውስጥ 94.71 ብር በኢ-ክፍያ በመሰብሰቡ ድርሻው ከጠቅላላ ገቢ 29.43 በመቶ በመሆኑ የዕቅዱን 84% ማሳካት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም እስከ አሁን ወደ ኢ-ፔይመንት የገቡ ግብር ከፋዮች ብዛት 29,318 ሲሆን የገንዘብ መጠኑ ደግሞ ብር 222,409,921,502.62 ቢሊዮን ነው፡፡

ሰንጠረዥ 8 የኤሌክትሮኒክ ክፍያ (E-Payment) የእስከ አሁን አፈጻጸም

| ተ. ቁ. | ቅ/ጽ/ቤት | የግብር ከፋይ ብዛት | እስከ አሁን የተጠቃሚ ብዛት | ሽፋን በመቶኛ | በኢ-ፋይሊንግ በማሳወቅ ላይ ያሉ ግብር ከፋዮች ብዛት | የኢ-ክፍያ ሽፋን ከኢ-ማሳወቅ አንፃር | የትራንዛክሽን ብዛት | የክፍያ መጠን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ | 744 | 759 | 102 | 744 | 102.02 | 49,117 | 147,421,557,861.64 |
| 2 | መካከለኛ ቁ.1 | 4187 | 3,850 | 92 | 4186 | 92.24 | 123,490 | 29,477,909,220.57 |
| 3 | መካከለኛ ቁ.2 | 4029 | 3,718 | 92 | 4032 | 92.21 | 121,248 | 21,791,464,166.31 |
| 4 | ምሥራቅ | 12834 | 7,309 | 56 | 12337 | 59.24 | 83,669 | 3,306,051,739.70 |
| 5 | ምዕራብ | 10641 | 4,802 | 45 | 9638 | 49.82 | 53,288 | 2,543,464,954.95 |
| 6 | ሰሜን ምዕራብ | 8754 | 4,151 | 47 | 8389 | 49.48 | 39,871 | 1,569,889,291.09 |
| 7 | ባህርዳር | 3005 | 1,389 | 46 | 2901 | 47.88 | 13,502 | 3,879,141,559.64 |
| 8 | ሀዋሳ | 1933 | 1,018 | 53 | 1891 | 53.83 | 9,986 | 2,239,295,967.23 |
| 9 | መቀሌ | | 49 | | 46 | | 239 | 724,686,303.52 |
| 10 | አዳማ | 1435 | 903 | 63 | 1379 | 65.48 | 13,283 | 4,220,942,141.72 |
| 11 | ጅማ | 1622 | 611 | 38 | 1272 | 48.03 | 5,479 | 1,060,759,216.72 |
| 12 | ድሬደዋ | 538 | 280 | 52 | 510 | 54.90 | 3,028 | 2,846,468,423.85 |
| 13 | ኮምቦልቻ | 1098 | 479 | 44 | 1024 | 46.78 | 4,808 | 1,328,290,655.68 |
| | ድምር | 50,820 | 29,318 | 58 | 48,349 | 60.63 | 521,008 | 222,409,921,502.62 |

**ሰንጠረዥ 9 የቴሌብር ኤሌክትሮኒክ ክፍያ (E-Payment) የእስከ አሁን አፈጻጸም**

| ተ. ቁ | ቅርንጫፍ ጽ/ቤት | ከተተገበረ ጀምሮ | የትራንዛክሽን ብዛት | የተሰበሰበ የገንዘብ መጠን |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ | 12 | 129 | 15,583,989,505.36 |
| 2 | መካከለኛ ቁ.1 | 671 | 2797 | 221,026,808.85 |
| 3 | መካከለኛ ቁ.2 | 406 | 1585 | 88,980,896 |
| 4 | ምስራቅ | 3457 | 13501 | 208,783,234.24 |
| 5 | ምዕራብ | 1014 | 3555 | 42,246,663.50 |
| 6 | ሰሜን ምዕራብ | 1616 | 6024 | 52,571,935.30 |
| 7 | ባህርዳር | 662 | 2990 | 51,525,663.84 |
| 8 | ሐዋሳ | 532 | 2083 | 54,020,367.08 |
| 9 | መቀሌ | 3 | 11 | 77,598.35 |
| 10 | አዳማ | 437 | 2059 | 79,137,143.66 |
| 11 | ጅማ | 251 | 901 | 33,615,736.57 |
| 12 | ድሬደዋ | 167 | 767 | 11,236,774.63 |
| 13 | ኮምቦልቻ | 98 | 422 | 5,078,569.57 |
| ድምር | | 9,326 | 36,824 | 16,432,290,897.07 |

በገቢዎች ሚኒስቴር እስከ ሰኔ 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ የተሰሩ ሥራዎች በኢ-ፋይሊንግ የመጣ ክፍያ ብቻ ይስተናገድ የነበረው ከጥር 1 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ማንኛውም የሚከፈል ክፍያ በቴሌብር እንዲስተናገድ ተደርጓል፡፡ በስርዓቱ 9,326 ታክስ ከፋዮች በ 36,824 ትራንዛክሽኖች ብር 16,432,290,897.07 ተከፍሏል፡፡

**ሰንጠረዥ 10 የቴሌብር ኤሌክትሮኒክ ክፍያ (E-Payment) የበጀት ዓመቱ አፈጻጸም**

| ተ. ቁ | ቅርንጫፍ ጽ/ቤት | የከፈሉ ግብር ከፋዮች ብዛት | የትራንዛክሽን ብዛት | የገንዘብ መጠን |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ | 11 | 117 | 13,510,714,386.59 |
| 2 | መካከለኛ ቁ.1 | 663 | 2656 | 218,127,902.65 |
| 3 | መካከለኛ ቁ.2 | 374 | 1411 | 82,827,860.43 |
| 4 | ምስራቅ | 3396 | 12786 | 205,637,626.31 |
| 5 | ምዕራብ | 979 | 3234 | 40,462,556.36 |
| 6 | ሰሜን ምዕራብ | 1584 | 5713 | 51,079,496.25 |
| 7 | ባህርዳር | 628 | 2624 | 47,516,704.62 |
| 8 | ሐዋሳ | 523 | 1983 | 52,612,575.14 |
| 9 | መቀሌ | 3 | 11 | 77,598.35 |
| 10 | አዳማ | 430 | 1951 | 77,880,799.02 |
| 11 | ጅማ | 250 | 885 | 33,415,300.88 |
| 12 | ድሬደዋ | 165 | 694 | 10,307,152.77 |
| 13 | ኮምቦልቻ | 88 | 369 | 4,376,700.38 |
| ድምር | | 9,094 | 34,434 | 14,335,036,659.75 |

### 3.1.4 የቀረጥና ታክስ አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን ማረጋገጥ ስራዎች አፈጻጸም

በበጀት ዓመቱ 11,173 ግብር ከፋዮችን ወደ ታክስ መረቡ ለማስገባት ታቅዶ 12,374 (110.7 በመቶ) ምዝገባ ተካሂዷል፡፡ ከስታንዳርድ አንጻርም 94 በመቶ ለመፈጸም ታቅዶ 100 (106.38 በመቶ) በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ተስተናግደዋል፡፡ አጠቃላይ የግብር ከፋይ ቁጥር 63,116 ደርሷል፡፡ 881 ታክስ ከፋይ በራሱ ፈቃድ የስረዛ ክሊራንስ ወስዶ ከታክስ ስርአቱ ወጥቷል፡፡

በበጀት ዓመቱ 4,133 ታክስ ከፋዮች በቻርተር ስታንደርዱ መሰረት ለተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የተከናወነ ሲሆን ከተከናወነው ውስጥ 4,100 በስታንደርድና በታች 33 በመዘግየት አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡

### ሰንጠረዥ 11 የግብር ከፋዮች ምዝገባ አፈጻጸም

| ተቁ | ቅርንጫፉ | ጠቅላላ ግብር ከፋይ ከባለፈው በጀት ዓመት የዞረ | በ12 ወሩ አዲስ የገባ | ከሌላ ቅ/ጽ/ቤት የመጣ | ከማቆያ የወጣ | ንግድ ፈቃድ ስላመጡ የተከፈተ | በመረጃ ማጥራት የተደመረ | ድምር | በ12 ወሩ የተሰረዘ | ወደ ሌላ ቅ/ጽ/ቤት የዞረ | ወደ ማቆያ የገባ | በመረጃ ማጥራት የተቀነሰ | ከ3 ወር በላይ አካውንት ስላልከፈቱ የተዘጋ | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ | 642 | 0 | 272 | 0 | 0 | 0 | 914 | 0 | 156 | 14 | 0 | 0 | 744 |
| 2 | መካከለኛ ቁጥር 1 | 3753 | 1 | 2503 | 0 | 0 | 14 | 6271 | 8 | 1906 | 0 | 17 | 0 | 4340 |
| 3 | መካከለኛ ቁጥር 2 | | 0 | 4111 | 0 | 0 | 1 | 4112 | 37 | 34 | 0 | 0 | 0 | 4041 |
| 4 | ምስራቅ | 14257 | 3603 | 1041 | 47 | 403 | 90 | 19441 | 276 | 2243 | 496 | 0 | 1472 | 14954 |
| 5 | ምዕራብ | 13319 | 2875 | 96 | 100 | 0 | 506 | 16896 | 172 | 3612 | 0 | 481 | 0 | 12631 |
| 6 | ሰሜን ምዕራብ | 10233 | 2204 | 1113 | 12 | 15 | 10 | 13587 | 215 | 1774 | 0 | 0 | 369 | 11229 |
| 7 | ባህርዳር | 4000 | 1045 | 4 | 25 | 176 | 2 | 5252 | 43 | 2 | 0 | 1 | 1082 | 4124 |
| 8 | ሐዋሳ | 2178 | 397 | 51 | 15 | 24 | 2 | 2667 | 18 | 9 | 2 | 0 | 315 | 2323 |
| 9 | መቀሌ | 2313 | 534 | 9 | 56 | 37 | 236 | 3185 | 16 | 1 | 502 | 2 | 0 | 2664 |
| 10 | አዳማ | 1364 | 525 | 0 | 3 | 19 | 2 | 1913 | 33 | 13 | 1 | 2 | 103 | 1761 |
| 11 | ጅማ | 2334 | 700 | 45 | 2 | 40 | 0 | 3121 | 20 | 0 | 6 | 0 | 1006 | 2089 |
| 12 | ድሬዳዋ | 658 | 135 | 3 | 5 | 26 | 0 | 827 | 16 | 1 | 2 | 0 | 30 | 778 |
| 13 | ኮምቦልቻ | 1381 | 355 | 30 | 12 | 98 | 0 | 1876 | 27 | 1 | 13 | 54 | 343 | 1438 |
| ጠቅላላ | | 56432 | 12374 | 9278 | 277 | 838 | 863 | 80062 | 881 | 9752 | 1036 | 557 | 4720 | 63116 |

በርቀት የጣት አሻራ ምዝገባ (Remote Registration) ከተለያዩ ሀገራት የተላኩ 510 የዲያስፖራ ግብር ከፋዮች የጣት አሻራ መረጃ አጥርቶ ወደ ሲስተም በማስገባት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዲያገኙ ተደርጓል።

በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አንድ አለቀ የምዝገባ ማእከል ለ218 የውጭ ሀገር ባለሀብቶች የግ.ከ.መ.ቁ ተሰጥቷል። በተጨማሪም በስልክና ITSM የመጡ 654 ጉዳዮች ተስተናግደዋል።

## ፋይዳ ኢትዮጵያ ዲጅታል መታወቂያ ከግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ጋር ማቀናጀት ሥራዎች፣

የዲጅታል መታወቂያ (ፋይዳ ቁጥር) ለድርጅት ሥራ አስኪያጆችና ሼር ሆልደሮች በተቋሙ ለመስጠት በሁለት ኪት ለ600 ሥራኪያጆችና ሼር ሆልደሮች ብሄራዊ መታወቂና የግብር ከፋይ መለያ በአዲስ መስጠት/ማቀናጀት ተሰርቷል።

ተቋሙ ሲገለገልበት የነበረው AFIS መሰረት ያደረገ የታክስ ከፋዮች መለያ ቁጥር አሰጣጥ ከታህሳስ 20 ቀን 2016 ጀምሮ ተቋርጦ ወደ ፋይዳ መሰረት ያደረገ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ስርአት ( Fayda based TIN system) ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ወደ አዲሱ ስርአት የገቡ ሲሆን እስከ የካቲት መጨረሻ ለ251,726 ነባርና አዲስ ግብር ከፋዮች ዲጅታል መታወቂያ ወስደዋል።

በስታንደርድ የክሊራንስ አገልግሎት አሰጣጥ በተመለከተ በድምሩ 71,879 ተገልጋዮች ጠይቀው ለ71,272 ታክስ ከፋዮች በ16 የክሊራንስ አይነቶች አገልግሎት ሲሰጥ የ407 ተገልጋዮች ጥያቄ በክሊራንስ መመሪያው የተደነገገውን ስላላሟሉ አገልግሎት አልተሰጠም። ከተሰጠው አገልግሎት ለ71,272 ተገልጋዮች በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎት ሲሰጥ ለ407 ተገልጋዮች ደግሞ በመዘግየት አገልግሎት ተሰጥቷል።

በበጀት ዓመቱ ውስጥ በተገልጋዮች ቻርተር ስታንዳርድ መሰረት አጠቃላይ 883,489 አገልግሎት ተሰጥቷል። በስታንዳርድ የተሰጠ ብዛት 318,212 ወይም 36.02 በመቶ፣ ከስታንዳርድ በታች የተሰጠ ብዛት 484,947 ወይም 54.89 በመቶ እና ከስታንዳርድ በላይ(በመዘግየት) የተሰጠ ብዛት 10,693 ወይም 9.09 በመቶ ነው።

በበጀት ዓመቱ ውስጥ በሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች 103,542 የተለያዩ የውሳኔ ማስታወቅያዎች የነበሩ ሲሆን 103,002 (99.48) በመቶው የተለያዩ የውሳኔ ማስታወቂያዎች ስርጭት ሲከናወን 540 (0.52) በመቶው በተለያዩ ምክንያቶች ያልተሰራጩ የውሳኔ ማስታወቅያዎች ናቸው።

በጉምሩክ ኮሚሽን በኩል በተገልጋዮች ቻርተር ላይ የተቀመጡ አገልግሎቶችን በተቀመጠላቸው ጊዜ ገደብ ውስጥ 98 በመቶ አገልግሎት ለመስጠት ታቀዶ አፈፃፀሙ 95.98 በመቶ በመሆኑ የዕቅድ አፈፃፀም 97.94 በመቶ ሲሆን ችሏል፡፡ የዜጎች ቻርተር አገልግሎት አፈፃፀምን በተመለከተ በበጀት አመቱ የቻርተር ሪፖርት በማካተት በአጠቃላይ 5,709,779 አገልግሎት የተሰጠ ሲሆን በስታንዳርድ እና ከስታንዳርዱ በታች የተሰጡ አገልግሎቶች 5,493,284 (96.21%) ሲሆኑ ከተቀመጠለት የአገልግሎት ስታንዳርድ በላይ የተሰጠ አገልግሎት 216,495 (3.79%) ሆኖ ተመዝግቧል፣ ከተቀመጠው ስታንዳርድ በላይ የተፈፀመበት ዋና ዋና ምክንያቶች፡- ሲስተም መቆራረጥ፣ የተሽከርካሪ ብዛትና የሪስክ ደረጃቸው ከፍተኛ የሆኑ ተሽከርካሪዎች መብዛታቸው እና የመሳሳሉት እንደ ምክንያት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

## የአገልግሎት ኦዲት ስራዎች አፈጻጸም

ከቀረቡ የአገልግሎት ጥያቄዎች ውስጥ 99 በመቶውን ምላሽ ለመስጠት ታቅዶ በበጀት ዓመቱ ከቀረበው 6,510 ውስጥ ለ6,474 (99%) ምላሽ የተሰጠ ሲሆን 36 (1 በመቶ) ወደ ቀጣይ ወር የዞረ ጥያቄ ነው፡፡ አፈጻጸሙም ምላሽ ለመስጠት ከታቀደው (99%) ነው፡፡

ሰንጠረዥ 12 የአገልግሎት ኦዲት አፈጻጸም በማህደር

| ተ.ቁ | ቅርንጫፍ | በ12 ወር የቀረበ ድምር | በተለያየ ምክንያት የተቋረጠ ማህደር | ውሳኔ የወጣለት /በሙሉ የተከናወነ | ጠቅላላ ክንውን | አፈጻጸም በመቶኛ | በስታንዳርዱ የተስተናገዱ | ወደ ቀጣይ የዞረ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ | 359 | | 359 | 359 | 100 | 357 | 0 |
| 2 | መካከለኛ ቁ 1 | 552 | 41 | 507 | 548 | 99 | 485 | 4 |
| 3 | መካከለኛ ቁ. 2 | 471 | 73 | 393 | 466 | 99 | 464 | 5 |
| 4 | ሰሜን ምዕራብ | 965 | 6 | 955 | 961 | 100 | 955 | 4 |
| 5 | ምዕራብ | 1024 | 142 | 877 | 1019 | 100 | 834 | 5 |
| 6 | ድሬዳዋ | 46 | 5 | 40 | 45 | 98 | 40 | 1 |
| 7 | ምስራቅ | 1260 | 111 | 1144 | 1255 | 100 | 1,255 | 5 |
| 8 | ጅማ | 84 | 0 | 84 | 84 | 100 | 84 | 0 |
| 9 | አዳማ | 93 | 1 | 91 | 92 | 99 | 88 | 1 |
| 10 | መቀሌ | 176 | 77 | 91 | 168 | 95 | 77 | 8 |
| 11 | ባህር ዳር | 450 | 59 | 390 | 449 | 100 | 390 | 1 |
| 12 | ሀዋሳ | 928 | 5 | 921 | 926 | 100 | 926 | 2 |
| 13 | ኮምቦልቻ | 102 | 0 | 102 | 102 | 100 | 97 | 0 |
| | ድምር | 6510 | 520 | 5954 | 6474 | 99 | 6052 | 36 |

ሰንጠረዥ 13 የአገልግሎት ኦዲት አፈጻጸም በገንዘብ (በፍሬ ግብር)

| ተ.ቁ | ቅርንጫፍ ጽ/ቤት | ዕቅድ | ክንውን | | | | አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በፍሬ ግብር | ወለድ | መቀጫ | ክንውን ድምር | |
| የተቋሙ የ9 ወራት አፈጻጸም | | 2,943,307,976.00 | 2,878,198,984.52 | 609,243,724.56 | 809,633,628.98 | 4,297,076,338.06 | 98 |

## የታክስ ተመላሽ ስራዎች አፈጻጸም በማህደር

ከቀረቡ የተመላሽ ጥያቄዎች ውስጥ 97 በመቶውን ምላሽ ለመስጠት ታቅዶ የዞረውን ጨምሮ በበጀት ዓመቱ 3,818 ጥያቄዎች ቀርበው 3,742 (98%)ምላሽ የተሰጠ ሲሆን ይህ አፈጻጸም ጥሩ ውጤትና መሻሻል የታየበት ነው፡፡ ከስታንዳርድ አንጻር 99 በመቶ ለመፈጸም ታቅዶ 3,580 (95.67%) በስታንዳርዱ መሰረት የተከናወነ ነው፡፡

**ሰንጠረዥ 14 የታክስ ተመላሽ ስራዎች አፈጻጸም**

| ተ.ቁ | ቅርንጫፍ | በ12 ወሩ የቀረበ | ክንውን | ክንውን በመቶኛ | በሙሉ ውድቅ የተደረገ | የተቋረጠ | በገንዘብ እንዲመለስ የተወሰነ | ለዕዳ የተካካሰ | በስታንደርዱ የተስተናገደ | ወደ ቀጣይ የዞረ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ | 661 | 661 | 100 | 28 | 129 | 359 | 145 | 661 | - |
| 2 | መካከለኛ 1 | 465 | 465 | 100 | 1 | 82 | 199 | 183 | 465 | - |
| 3 | መካከለኛ ቁ.2 | 277 | 277 | 100 | 14 | 21 | 105 | 137 | 277 | - |
| 4 | ሰሜን ምዕራብ | 261 | 259 | 99 | 1 | 27 | 184 | 47 | 187 | 2 |
| 5 | ምዕራብ | 855 | 804 | 94 | 10 | 148 | 576 | 70 | 749 | 51 |
| 6 | ድሬዳዋ | 36 | 35 | 97 | 1 | 3 | 23 | 8 | 35 | 1 |
| 7 | ምስራቅ | 761 | 754 | 99 | 32 | 67 | 582 | 73 | 748 | 7 |
| 8 | ጅማ | 25 | 25 | 100 | 4 | 8 | 11 | 2 | 25 | - |
| 9 | አዳማ | 24 | 24 | 100 | 1 | 3 | 19 | 1 | 21 | - |
| 11 | መቀሌ | 110 | 99 | 90 | 10 | 15 | 56 | 18 | 94 | 11 |
| 12 | ባህር ዳር | 100 | 99 | 99 | 16 | 5 | 75 | 3 | 99 | 1 |
| 13 | ሀዋሳ | 179 | 178 | 99 | 35 | - | 110 | 33 | 178 | 1 |
| 13 | ኮምቦልቻ | 64 | 62 | 97 | 5 | 1 | 51 | 5 | 41 | 2 |
| | ድምር | 3,818 | 3,742 | 98 | 158 | 509 | 2,350 | 725 | 3,580 | 76 |

**ሰንጠረዥ 15 የተመላሽ አፈጻጸም በገንዘብ**

| ተ.ቁ | ቅርንጫፍ | ጠቅላላ የቀረበ የተመላሽ ጥያቄ | ውድቅ የተደረገ | የተቋረጠ | በገንዘብ እንዲመለስ የተወሰነ | ለዕዳ የተካካሰ | ድምር | ወደ ቀጣይ የዞረ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ | 5,648,115,784.26 | 918,645,031.06 | 754,106,196.44 | 3,045,575,762.83 | 929,788,793.93 | 5,648,115,784.26 | - |
| 2 | መካከለኛ 1 | 1,518,162,820.04 | 313,371,155.31 | 230,415,101.16 | 827,693,731.53 | 146,682,832.04 | 1,518,162,820.04 | - |
| 3 | መካከለኛ 2 | 1,861,555,543.16 | 335,507,668.59 | 555,028,320.89 | 840,792,179.20 | 130,227,374.48 | 1,861,555,543.16 | - |
| 4 | ሰሜን ምዕራብ | 232,178,823.48 | 18,412,723.91 | 38,450,023.47 | 169,493,787.20 | 4,901,567.63 | 231,258,102.21 | 920,721.27 |
| 5 | ምዕራብ | 1,850,733,608.48 | 731,007,993.57 | 225,452,646.45 | 637,419,911.37 | 11,421,899.84 | 1,605,302,451.23 | 245,431,157.25 |
| 6 | ድሬዳዋ | 20,913,541.25 | 985,902.72 | 357,455.10 | 13,855,609.67 | 5,626,688.96 | 20,825,656.45 | 87,884.80 |
| 7 | ምስራቅ | 919,787,089.64 | 502,677,177.40 | 133,522,412.48 | 228,437,740.14 | 35,521,285.40 | 900,158,615.42 | 19,628,474.22 |
| 8 | ጅማ | 13,529,022.00 | 5,091,680.65 | 5,700,523.39 | 1,592,967.99 | 1,143,849.97 | 13,529,022.00 | - |
| 9 | አዳማ | 33,082,784.80 | 1,547,229.47 | 24,021,816.95 | 7,513,738.33 | - | 33,082,784.75 | 0.05 |
| 10 | መቀሌ | 87,401,413.69 | 2,406,043.72 | 20,730,941.79 | 35,680,665.48 | 9,212,333.90 | 68,029,984.89 | 19,371,428.80 |
